# የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና በጢሮ አፈታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በ

ሮማን ተክሌ

## በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች አንዱን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ጅማ ዩኒቨርስቲ ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

ሐምሌ 2011 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና በጢሮ አፈታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት


በ

ሮማን ተክሌ

አማካሪ፡ ጌታቸው አንተነህ (ዶ/ር)


በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች አንዱን ለማሟላት የቀረበ ጥናት


ጅማ ዩኒቨርስቲ ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር



ሐምሌ 2011 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ


## ምስጋና

በቅድሚያ ይህን ጥናት በተቃና ሁኔታ ከዳር እንዳደርስ የረዱኝን የጥናት አማካሪዬ ለሆኑት ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለመላ ቤተሰቦቼ ይህን ጥናት በማካሂድበት ጊዜ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የሞራል ድጋፍ አድርገውልኛል፡፡ በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ጥናቱን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ የዲምቱ፣ አኮና ራጋ ሲባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች፣ መምህራንና ተማሪዎች መረጃ ለማጠናከር በተመላለስኩባቸው አውዶች ሁሉ ከፍ ያለና ቀና ትብብራቸው አልተየኝም ነበር፡፡ ለሁሉም ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገኝን በጀት በመመደብ ጥናቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ላደረገልኝ ድጋፍ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጽህሮተ-ጥናት

ይህ ጥናት ያተኮረው በጢሮ አፈታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው የምርምር ንድፍ ገላጭ ሲሆን፤ በዚህ ዘዴ በመታገዝ ትምህርታዊ ችግሮችን በቀረቡበት ሁኔታ በገለጻ አስደግፎ ለመተንተንና መፍትሂዎቻቸውን ለማቅረብ ምቹ በመሆኑ የተመረጠ ነው፡፡ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ላይ በመመርኮዝ አኮ፣ ዲምቱ፣ ገበራ እና ራጋ ሲባ የተባሉ በወረዳው የሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተደርገዋል፡፡ በወሳኝ ንሞና ዘዴ በመጠቀም በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች ሁሉ ከ1–10 ደረጃ የወጡ 220 ተማሪዎችን ለዚህ ጥናት በመረጃ አቀባይነት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅና የክፍል ምልከታ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግለዋል፡፡ በመጠናዊ እና አይነታዊ መረጃዎች መካከል ያሉ ተዛምዶዎችን በመቃኘትም በበቂ ገለጻና ማብራሪያ ትንተናው በመደገፍ ወደማጠቃለያ ተደርሷል፡፡ በዚሁ መሰረት በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ቢኖሩም በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን ተከታታይነት ባለው አኳኋን አያካሂዱም፡፡ የመምህራኑ ማበረታቻ አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ እንዲማሩ ያደረገላቸው አስተዋጽኦ ያን ያህል ጉልህ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚደረጉት ከማንበብ ጋር የተያያዙ የማበረታቻ ስልቶች ከመጻፍ ክሂል ማበረታቻ ትግበራ አንጻር ሲቃኙ ማንበብን በማበረታታት የተሻለ ጥረት እንዳለ መግለጽ ቢቻልም የማንበብ ክሂል ማበረታቻው በበቂና አስተማማኝ ሁኔታ ይተገበራል ለማለት አያስችልም፡፡ ከመጻፍ ክሂል ጋር ተያይዞ ለተማሪዎቹ የሚቀርበው ማበረታቻ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ዝቅተኛ ይዞታ ላይ የሚገኝና ተማሪዎቹ በጽህፈት ክንዋኔ እንዲበረታቱ ለማድረግ የሚረዳ አለመሆኑን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ መምህራኑ የሚተገብሯቸው የማንበብ ማበረታቻዎች የተማሪዎቹን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል መጠነኛ ድጋፍ ቢኖራቸውም፤ ከተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ዳራ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ጨምሮ፤ ሁሉንም ተማሪዎች በማንበብ ለማሳተፍ በየመማሪያ ክፍሉ ማንበብ አዳጋች የሚሆንባቸውና የቃላትን ትርጉም የማይረዱ ተማሪዎች መኖራቸው፣ ቋንቋውን አስተካክለው መናገር የማይችሉና የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ሁኔታ ብርቱ ትኩረት የሚጠይቅ መሆኑን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ በመጨረሻም ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማበረታቻ ስልቶችና ትግበራ ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፣ የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነትን ማዳበር፣ ተማሪዎቹ እርስበርስ የሚረዳዱበትን እድል ማመቻቸት እና የአጫጭር ጊዜያት የቋንቋ ትምህርት ግቦችን እያስቀመጡ እንዲማሩ ማበረታታት የመፍትሄ ሐሳቦች ተጠቁመው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና........................................................................iii
አጽሕሮተ–ጥናት....................................................................iv
የይዘት ማውጫ.....................................................................v
የሰንጠረዥ ማውጫ...................................................................iiiv

**ምዕራፍ አንድ**

መግቢያ.........................................................................1
1.1 የጥናቱ ዳራ.................................................................1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........................................................4
1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች......................................................5
1.4 የጥናቱ ዓላማ...............................................................6
1.4.1 የጥናቱ አቢይ ዓላማ..........................................................6
1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች......................................................6
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ.............................................................6
1.6 የጥናቱ ወሰን...............................................................7

**ምዕራፍ ሁለት**

ክለሳ ድርሳናት...................................................................8

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ መሰረቶች.........................................................8
2.2 የማበረታቻ ምንነት...........................................................9
2.3 ማበረታቻ ከስነልቦና ጋር ያለው ግንኙነት........................................11
2.4 የቋንቋ ትምህርትና ማበረታቻ....................................................12
2.4.1 በክፍል ውስጥ ጓደኛዊ ደባብ መፍጠር..............................................14
2.4.2 ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍሉን ደባብ በራሳቸው መንገድ እንዲጠቀሙበት ማድረግ..........................14
2.4.3 ተማሪዎቹ የማንነት /የማንነታቸው/ ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ..........................15
2.4.4 ተማሪዎቹ የአጭር ጊዜ ግባቸውን እንዲያስቀምጡ ግፊት ማድረግ .........................15
2.4.5 ለተማሪዎቹ የጥንድና የቡድን ተግባራትን በማቅረብ በራስ መተማመን እንዲያሳድጉ ማድረግ.......................16
2.5 ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ማበረታቻ ስልቶች ...........................................17
2.5.1 ተማሪው ላይ ትኩረት ማድረግ (Person-in-context)................................17
2.5.2 ለሁለተኛ ቋንቋ የሚመጥን ማበረታቻ ማቀድና ማተግበር........................................18

2.5.3 ውስብስብ ተለዋጭስልት (Complex dynamic system)........................18

2.6 ተማሪዎች ሲያነበና ሲጽፉ እንዴት ይበረታታሉ?.............................................19

2.7 ተማሪዎች የማንበብ የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ በሚዳ

ሚሉ ማንበብ መጻፍን መቀናጀት......................................................20

2.7.1 ማንበብን ማበረታታት............................................................. . .... .21

2.7.2 መጻፍን ማበረታታት................................ . . ...................................21

2.8 ንባብና ጽህፈትን የማበረታታቻ ብልሃቶች..፣ ................................................. . .24

2.8.1 አዎንታዊ የሆነ የጽህፈት፣ የንባብና የመማሪያ ክፍል ደባብ መፍጠር.......... . . .24

2.8.2 ጽህፈትን መቀናጀት.........................................................................25

2.8.3 የንባብ ክንዋኔን ለጽህፈት መነሻ ማድረግ............................................ . .26

2.8.4 ደጋግመው እንዲጽፉ ማበረታታት........................................................ .27

2.8.5 እርስበርስ የሚዳዳበትን እድል መፍጠት ................................ . . . ......29

2.9 የተዛመጅ ጥናቶች ቅኝት.............................................................. . ...............29

## ምዕራፍ ሦስት

3 የጥናቱ ስልትና ዘዴ........................................................... . ............. . .33

3.1. የጥናቱ ዘዴ .....................................................................................33

3.2. የጥናት አካላዮች............................................................................ . . . .33

3.3 የተጠኚዎች አሜረጥና የናሙና መጠን.................................................... . . .34

3.4 የሚጃ መሰብሰቢያ ዘደዎች................................ . ............................ . . . . .35

3.4.1 የጽሁፍ መጠይቅ..................................................................35

3.4.2ቃለ-መጠይቅ.........................................................................36

3.4.3 የክፍል ምልከታ.....................................................................36

3.5 የሚጃ መተንተኛ ዘዴ.......................................................... . .......... . .37

## ምዕራፍ አራት

4. የጥናቱ መረጃ ትንተና............................................... . ........................38

4.1 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ

የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ................................................... . .........38

4.2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ

የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ................................................. . .... . .43

4.3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ

የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ..........................................................49
4.4 መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ሲያጽፉ እና ሲያስነብቡ ተማሪዎቹን
ለማበረታታት የሚጠቀሟቸው የማበረታቻ ስልቶች የአነቃቂነት ደረጃ……………..52
4.5 የጥናቱ ግኝቶች ማብራሪያ… ..........................................................66

## ምዕራፍ አምስት

5. የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት..........................................................76
5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ..........................................................76
5.2 አስተያየት..........................................................79
5.3 የወደፊት ጥናት ሊከናወኑባቸው የሚገቡ ርእሰጉዳዮች..........................................82

ዋቢ መጻህፍት..........................................................83
አባሪዎች..........................................................86
አባሪ 1፡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች
ለማወቅ የቀረበ መጠይቅ..........................................................86
አባሪ 2፡ ለመምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ..........................................................91
አባሪ 3፡ የምልከታ መቃኛ ነጥቦች (Observation Check List)..................................92

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ

ገጽ

*ሰንጠረዥ 1፡ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚደረግ ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ*.............................. . ..........................................  . . ...... . . ......39

*ሰንጠረዥ 2፡ በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ*............................. . . ..........................................44

*ሰንጠረዥ 3፡ በአማርኛ ቋንቋ ሲያነቡ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ*.............................. . . ............................49

*ሰንጠረዥ 4፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ የአነቃቂነት ደረጃ የተማሪዎቹ ምላሽ*............................. . . .................................. . 52

*ሰንጠረዥ 5፡ የምልከታ ሂደት ማጠቃለያ*.............................. . . ............................56

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲማሩ መምህራን በሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ትንተና ላይ ነው፡ ማበረታቻ (በእንግሊዝኛው ‹‹motivation›› ከሚለው ቃል ጋር አቻ ትርጓሜ አለው) በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሒደት በተነቃቃ ሁኔታ ለማከናወን በጣም አስፈላጊ የሆነ ግብአት ነው፡ ማበረታቻን አስመልክቶ የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን አቅርበዋል፡፡ ማበረታቻ (motivation) ለእያንዳንዱ ሰው በህይወቱ ውስጥ ከሚያስፈልጉት አበይት ጉዳዮች በጣም ወሳኙ ሲሆን በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ በገሃዱ አለም የሚያጋጥሙትን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወንና የሚጥሙትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ከፍ ያለ ሚና አለው፡ ማበረታቻ የሚለጸው አንድን ክንዋኔ በብቃት ለሚፈጸም በግለሰቡ ውስጥ ባሉ ውስጣዊ እና/ወይም ውጫዊ ግፊቶች ነው፡ እነዚህ ግፊቶች በግለሰቡ ውስጥ የስሜት መነሳሳትን ይፈጥራሉ፤ አቅጣጫ ያመላክታሉ፤ ፍላጎት ያሳድራሉ፤ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በጽናት ተቋቁሞ የማለፍ አስተሳሰብን ያቀዳጃሉ (Dörnyei እና Ushioda, 2013)፡፡ ከዚህ አንጻር ማበረታቻ ከግለሰብ ውስጣዊ ግፊትነቱ ይልቅ

ውጫዊ በሆነ መልኩ በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት የተማሪዎቹን በመማሪያ አውድ ማነቃቃትና ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ በሚደረጉ ስልቶችና ብልሃቶች ላይ ያተኮረ ነው፡

Debra (2015) ባቀረቡት ገለጻ፤ ማበረታቻ በመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ጠቃሚነት እንዳለውና ተማሪዎቹ በማነቃቃት በቋንቋ ትምህርቱ አውድ ወይም ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ጠቁመዋል፡፡ ማበረታቻ ቋንቋን በመማር ሂደት ጉልህ አበርክቶ ያለው መሆኑን Jodai እና Zafarghandi (2013) ይገልጻሉ፡፡ Ushioda (2012) እንደሚሉት ደግሞ፣ የቋንቋ መምህራን በቋንቋ መማር ሂደትና በማበረታቻ ጠቀሜታ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በውል ካልተገነዘቡ ውጤታማ የሆነ ቋንቋ የማስተማር ተግባር ሊያከናውኑ አይችሉም፡ Jodai እና Zafarghandi (2013) እንደሚገልጹት፤ የማበረታቻ ዋንኛ ፍሬ ነገር በተማሪዎቹ አስተሳሰብ ውስጥ ጥልቅ የሆነ አዎንታዊ ስሜት መፍጠር ነው፡ ይህም በተማሪዎቹ ዘንድ እውነተኛ የተፈጥሮ ስጦታ በማነቃቃት፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት በመፍጠርና በማሳደግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ግባዊ፣ ተማሪዎቹንም ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርግ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አበክረው ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ማበረታቻ ለተማሪዎቹ የሚያበረክተው ጠቀሜታ በሚማሩት የቋንቋ ትምህርት ዙሪያ አዎንታዊ ስሜት እንዲይዙ ማድረግ፣ የተፈጥሮ ስጦታቸውን ተጠቅመው የሚማሩትን ትምህርት በንቁ ተሳትፎና ገቢራዊ ተሳትፎ እንዲማሩት ማድረግ ነው፡

ተማሪዎች ከቋንቋ ትምህርቱ ገበታ ጥራት ያለው የማስተማር መማር ሂደት፣ ግብአቶች፣ ተራክቦዎችና ምቹ የመማሪያ እድሎችን በማግኘት በተከታታይ የክሂል ትምህርቱን መቅሰም ይኖርባቸዋል፡፡ ጥሩ መምህራን ተማሪዎቹ በውጫዊ ማበረታቻዎች በበቂ ሁኔታ ተደግፈው በውስጣቸው ያለውን ተፈጥሮአዊ ብርታት በመጠቀም በቋንቋ ትምህርቱ ሂደቱ ከፍ ያለ ተሳትፎ በማድረግ ከታቀደው ትምህርታዊ ግብ እንዲደርሱ ለማድረግ ዘወትር ይጥራሉ (Dörnyei, 2015)፡፡ በዚህ መሰረት የመምህራን ትልቁ ሚና የቋንቋ ትምህርቱን በምቹ ሁኔታዎች ማስደገፍ፣ ብርታት ኖሯቸው ንቁ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ ከታቀደው የትምህርት ግብ እንዲደርሱ መርዳት ነው፡

ሁለተኛ ቋንቋን መማር ጊዜና ተነሳሽነት ይጠይቃል፡፡ አንድ ሰው ሁለተኛ ቋንቋ በመማር አንደበተ ርቱእ (fluent) መሆን ከቻለ ይህ በራሱ የሚያስገኛቸው በርካታ ጠቀሜታዎችና እድሎች አሉ፡ ሁለተኛ ቋንቋ መማር ተግባራዊ፣ አእምሮአዊና ለሰብእና እድገት ጠቀሜታ ካላቸው እንደ ተግባቦታዊ ብቃት ካሉ እድሎች እንዲጎዳኝ ያደርጋል (Dörnyei, 2018)፡፡ **ይሁንና የትምህርቱን ሂደት ስኬታማነት የሚወስኑ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴ፣ የተማሪዎቹ የመማር አላማ፣ የቋንቋ ተጋልጦ** (language exposure)፣ **የማነቃቂያ እና የማበረታቻ ስልቶች ወሳኝ ሚና አላቸው** (Bernaus እና Gardner 2016፣ Carson 2011፣ Dornyei 2015፣ Geberew 2014)፡፡

በየትኛውም የክፍል ደረጃ ውጤታማ የሆነ የንባብና የጽህፈት ቅንጅት የሚጀምረው ተማሪዎቹ በቀደሙት ክፍል ከቀሰሙት እውቀት፣ ካያዙት ልምድ እና ካያዙት ሚዛን በማሳትና በሚዳት ነው፡ ሌላው ንባብና ጽህፈትን የትምህርቱ ማእከል ለማድረግ የሚረዳ መሰረታዊ መሆኑ ተማሪዎቹ ስለሚማሩት ነገር ራሳቸውን እንዲመክሩ ጊዜ ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡ ይህም ቋንቋውን በመማር ወደፊት ምን ማድረግ ወይም መሆን እንደሚፈልጉ ማንዘብንና መወሰንን ያካትታል (Greene, 2012)፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ማንበብና መጻፍ ተማሪዎች የሚኖሩበትን አለም በሚገባ ለማንዘብ የሚረዳቸውና ጠንካራ ትስስር ያለው አእምሮአዊ ሂደት (cognitive processes) በመሆኑ ነው (Syverson, 2016)፡፡ ማንበብና መጻፍ በዚህ ጥናት ከማበረታቻ ጋር በተያያዘ ሚናኮ በአጽንኦት እንዲታዩ የተፈለገበት ምክንያት በአራቱም የቋንቋ አበይት ክሂሎች የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቹን በምን ሚናኮ እንደሚበረታቱ ሚተሹ አዳጋች ስለሆነና ከቅበላ ክሂል ማንበብን፣ ከአመንጪት ክሂል መጻፍን በመውሰድ የጥናቱን መጠት ጠበብ አድርጎ ችግሩን በጥልቀት ሚተሽ በማስፈለጉ ነው፡

***የቋንቋ መምህራን የጽህፈት እና የንባብ ክሂልን በሚያስተምሩበት ክፍል ውስጥ የሚያካሂዱቸው የማበረታቻ ስልቶች*** (motivational strategies) ***ዘለቄታማነት ክሂሉን ለማስረጽ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው*** (Al-Mahrooqi ***እና*** Asante 2010)፡፡ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ የተገነባ፣ ጽዱና ስህተት የሚገኝበት ጽሁፍ እንዲያቀርቡ ማድረግ አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ መምህራን ምኞት ቢሆንም፣ ተማሪዎቻቸው በአብዛኛው ይህን ለማድረግ ፍርሃት ይይዛቸዋል፡፡ Richards ***እና*** Renandya (2012፣ 203) ***እንዳቀረቡት፤ ‹‹በእርግጥም የጽህፈት ክሂልን ለተማሪዎቹ ማስጨበጥ ከሁሉም ክሂሎች ይልቅ አዳጋችነት ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ አዳጋችነቱም ሃሳብ አመንጭቶና ተገቢ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ በማቅረብ ላይ ብቻ ያረፈ አይደለም፡፡ ቃላትን በማቀነባበር፣ በማዋሃድና በተገቢ መንገድ ስርአተ-ነጥቦችን በመጠቀም ተነባቢ ጽሁፍ ማቅረብ ስለሚሳናቸው ጭምር ነው፡፡›› ይህም የመጻፍ ሂደትን በማበረታቻ የማስደገፍ ተገቢነት ጉልህ ያደርገዋል፡፡***

በEllis (2010) ***ገለጻ መሰረት፤*** የጽህፈት ክፍሉ ደባብ አዎንታዊ ፍላጎትን የሚፈጥር፣ ተማሪዎቹን በጽህፈቱ ተግባር እንዲነቃቁ ለማድረግ የሚረዳ፣ የሚጣሟቸውን ችግሮች የሚቃልል፣ በይበልጥ እንዲያነቡና እንዲያስቡ የሚበረታታ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎቹ ጥሩ የጽህፈት ውጤቶችን ባቀረቡ ጊዜም ስራዎቻቸውን ማድነቅ፣ ማበረታታት፣ በሌሎች ሰዎች ፊት እንዲያቀርቡ ማድረግ አዎንታዊ ግፊት ይፈጥርላቸዋል ብለዋል፡፡

***በመሆኑም ይህ ጥናት የጢሮ አፈታ ወረዳ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በ9ኛ መማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና ላይ ያተኮረ ነው፡፡***

የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የማበረታቻ ስልቶች ጠቀሜታ ለመተንተን ጥናቱ በማንበብና መጻፍ ክሂሎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ከቅበላ ክሂል (receptive skill) አንዱን እንዲሁም ከአመንጪነት ክሂል (productive skill) አንዱን በመውሰድ የማበረታቻ ስልቶችና ብልሃቶችን ጠቀሜታ ለመመርመር በማሰብ የተደረገ ምርጫ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት ያተኮረው በጅማ ዞን ጢሮ አፈታ ወረዳ በሚኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ንባብና ጽህፈት ሲያካሂዱ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና ላይ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚያጋጥሙ ክስተቶች በውል ለሚዳት እንደተቻለው በርከት ያሉ ተማሪዎች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ‹አልችልም› በማለት በጽህፈትና ንባብ ክንዋኔዎች ዙሪያ ማሳሰትና ተሳትፎአቸው የተገደበ መሆኑን አጥኚዋ አስተውላለች፡፡ ፍርሃትና ሃፍረትም በመጻፍና ማንበብ ክንዋኔ እንዳይበረታቱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ታስባለች፡፡ መምህራንም ተማሪዎች ትክክለኛ የጽህፈት ውጤቶች ከማቅረብ ማገድ ወደኋላ እንደሚቀሩ በማንዘብ አለያም የበርካታ ተማሪዎችን የጽህፈት ስህተቶች ሚዛም አሰልቺ ተግባር እንደሆነ በሚያምኑም እንደ አንቀጽ እና ድርሰት ያሉ ረዘም ያሉ ጽሁፎችን ለተማሪዎች ቀጣይነት ባለው ሚልኩ በማቅረብ እንዳበረታቱ ሲያደርጉ በአጥኚዋ ካለማየታቸው ሌላ አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት በንባብ ክሂል የተበረታቱ ተማሪዎች እንደሚኖሩ አጥኚዋ ገምታለች፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ከጊዜ ወደጊዜ ዝቅተኛ መሆኑን አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት በተደጋጋሚ የተመለከተች ከመሆኑ ጋር በጢሮ አፈታ ወረዳ በሚገኘው የመቅናዶ ትምህርት ቤትም የአማርኛ ቋንቋ የመቅናዶ ተማሪዎች አለመኖራቸው በታላሚው ቋንቋ የሚበረታቱ ተማሪዎች ባለመኖራቸው ይሆን? ብላ እንድታስብ አድርጓታል፡፡

ስህተት አንዱ የመማሪያ ማገድ ነውና፤ እየተሳሳቱም ቢሆን የንባብና የጽህፈት ክሂልን ማሻሻል እንደሚችሉባቸው አጥኚዋ ታስባለች፡፡ ወደፊት ተማሪዎቹ ጥሩ ጸሃፊ፣ ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ በበቂ ልምምድ ማዳበር ያለባቸው ዛሬ ነው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ልምምዶች ዘለቄታ ባለው ሚልኩ እንዲያካሂዱ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎችና ክትትሎች ወሳኝ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ብላ ታምናለች፡፡ በዚሁ መሰረት ይህ ጥናት መምህራን በንባብና ጽህፈት ክፍለጊዜያት ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ምን ይመስላሉ?

**ማበረታቻዎቹ የቱን ያህል ለተማሪዎቹ የንባብና ጽህፈት ልምምድ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው? የሚሉትን ጉዳዮች ማጥናት አስፈልጓል፡፡**

ከዚህ ጥናታዊ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጥናቶች በአጥኚዋ ተዳስሰዋል፡፡ ከውጭ ሀገር ጥናቶች Masgoret እና Gardner (2013) ‹‹Attitudes, Motivation, and Second Language Learning›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት፣ Clément እና Kimberly (2014) ‹‹Motivation, Self-confidence, and Group Cohesion in the Foreign Language Classroom in Oman, English Language Teaching›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ተቃኝተዋል፡፡ ከሀገር ውስጥ ደግሞ፣ የዘውዱ (2014)፣ **የእንዳለ** (2015)፣ **የአማረ** (2006)፣ **የልዑልሰገድ** (2007) ቀደምት ጥናቶች በአጥኚዋ ተቃኝተዋል፡፡ እነዚህ ከዚህ ቀደም የቀረቡ ጥናቶች በተማሪዎቹ የጽህፈት ትምህርት አቀባበልና የጽህፈት ስህተት የተቃኙ ሲሆኑ ይህ ጥናት ከተማሪዎቹ የጽህፈት ትምህርት አቀባበልና የጽህፈት ስህተቶች ይልቅ በአማርኛ **ቋንቋ** መምህራን የንባብና የጽህፈት ክሂል አተገባበር፣ በተለይም በማንበብና መጻፍ ክፍለጊዜ የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች፣ የማበረታቻ ስልቶቹ ሁለተኛ **ቋንቋን** በማንበብና መጻፍ **ክፍል ከማስተማር አንጻር ባላቸው ጠቀሜታዎች** ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ይለያል (ዝርዝሩ *በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት* አምድ ቀርቧል)፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1. *የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ምንድናቸው?*
2. *የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው?*
3. *የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው?*
4. *የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስነብቡና ሲያጽፉ የሚጠቀሙት የማበረታቻ ስልት አነቃቂ ነውን?*

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ አቢይ አላማ

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በጡሮ አፈታ ዉረዳ በሚኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች መተንተን ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ምን እንደሚመስሉ መመርመር፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ መፈተሽ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ መፈተሽ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስነብቡና ሲያስጽፉ የሚጠቀሙት የማበረታቻ ስልት የአነቃቂነት ደረጃ መፈተሽ፡፡

### 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የአማርኛ ቋንቋ አበይት ክሂሎችንና ንኡሳን ክሂሎችን በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል በተገቢ ሁኔታ ለማስተማር መምህራን የሚያካሂዷቸው የማበረታቻ ስልቶች ለተማሪዎቹ የቋንቋ ለመዳ በጣም ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ ጥናቱ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ቋንቋን በማስተማርና የማበረታቻ ስልት ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦች የቋንቋ መምህራን ማበረታቻን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገብሩ ፍንጭ በመጠቆም ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታሰባል፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሁለተኛ ቋንቋን በማበረታቻ አስደግፎ ስለመተግበር ጥናቱ የሚያቀርባቸው ጥቆማዎች ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ እየተበረታቱ እንዲማሩ ለማድረግ ስለሚረዳ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በቋንቋ ማበረታቻ አተገባበር ጥናቱ የሚያቀርባቸው ድምዳሜዎች የቋንቋ ትምህርት በሚያቅዱ እና የትምህርቱን ስራ በሚመሩ ኃላፊዎች አይን እንዲታዩ በማድረግ ረገድ የበኩሉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ሌሎች በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ወደፊት ጥናታቸውን ለማከሚኮዝ ለሚሊጉ ወይም በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለማካሄድ ለሚሱ አጥኚዎች የሚበረክተው ፋይዳ ሊኖር እንደሚችልም ይገማታል፡፡

### 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ያተኮረው ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች እንዴት ያሉ እንደሆኑ መተንተን ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በክፍል ውስጥ በመምህርና በተማሪ መካከል ከሚከናወኑ ማናቸውም ግንኙነቶችና ተራክቦዎች ይልቅ በአማርኛ ቋንቋ የማንበብና መጻፍ ትምህርት የማበረታቻ ስልቶች ተገቢነት ላይ አትኩሯል፡፡ የማንበብና መጻፍ ክሂሎች በዚህ ጥናት ከማበረታቻ ጋር በተያያዘ ሜለኩ በአጽንኦት እንዲታዩ የተፈለገበት ምክንያት በአራቱም የቋንቋ አበይት ክሂሎች የቋንቋ መምህራን ተማሪዎቹን በምን ሜለኩ እንደሚበረታቱ ሜቲተሹ አዳጋች ስለሆነና ከቅበላ ክሂል ማንበብን፣ ከአማጨት ክሂል መጻፍን በመውሰድ የጥናቱን ሜቼት ጠበብ አድርጎ ችግሩን በጥልቀት ሜቲተሽ በማስፈለጉ ነው፡

በጥናት አካባቢ የዚህ ጥናት ትኩረት በጅማ ዞን በጢሮ አፈታ ወረዳ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ዲምቱ፣ አኮ፣ ገበራ እና ራጋ ሲባ) የተገደበ ነው፡ በአራቱ ተተኳሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2011ዓ.ም ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ ተማሪዎች ጥናቱ ያተኮረው በ9ኛ ክፍሎች ላይ ነው፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 ንድፈ-ሃሳባዊ ማእረፆች

ያለንበትን ዘመን የሚያከብሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ በተማሪዎች መካከል የሚታዩ እንደ አመለካከት፣ ችሎታ፣ ዝንባሌ፣ ማቀታት፣ የመማሪያ ስልት፣ የግንዛቤ ደረጃ የመሳሰሉ ግለሰባዊ ልዩነቶችን ያካተቱ የማስተማሪያ ስልቶችን አቅዶና ከማበረታቻ ስልቶች ጋር አቀናጅቶ ወይም አጣጥሞ መቅረብ ተገቢ መሆኑን ይጠቁማሉ (Bernaus እና Gardner 2016፣ Carson 2011፣ Dornyei 2015፣ Geberew 2014)፡፡ በተለይ ቋንቋን የመማር ሂደት በበቂ የማበረታቻ ስልቶች ካልተደገፉ የማስተማር መማር ሂደቱ የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል Al-Mahrooqi እና Asante (2010) ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ መሰረት በክፍል ውስጥ የሚሰጥ የጥናቱ በማበብር ሜዳፍ የቋንቋ ክሂሎች ላይ አትኩሯል፡፡

ትምህርት ከአላማና ይዘት የመነጩ ክንዋኔዎች ላይ ተመስርቶ ሲታቀድ ለመማሪያ ክፍሉ ተስማሚ የሆነ የማበረታቻ ስልት አብሮ መታቀድ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

ቋንቋን በማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የሚተገበሩ የማበረታቻ ስልቶች ተገቢነት በአብዛኛው የሚወሰነው በመምህራኑ የማስተማር ልምድ እና በጥናትና ምርምር ተደግፈው በተመረጡ ስልቶች ነው (Cedar 2014)፡፡ ከነዚህ መካከል ዋንኛው የተማሪዎቹን የመማር ዝንባሌና ባህሪ ያካተቱ የማበረታቻ ስልቶች ይበልጥ ውጤታማ እንደሆኑ Bernaus እና Gardner (2016)፣ Carson (2011) ያስረዳሉ፡፡ አንዳንድ ምሁራን ቅይጥ የማበረታቻ ስልቶችንና ንኡሳን ስልቶችን (micro-strategies) መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ይጠቁማሉ (Bernaus እና Gardner 2016)፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚተገበሩ በርካታ ውጤታማ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶች አማራጮች አሉ፡፡ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት በጎ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ እንደ አንድ የማበረታቻ ስልት ይቆጠራል (Dornyei 2018)፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምሁራን መሰረት በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ታቅደው የሚቀርቡ ማበረታቻዎች በመምህራኑ የማስተማር ልምድ እና በጥናትና ምርምር ተደግፈው ለተማሪዎቹ እድሜ፣ የቋንቋ ዳራ፣ ወቅታዊ ችሎታ ተመጣጣኝ በሆኑ ስልቶችና ብልሃቶች ላይ ማትኮር ይኖርበታል፡፡ የትምህርቱን ተፈላጊ ግብ በተነቃቃ አውድ ተጨባጭ ለማድረግም ከአንድ አይነት ተዘውታሪ የማበረታቻ ስልት ይልቅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቅይጥ ወይም ተለዋዋጭ ማበረታቻዎች ላይ ማትኮር ያስፈልጋቸዋል፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ማበረታቻ የሚሰጠው ጠቀሜታ ተማሪውን ውጤታማ እንዲሆን ካለው ከፍ ያለ እገዛ እና የተቀመጠውን የትምህርት ግብ ስኬታማ ለማድረግ ካለው ድጋፍ አንጻር የሚጤን ነው፡፡ ማበረታቻ የተማሪውን የመማር ፍላጎት በበለጠ ለማነሳሳት፣ በመማሩ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ፣ የሚማረውን ትምህርት በተሻለ የኃላፊነት መንፈስ ሆኖ እንዲያከናውን፣ በክፍሉ ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ተባባሪ፣ ተሳታፊ፣ አከናዋኝ እንዲሆንና የግንዛቤ ኃይሉን ሁሉ በስራ ላይ በማዋል የሚፈለገውን እውቀት እንዲቀስም ለማድረግ የሚረዳ የስልት ቋት ነው (Geberew 2014)፡፡ ማበረታቻ በሚከናወነው ትምህርታዊ ተግባር ዙሪያ የመገንዘብና የመፈለግ ስሜትን በማነሳሳት የሚፈለገው ግብ እንዲጨበጥ ለማድረግ የሚረዳ፣ እውቀትንና አካላዊ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ ግብር ነው (Al-Mahrooqi እና Asante 2010)፡፡

በመሆኑም፣ በቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታይ ውስብስብነትና አዳጋችነት የሚታይበትና በተለይም ተማሪዎች በፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲማሩ ከማድረግ አንጻር ማበረታቻ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡

## 2.2 የማበረታቻ ምንነት

ማበረታቻ በመማር ማስተማር ክንዋኔ ተማሪዎች በመነቃቃትና በተሳትፎ እንዲሁም በኃላፊነት ስሜት ትምህርቱን እንዲከታተሉና ለማስጨበጥ በተፈለገው እውቀት ዙሪያ ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ አይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ Williams እና Burden (2015) እንደገለጹት፣ ማበረታቻ ከሚፈለግ ግብ ላይ ለመድረስና ስኬታማ ለመሆን የሚገፋፋ ውስጣዊ ኃይል ነው፡፡ ማበረታቻ ማንኛውም ሰው ባለው ውስጣዊ ፍላጎትና ምኞት ይደገፋል፡፡ ማበረታቻ ማሳካት ለሚፈለገው ውጤታማነት አነቃቂ ወይም ብርታት ሰጪ ኃይል ሲሆን በሚፈለገው አቅጣጫ ለመጓዝ ብርታት ወይም ጥንካሬን ይፈጥራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አንድን የተወሰነ ጉዳይ ለመፈጸም ፍላጎት ይዘን እንነሳለን፡፡ የምንፈልገውን ነገር ለማሳካት ንቅናቄ የምናደርገው በማበረታቻ ድጋፍ ነው፡፡

በዘመናዊው ስነልቦናዊ ትርጓሜው፣ ማበረታቻ ምን አይነት ልምዶችን ማካበት፣ ምን አይነት ግቦችን ማሳካት እንዳለባቸው የሚወስኑት ምርጫ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ማበረታቻ ምን አይነት ስልቶችን መከተል፣ በምን አይነት ብልሃትና ጥረት መጓዝ እንዳለባቸው እና ለጥረቶች ራስን ተገዢ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ማበረታቻ በእውቀት እና በብልሃት

ላይ መመስረት ይኖርበታል፡፡ የጥረቱ መጠን በይበልጥ አጽንኦት ሲደገፍ የሚፈለገውን ስኬት ለመቀዳጀት ያግዛል፡፡ ማበረታቻ በእውቀት የተደገፉ አማራጮችን ማቀድና ዘላቂነት ባለው መልኩ መተግበርን ግድ ይላል (Shaaban እና Ghaith 2013)፡፡ በShaaban እና Ghaith መሰረት፤ ማበረታቻ ሦስት ሰንሰለታዊ እርከኖች አሉት፡፡ እነዚህ እርከኖች በሚከተለው አይነት ቅንጅት ይፈጥራሉ፡፡ (1) አንድን ተግባር ለመፈጸም የተቀመጠ ምክንያት፣ (2) ድርጊቱን ለመተግበር መወሰንና (3) ድርጊቱን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መተግበር፡፡

በዚህ መሰረት ማበረታቻ በሶስት ምንዝሮች ላይ ይመረኮዛል፡፡ አንድን ተግባር ለመፈጸም የተቀመጠ ምክንያት ማበረታቻን መተግበር ለምን እንዳስፈለገ የሚገልጽ አላማ መኖር እንዳለበት የሚጠቁም ነው፡፡ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ አንጻር የተቀመጡ የትምህርት ግቦችን ለማስጨበጥ የሚረዳ መነቃቃት፣ ተሳትፎ፣ የግልና የጋራ ጥረት አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ድርጊቱን ለመተግበር መወሰን ደግሞ በእውቀት የተደገፉ የማበረታቻ አማራጮችን ማቀድን የሚጠይቅ ሲሆን፤ ድርጊቱን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መተግበር እንዲሁ የማበረታቻ ስልቶችን ዘላቂነት ባለው መልኩ መተግበርን እንዲሁም የማበረታቻ ስልቶችን ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የቋንቋ ዳራና የመማሪያ አውድ ጋር አስማምቶ ማቅረብን የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ንባብ እና ጽህፈትን ለማስተማር የተቀመጠ ምክንያት ተማሪዎቹ የንባብና ጽህፈት ክሂልን በክፍል ውስጥ እንዲማሩ የተቀመጡ አላማዎች ሲሆኑ፤ የማበረታቻ ስልቶች የጽህፈት ክሂልን በተጨባጭ የማስተማሪያና የማነቃቂያ ዘዴዎች በማሳገዝ መተግበርን ይመለከታል፡፡ ተማሪዎቹ የንባብ እና ጽህፈት ክሂልን እንዲያዳብሩ የማበረታቻ ስልቱ በተገቢና ተለዋዋጭ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መተግበር ይኖርበታል፡፡

## 2.3 ማበረታቻ ከስነልቦና ጋር ያለው ግንኙነት

ይህ በማበረታቻና በቋንቋ ትምህርት ግንኙነት ላይ የተማከለ ጥናት ቀዳሚ ትኩረቱ የአዎንታዊ ስነልቦና ታሳቢዎች ከማበረታቻ ንድፈሃሳቦች ታሳቢዎች የሚዋሃዱበትን ስልት መሰረት በማድረግ በሰፊው ትኩረት እያገኘ በመጣው የቀለም ትምህርት ሂደት እንዴት ጠቀሜታ ላይ እንደሚውሉ ማጥናትን ነው፡ በትምህርት

ማዕከ ሊጨበጡ የሚቡ ግቦች፣ የሚጠበቁ እምነቶች፣ ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው እሴቶች በአምንታዊ የስነ ልቦና ተለዋዋጮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል፤ ከቀለም ትምህርት ትግበራ ጋር የተቆራኙ ሶስት ስነ ልቦናዊ ተጽእኖ ያላቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ማበረታቻ፣ በራስ መተማመን ከፍ በማድረግና ጭንቀትን በማስወገድ በትምህርት ዙሪያ የሚጠበቀውን ግብ ለማሳካትና ተማሪዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመቅረጽ የየራሳቸው ተጽእኖ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ባህርያት በክፍል ውስጥ በሚካናወኑ ትምህርታዊ ትግበራዎች በተለያየ መጠን በተማሪዎቹ የሚጸባረቁ በመሆናቸው የሚታዩ ግለሰባዊ ልዩነቶችን አጥጠ ማዝናዊ በሆነ ሜልክ የዉል ተሳትፎን እውን በማድረግ የሚጠበቀው ትምህርታዊ ግብ እንዲጨበጥ ማድረግ ተገቢ ይሆናል (Williams እና Burden, 2015)፡፡

ማበረታቻ ለእያንዳንዱ ሰው በህይወቱ ውስጥ ከሚያስፈልጉት አበይት ጉዳዮች በጣም ወሳኙ ሲሆን፤ በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ በገሃዱ አለም የሚያጋጥሙትን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወንና የሚጥሙትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ከፍ ያለ ሚና አለው፡ ማበረታቻ የሚለጸው አንደን ክንዋኔ በብቃት ለሚያጸም በግለሰቡ ዘንድ ባሉ ውስጣዊ እና/ወይም ውጫዊ ግፊቶች ነው፡ እነዚህ ግፊቶች በግለሰቡ ውስጥ የስሜት ማነሳሳትን ይፈጥራሉ፤ አቅጣጫ ያመላክታሉ፤ ፍላጎት ያሳድራሉ፤ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በጽናት ተቋቁሞ የማለፍ አስተሳሰብን ያቀዳጃሉ (Dörnyei እና Ushioda, 2013)፡፡

ምንጫቸው ግለሰቡ ራሱ በመሆኑም ሆነ በሌላ ሰው ግፊት የተገኙ የማበረታቻ አይነቶች እዉነተኛ የተፈጥሮ ስጦታ (intrinsic) እና ዉጫባህርያዊ (extrinsic) በማለል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በአጠቃላይ ዉጫባህርያዊ ማበረታቻዎች ለምሳሌ ከአሰልጣኞች፣ ከመምህራን፣ ከወላጆችና ሌሎች ለማበረታታት ምክንያትና የማበረታቻ እዉቀት ካላቸው ሰዎች ሊገኙ የሚችሉ ሲሆኑ፤ በአመዛኙ በዉጫባህርያዊ ማበረታቻ ላይ የሚያዘነብሉ ግለሰቦች በእዉነተኛ የተፈጥሮ ስጦታ ከሚበረታቱት አንጻር ሲታዩ ስኬታማነታቸው ያነሰ ነው፡ በዉጫባህርያዊ ማበረታቻዎች ላይ የሚደገፉ ሰዎች አንደን ተግባር ለማከናወን ያላቸው ተነሳሽነት በራሳቸው ተነሳሽነት ተግባሩን ለማከናወን ካላቸው ግፊት ይልቅ በሽልማት (reward) ላይ የተመሰረተ ግፊት ያላቸው ናቸው፡ ይሁንና ማንኛውም ግለሰብ በተወሰነ ሜልኩ ዉጫባህርያዊ ማበረታቻ እንደሚያስፈልገው ጥናቶች ይጠቁማሉ (Clement, 2012፣ Dörnyei እና Ushioda, 2013)፡፡

በአኳያው በራስ መተማመን ተግባራትን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የሚጠቅም ስነ ልቦናዊ ማገልገያ ነው፡ በራስ መተማመን አንድ ሰው በራሱ ችሎታና አቅም ያለው የሚደገፍ ዝንባሌ ሲሆን ይህን ችሎታና አቅም ስራ ላይ በማዋል አንደን ክንዋኔ አደራጅቶና አከናውኖ ውጤታማ በሆነ ሜልኩ ለሚያጸም ያለው ብቃትም ነው፡ በትክክለኛ ግንዛቤ እና የማከናወን አቅም የተነቃቃ በራስ መተማመን ራስን ለማበረታታት እና ተግባራትን አነሰም በዛ በብቃት ለማከናወን ሰፊ ጠቀሜታ እንዳለው ሲታመን በአንጻሩ እዉነተኛ የሆነ በራስ መተማመን

ለሚያደላቸው ሰዎች ዉጨባህርያዊ ማበረታቻ ሚያረግ ያስፈልጋቸዋል (Williams እና Burden, 2015)፡፡

በዚህ ስነልቦናዊ የማበረታቻ ንደፈ ሃሳብ ማሰረት ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው ከእዉነተኛ የተፈጥሮ ስጦታ (intrinsic) ማበረታቻ ስልት ይልቅ በዉጨባህርያዊ (extrinsic) የማበረታቻ አይነት ላይ ያተኩራል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ የሚያተኩረው የአማርኛ ቋንቋ ማምህራን በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች በሚያደርጓቸው የማበረታቻ ስልቶች ምንነትና ጠቀሜታ ላይ የሚያተኩር በመሆኑና ይህም ተማሪዎቹ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ተፈጥሮአዊ በሆነ ማንገድ በዉስጣቸው ካለው ተነሳሽነትና ግፊት ይልቅ ማምህራኑ የሚያደርጉላቸዉን የማበረታቻ ስልቶች በመመርመር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው፡

## 2.4 የቋንቋ ትምህርትና ማበረታቻዎች

Debra (2015) ባቀረቡት ገለጻ፤ ማበረታቻ በመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ጠቃሚነት እንዳለዉና ተማሪዎቹ በማቃቃት በቋንቋ ትምህርቱ አዉድ ወይም ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ጠቁመዋል፡፡ ማበረታቻ ቋንቋን በመማር ሂደት ጉልህ አበርክቶ ያለው መሆኑን Jodai እና Zafarghandi (2013)ም ይገልጻሉ፡ እነዚህ ምሁራን እንደሚሉት፤ የቋንቋ ማምህራን በቋንቋ መማር ሂደትና በማበረታቻ ጠቀሜታ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በዉል ካልተገነዘቡ ዉጤታማ የሆነ ቋንቋ የማስተማር ተግባር ሊያከናዉኑ አይችሉም፡ የማበረታቻ ዋንኛ ፍሬ ነገር በተማሪዎቹ አስተሳሰብ ዉስጥ ጥልቅ የሆነ አዎንታዊ ስሜት መፍጠር ነው፡ ይህም በተማሪዎቹ ዘንድ እዉነተኛ የተፈጥሮ ስጦታና ፍላጎት በመፍጠርና በማዳበር የመማር ማስተማሩን ሂደት ግባዊ፣ ተማሪዎቹንም ይበልጥ ዉጤታማ የሚያረግ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን Jodai እና Zafarghandi (2013) አበክረው ይጠቁማሉ፡፡

ስኬታማ ተማሪዎች ምርጫዎቻቸዉን፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸዉን በሚገባ ጠንካራ ጎኖቻቸዉን ዉጤታማ በሆነ ማንገድ የሚጠቀሙት ሲሆን ደካማ ጎኖቻቸዉን ለማሻሻል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ዉጤታማ የቋንቋ ትምህርትም ከተማሪዎቹ ጥልቅ ስሜት ጋር መዛመድ ይኖርበታል (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ ማምህራንም ትምህርቱን ከተማሪዎቹ ጥልቅ ስሜት ጋር ለማዛመድ የሚያስችሉ ስልቶችና ብልሃቶችን በመቀየስ ተማሪዎቹ ከቋንቋ ትምህርቱ በተሻለ ሚልኩ እዉቀትና ግንዛቤ እንዲቀስሙ ድጋፍ ሚያረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ማበረታቻ ደግሞ አንዱ ማንገድ ነው (Reeve, 2013)፡፡

ተማሪዎች ከቋንቋ ትምህርቱ ገበታ ጥሪት ያለው የማስተማር መማር ሂደት፣ ግብአቶች፣ ተራክቦዎችና ምቹ የመማሪያ እድሎችን በማግኘት በተከታታይ የቋንቋ ትምህርቱን መቅሰም ይኖርባቸዋል፡፡ ጥሩ ማምህራን ተማሪዎቹ በዉጫዊ ማበረታቻዎች በበቂ ሁኔታ ተደግፈው በዉስጣቸው ያለዉን ተፈጥሮአዊ ብርታት በማጠቀም

በቋንቋ ለመዳ ሂደቱ ከፍ ያለ ተሳትፎ በሚደረግ ከታቀደው ትምህርታዊ ግብ እንዲደርሱ ለሚደረግ ዘወትር ይጥራሉ (Dörnyei, 2015)፡፡

ከፍ ሰል በቀረበት ምሁራን ገለጻዎች መሰረት ተማሪዎች በተነቃቃና ከፍ ባለ ተሳትፎ ልዩ ልዩ ተግባራትና ክንዋኔዎችን የሚከናወኑባቸውን የመማሪያ አውዶች ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ለሚሰጡት ትምህርት ተመስጦ እንዲፈጥሩ ሚደረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት በሃላፊነት ማሳደስ፣ በራስ መተማመንና ተነሳሽነት እንዲሚዱ ሚደረግ ያስፈልጋል፡፡ የቋንቋ መምህራን የሚገብሯቸው ማበረታቻዎች በተማሪዎቹ የመማር ፍላጎትና አስተሳሰብ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ የሚፈጥሩ፣ ለመማር ማስተማሩ አውድ አሳታፊነትና አከናዋኝነት ምቹ አውድ የሚያስገኙና የክፍል ውስጥ ተግባራትና ክንዋኔዎችን በተገቢ ሁኔታ በማስለጥ ተማሪዎቹ የታቀዱትን ትምህርታዊ ግቦች እንዲጨብጡ ለሚደረግ የሚረዱ መሆን ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡ የማበረታቻ ዋንኛ ፍሬ ነገር በተማሪዎቹ አስተሳሰብ ውስጥ ጥልቅ የሆነ አዎንታዊ ስሜት መፍጠር ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፡

የማበረታታት ሁኔታ በየጊዜው ተለዋዋጭ በመሆኑ የቋንቋ ተማሪዎችን ማበረታታት ሁልጊዜ ጠብቆ ማቆየት አስቸጋሪነት የሚታይበት ሂደት ነው፡ የቋንቋ ትምህርት ሲታቀድ መምህራን ማስተዋል ያለባቸው ተማሪዎቹ የተለያየ ፍላጎትና የሚጠብቁት ነገር እንዳላቸው ነው (Ushioda, 2012)፡፡ ከUshioda በተጨማሪ በGardner እና Lambert (2009) መሰረት የሚከተሉት ስልቶች የቋንቋ ተማሪዎችን ውጫዊ ባህርያዊ ማበረታቻ ከፍ ለሚደረግ ውጤታማ የሆኑ ዘዴዎች ናቸው፡

### 2.4.1 በክፍል ውስጥ ጓደኛዊ ደባብ መፍጠር

በክፍል ውስጥ ጓደኛዊ ደባብ መፍጠር ተማሪዎቹ ሁሉ እውቅና እና ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑን እንዲያስቡ ለሚደረግ ይረዳል፡፡ በርካታ ተማሪዎች ሌሎች አቻዎቻቸውንና መምህራቸውን ካወቁ በኋላ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለሚደረግ ምቾት ይሰማቸዋል፡፡ ተማሪዎቹን የሚከባከብና ምቾት እንዲሰማቸው የሚያደርግ የክፍል ደባብ (environment) መፍጠር እያንዳንዱ ተማሪ ራሱን የማየው ክፍል አካል አድርጎ እንዲቆጥር ስለሚያደርገው ማበረታቻን ተግባራዊ ለሚደረግ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ በዚህ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገቢና ተለዋዋጭ የማበረታቻ ስልቶችን ከማቀድና ዘላቂ በሆነ ሜሌኩ ከመተግበር ሚናቸው ጎን ለጎን በክፍል ውስጥ ጓደኛዊ ደባብ መፍጠር መቻላቸው እንድ የማበረታቻ ግብአት የሚቆጠርና በተማሪዎቹ መካከል የመግባባት፣ የመተማመንና የተሳትፎ ደባብ ለማስፈን ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ ነው፡

### 2.4.2 ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍላቸውን ደባብ በራሳቸው ማገድ እንዲጠቀሙበት ሚደረግ

ለተማሪዎቹ ተማሪ-ተኮርና ብስጬ የማያደርጋቸው የክፍል ደባብ መፍጠር ለትምህርት አቀባበሉ ሂደት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡ በራሳቸው ማገድ እንዲገለገሉበት ማድረግ (Personalizing) ተማሪዎቹ ዘና እንዲሉና ጓደኛዊነት እንዲሰማቸው ስለሚያደርግ ቋንቋ የመማር ፍላጎታቸውን በማሳሳት ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡ ምቾትና ክብከቤ የሚሰማቸው ተማሪዎች ጭንቀት ሳይሰማቸው የተሳትፎ እድሎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ ደምጻቸውን ከፍ አድርገው ለማበብ ብሎም የመተቸት ፍርሃት ሳይሰማቸው ድርሰት ለመጻፍ ማቃታት ያገኛሉ (Ushioda, 2012፣ Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉን ደባብ ራሳቸው የሚፈጥሩት ከሆነ ስለሚጽፉት ጉዳይ የሃላፊነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል፤ እርስ በርሳዊ ግንኙነታቸውን ያጠነክራል፡፡ በሚጽፉት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳብ የመግለጽ ነጻነት እንዲሰማቸው፡ ያሉባቸው ጭንቀቶች እንዲቀነሱና ትኩረታቸውን እንዲሰበስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ የአሚሮኛ ቋንቋ መምህሩ ሚና በተገቢ ሁኔታ ክፍሉን መምራትና ተግባራትን መምራትን ይሆናል ማለት ነው፡

## 2.4.3 ተማሪዎቹ የመቻናወን /የመቻል/ ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ

አከናውናለሁ ወይም እፈጽማለሁ የሚል ስሜት ተማሪዎች እንዲሰማቸው ማድረግ ተማሪዎችን ለማበረታታት ትልቅ ድርሻ አለው፡ በዚህ የተነሳ መምህራን አዎንታዊ ግብረ መልስ እና ማጠናከሪያ ስለመስጠት እርግጠኛ መሆን አለባቸው፡ ይህን በማድረጋቸውም የተማሪዎቹን እርካታ እና አዎንታዊ የራስ ግምገማ ለማሳደግ ይችላሉ (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ ተማሪ የመቻናወን ስሜት ሊሰማው ከቻለ ራሱን አጠናክሮ በማሰራት ቋንቋውን ለመማር /ለማጥናት/ እና ውጤት ላይ ለማድረስ ግፊት ይኖረዋል፡፡ በመምህራን የሚሰጡ አዎንታዊና አሉታዊ አስተያየቶች በማበረታታት ላይ የየራሳቸው ተጽእኖ ያሳድራሉ፡ ይሁንና የጥናት ውጤቶች እንደሚያረጋግጡት ተማሪዎች በደበልጥ ስሜታቸው የሚቀሰቀሰው በአዎንታዊ ግብረመልሶች እና ውዳሴዎች ነው፡ አድናቆትና ምስጋና የተማሪዎቹን በራስ መተማመን፣ ብቃት እና አዎንታዊ ግፊት ለማነባት ወይም ለማከበባከብ ይረዳሉ (Ushioda, 2012)፡፡

## 2.4.4 ተማሪዎቹ የአጭር ጊዜ ግቦቻቸውን እንዲያስቀምጡ ግፊት ማድረግ

የቋንቋ ተማሪዎች የራሳቸውን ግቦች በማስቀመጥና በሚጠብቁት ውጤት አቅጣጫ የራሳቸውን የአጠናን ስልቶች በመከተል ውጤታማ ለመሆን ይችላሉ፡ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው በማገዝ፣ የቋንቋ መማር ፍላጎታቸውን በመወሰንና ለምን ቋንቋውን እንደሚጽፉ በማወቅ ትምህርታዊ ግባቸውን ሊያሳኩ ይችላሉ (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ ከቋንቋ ትምህርቱ የሚጠብቁትን ቁምነገር ለይቶ ማወቅና ግብን ማየት ወደ ማበረታታት ይመራቸዋል፡፡ ይህም በበኩሉ ከፍ ወዳለ የቋንቋ ብቃት ያደርሳቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው እንደ ከተናጋሪዎቹ ጋር በበቂ ሁኔታ ተግባቦት ማካሄድ፣ በቋንቋው የተጻፉ መጻህፍትን በትክክል ማንበብና አገናዝቦ መጻፍ የመሳሰሉ የተወሰነ የአጭር ጊዜ ግብ

አስቀምጠው በመሆ ማትተሙ ሂደት እንዲሰተፉ ማበረታታት ይጠበቅበቸዋል (Ushioda, 2012)፡፡ ከፍ ሲል ከቀረበት ገለጻዎች ማንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎች ስለሚኬት የትምህርት ይዘቶች ትምህርታዊ ግቦችን ማቅጠሞ ከፍ ያለ የግፊትና የተነሳሽነት ምንጭ ነው፡ የተሰበሰበ ትኩረት በመፍጠር በሚከናወኑት ተግባር ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል፡፡ አቅጣጫም ያስይዛቸዋል፡፡ ለምሳሌ፤ የአንድ ክፍለ ጊዜ ወይም የሁለት ተከታታይ ክፍለጊዜያት የትምህርት ይዘት ትምህርታዊ ግቦች ‹‹ከዚህ ወይም ከነዚህ ክፍለጊዜያት ትምህርቶች በኋላ ጥሩ ገላጭ ድርሰት ጽፌ ለመምህሬ አቀርባለሁ›› ብለው ተማሪዎቹ ሊያቅዱ ይችላሉ፡ በዚህ ትምህርታዊ ግብ ተመርኩዘው ገላጭ ድርሰት እንዴት ያለ እንደሆነ፣ ቅርጽና ይዘቱ ምን እንደሚካትት ማሰላሰልና ማጣጣሙን ትኩረታቸው ያደርጋሉ፡ ትምህርታዊ ግብ የማቅጠሙ ማበረታቻ ልምምዱን አነቃቂና ይብልጥ አሳታፊ ያደርገዋል፡፡ በማነቃቃት ላይ የተመሰረተው ገላጭ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ትኩረታቸውን አቅጣጫ በማስያዝ ከሚፈለገው ጥሩ ገላጭ ድርሰት ወደመጻፍ ክንዋኔ በተመስጦ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡

### 2.4.5 ለተማሪዎቹ የጥንድና የቡድን ተግባራትን በማቅረብ በራስ መተማመን እንዲያሳድጉ ማድረግ

ተማሪዎች በማስራት፣ በማድረግ፣ በመጻፍ፣ በመፍጠር፣ ችግር በመፍታት ይማራሉ፡ ኢ-ተሳትፎአዊነት (passivity) የተማሪዎቹን ማበረታታት እና ትኩረት ይቀንሳል፡፡ የተማሪዎች ብርታት፣ ተሳትፎ እና ፈቃደኛነት የክፍል ውስጥ ትምህርቱ የውይይት ጥራት ለውጤታማ መሆ የሚበረክተውን ድርሻ ይወስናል፡፡ በትንንሽ ምድቦች የሚካሄድ ተግባር እና የጥንድ ሥራ ልምምድ አጎልባች ሲሆን በራስ መተማመን ከፍ የሚደረግና የማበረታቻ ምንጭ የመሆን ድርሻ አለው፡ የቡድን ሥራ ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ርእሰ ጉዳይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ እንዲችሉ ምቹ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዴ ተማሪዎቹ በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ሃሳባቸውን መግለጽ ከተለማመዱ በመላው የመማሪያ ክፍሉ ተማሪ ፊት ሃሳባቸውን ለማቅረብ አያፈገፍጉም፤ አያፍሩም፤ አይፈሩም፡ የቡድን ስራ ሃሳባቸውን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን የክፍሉን ትስስር ብሎም ማበረታታት ለማስደግ የሚረዳውን አብሮ የመስራት ልምድ ለማዳበር ይረዳል (Gardner እና Lambert, 2009፤ Ushioda, 2012)፡፡

## 2.5 ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ማበረታቻ ስልቶች

ሁለተኛ ቋንቋ የሚባለው እያንዳንዱ ሰው ከአፍ መፍቻ ቋንቋው ወጪ የሚማረው ቋንቋ ነው፡ ሁለተኛ ቋንቋ በመሆ ውጤታማ ወይም ስኬታማ የመሆን ጽንሰ ሃሳብ አብዛኛውን ጊዜ ከማበረታቻ ጋር ይያያዛል፡፡ ማበረታቻ በአብዛኛው የቋንቋ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ የደረሰበትን ስኬት ወይም ወደኋላ መቅረት ለመግለጽ ይረዳል፡፡ በማበረታቻ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ለልዩ ልዩ ባህርዮቻችንና ድርጊቶቻችን ብርታት የሚሰጡን፣ አቅጣጫ የሚያቁሙ፣ በአጠቃላይ የጥንካሬ፣ የአላማ የመስራት ቆይታ

የሚጎርልን ውስጣዊ ሂደት (internal process) ነው (Gardner እና Lambert, 2009 2009)፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ መማር ጊዜና ተነሳሽነት ይጠይቃል፡፡ አንዴ አንድ ሰው ሁለተኛ ቋንቋ በመማር አንደበተ ርቱእ (fluent) መሆን ከቻለ ማወቁ የሚያስገኛቸው በርካታ ጠቀሜታዎችና እድሎች አሉለት፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ መማር ተግባራዊ፣ አእምሮአዊና ለሰብአና እድገት ጠቀሜታ ካላቸው እንደ ተግባቦታዊ ብቃትና ራስን በትክክል የመግለጽ ችሎታ ካሉ እድሎች እንድንጎዳኝ ያደርገናል (Dörnyei, 2018)፡፡

የማህበራዊ ለውጥ (socio-dynamic) ወቅት በጣም ወቅታዊ የሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ማበረታቻ ጥናቶች የቀረበበት ወቅት ነው፡ ስያሜው እንደሚያመለክተው ዘላቂ የሆነ ማበረታቻ ተኮር ለውጥና የተማሪዎቹ ተራክቦ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ሁነኛ አነቃቂ ሚና እንዳለው (Dörnyei እና Ushioda, 2013) ይጠቁማሉ፡ እንደነዚህ ምሁራን ገለጻ፤ የቋንቋ ትምህርት አቃጆች ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያካትቷቸው የቀለም ትምህርት የማበረታቻ አይነቶችና አላማዎች ወሳኝ ሚና አላቸው፡ ያለንበት ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ለመዳ ማበረታቻዎች በሰስት ስልተ ትውራዎች (approaches) ላይ ይሚኮዛሉ፡

### 2.5.1 ተማሪው ላይ ትኩረት ማድረግ (Person-in-context)

በማቅሚራዊ እና ለውጥ አማጭ ክንዋኔዎች ላይ ትኩረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ስልተ ትውራ መሰረት ተማሪው እንደ ምክንያት እና ውጤት ማስኤ አይወሰደም፡ ከዚህ ይልቅ ተማሪው የሚያየው ተለዋዋጭ ልዩ ግለሰብ (dynamic unique individual) ነው፡ ይህም ማለት፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርቱ ሂደት ላይ ብቻ አጽንኦት ከማድረግ ይልቅ በተማሪው ማህበራዊና ግላዊ ሁኔታዎች ላይ ተገቢውን አጽንኦት በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪው ፍላጎት ጋር የተጎዳኘ በቂና ጠቃሚ ማበረታቻ ማድረግ ያስፈልጋል (Dörnyei እና Ushioda, 2013)፡፡

### 2.5.2 ለሁለተኛ ቋንቋ የሚመጥን ማበረታቻ ማቀድና ማጣገበር

ይህ በDörnyei ተተልሞ በ Dörnyei እና Ushioda (2013) የቀረበ ስልተ ትውራ በሁለተኛ ቋንቋ ትግበራና ማበረታቻ ላይ አጽንኦት የሚያደርግ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው አሉታዊ አማካከትና ስሜት ሳይይዝ በሁለተኛ ቋንቋው ምን ጫኔ ማገር እንዳለበት መማሪያ አዉድንና የማስተማሪያ ስልቶችን ከተጨባጭ ሁኔታዎች በማቀናጀት የሚቀርብ የማበረታቻ ስልት ነው፡

### 2.5.3 ውስብስብ ተለዋጭ ስልት (Complex dynamic system)

ይህ ስልተ ትዉራ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተለዋዋጮች (variables) ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡ እነ ዚህ ተለዋዋጮች በሚባ ተቀናጅተው ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ክፍል በማጠራታቸነ ት እየዋሉና በዘላቂነ ት እየተለዋወጡ ከቀላል ወደ ወስብስብ በማምራት ተማሪዎቹ ከታቀደው ትምህርታዊ ግብ እንዲደርሱ ለማድረግ ያግዛሉ (Dörnyei እና Ushioda, 2013)፡፡

እነ ዚህ ምሁራን እንደጠቆሙት፤ ተማሪዎች በግለሰባዊ ባህርያቸው፣ በትምህርት አቀባበላቸው፣ በማህበራዊ አተያያቸው፣ ወዘተ የተለያዩ እንደሚሆናቸው ማወቅ እነ ዚህ ልዩነ ቶቻቸው በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ወስጥ የማጠረታታት ልምዶቻቸውን ይወስናሉ፡ በመሆኑም በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ወስጥ መምህራን የሚያቀርቧቸው ማጠረታቻዎች በተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ደረጃ፣ ፍላጎትና ሊያከናወኗቸው በሚችሏቸው ተግባራትና ልምምዶች የተቃኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ልምድና የቋንቋ ተግባቦት መሰረታዊ ፍላጎቶች ያገናዘቡ የማጠረታቻ ስልቶችና ብልሃቶችን ማቀድ፣ አሳታፊ በሆነ መልኩ ማጠረታቻዎችን መተግበርና ተማሪዎቹ ለወጥ አማጭ ክንዋኔዎች ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡

## 2.6 ተማሪዎች ሲያነ በና ሲጽፉ እንዴት ይበረታታሉ?

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ማንበብና መጻፍን ማቀናጀት በሁሉም የትምህርት መስኮች የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ያሻሽላሉ፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በሚማሩት ነገር ዙሪያ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ስለሚያስፈልግና ማንበብና መጻፍን ማቀናጀት ይህን ማድረግ ስለሚያስችል ነው (Ambrose, Bridges እና DiPietro, 2010)፡፡ በተነ ቃቃ የተማሪዎች ተሳትፎ ከፍ ያለ የትምህርት ወጤታማነ ት እውን እንደሚሆንና ይህም በበኩሉ የተማሪዎችን ማጠረታታት እንደሚያሳድግ ጥናቶች ያመላክታሉ (Bunn, 2011)፡፡

የማንበብና መጻፍ ተግባራት በአስፈላጊነ ታቸው መጠን በጥንቃቄ መደራጀትና መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡ ንባብን በዘፈቀደ እንዲያካሂዱት ብቻ ማተው በቂ አይደለም፡ ተማሪዎቹ እንዴት ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው አመራር ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመጻፍ ክንዋኔዎች የሚፈለገውን ወጤት እንዲያስገኙ ከተፈለገ በሚባ ታስቦባቸው እንዲሰሩ ሊደረግ ይገባል (Ericsson, Krampe እና Tescher-Romer, 2013)፡፡

በየትኛውም የክፍል ደረጃ ወጤታማ የሆነ የማንበብና መጻፍ ቅንጅት የሚጀምረው ተማሪዎቹ በቀደሙ ክፍል ከቀሰሙት እውቀት፣ ከገበዩት ልምድ እና ከያዙት መረጃ በማነሳትና በመረዳት ነው፡ ሌላው ማንበብና

ሜጻፍን የትምህርቱ ማእከል ለማድረግ የሚረዳ መሰረታዊ ሚና ተማሪዎቹ ስለሚጻፉት ነገር ራሳቸውን እንዲጠይቁና ጊዜ ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡ ይህም ቋንቋውን በመፃፍ ወደፊት ምን ማድረግ ወይም ምን እንደሚፈልጉ ማስገንዘብና ማስወሰንን ያካትታል (Greene, 2012)፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ማንበብና መጻፍ ተማሪዎች የሚኖሩበትን አለም በሚገባ ለማንዘብ የሚረዳቸውና ጠንካራ ትስስር ያለው አእምሮአዊ ሂደት (cognitive processes) በመሆኑ ነው (Syverson, 2016)፡፡

ውጤታማ የንባብ--ጽህፈት ተዛምዶ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ለማዋሃደና አዳዲስ ሚናዎችን ለመለስ ይረዳቸዋል፡፡ ማንበብና መጻፍን ለማሳደግ ሊደረጉ ከሚገባቸው የመሰረታዊ ጥረቶች መካከል፡ -

- ተማሪዎች እንዴት እንደሚያነቡና ለምን እንደሚጽፉ በሚገባ እንዲገነዘቡ ማድረግ፣
- በክሂል ደረጃ ተማሪዎች ስለሚያነቡትና ስለሚጽፉት ነገር ማወቅ ያለባቸውን ነገር ሚዳትና ይህንኑ በሚገባ ማስተማር፣
- ለልምምድ የሚረዱ እድሎችንና ተግባራዊ ክንውኖችን ማቅረብ፣
- ለተማሪዎቹ ቀጣይ ልምምድ የሚያግዙ የማንበብና መጻፍ ክንውኖች ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይጠቀሳሉ (Syverson, 2016)፡፡

## 2.7 ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ በሚረዳ መልኩ ማንበብና መጻፍን ማቀናጀት

ንባብ በተለያየ ሁኔታ ጽህፈትን እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል ልምድ ለማግኘት የሚረዳ፣ ተማሪዎች አሳማኝ በሆነ ስልት ጽሁፍን ለማቀናበር እንዲችሉ አቅጣጫ እና አላማ የሚያመላክት ማገድ ነው፡ በመሆኑም፣ ተማሪዎቹን በተወሰነ መልኩ የሚያታግል ስራ መስጠት ተገቢ ነው፡ ተማሪዎች ከቀረበው ነገር ሊማሩ የሚችሉት ሊሰሩት የሚችሉት ነገር ግን በተወሰነ መልኩ ጥረታቸውን በሚጠይቅ ተግባር ሲሳተፉ ነው (Bunn, 2011)፡፡

ለተማሪዎቹ በቂ የማንበብና የመጻፍ የልምምድ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው፡ ተማሪዎቹ ወደቤት ተመልሰው እንዲያነቡና እንዲጽፉ ከማድረግ ይልቅ የመሻለው የመፃፍ ማስተማሩ ሂደት በሚካሄድበት በክፍል ውስጥ በቂ ጊዜ በመስጠት ማለማመድ ተገቢ ነው (Greene, 2012)፡፡ ጥቂት መምህራን የመሚያ ክፍሉን ክፍለ ጊዜ ለንባብና ጽህፈት ማዋል አይፈልጉም፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያትም የክፍል ውስጥ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለእንደነዚህ አይነት ተግባራት የሚሰጥ ከሆነ ሚሃ ትምህርቱን በታቀደለት ጊዜ ለመሸፈን ያስቸግራል ከሚል ስጋት ነው፡ ነገር ግን በመሚያ ክፍል ውስጥ የማንበብና የመጻፍ ተግባራትን አቀናጅቶ ማቅረብ ለተማሪዎቹ ጥሩ የልምምድ ተጋልጦ መፍጠሪያ ማድረክ ነው (Ericsson, Krampe እና Tescher-Romer, 2013)፡፡

የተማሪዎቹን የማበብና የመጻፍ ተግባራት እየገመገሙ መቀጠል ሌላው አስፈላጊ የማበረታቻ ምንጭ ነው፡ ሁሉንም የጽህፈት ክንውኖች ማገምገም ወይም ማስቀመጥ አስፈላጊ ባይሆንም፣ ለተማሪዎቹ የማበብና የመጻፍ ልምምድ እድገቶች ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው (Ambrose, Bridges እና DiPietro, 2010)፡፡ የተማሪዎቹን ልዩ ልዩ ልምምዶች በአቻ እርማት ዘዴ በማስደገፍ ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠት መምህሩ ለግምገማ የሚጠፋውን ጊዜና የስራ ጫና ይቀንሳል (Greene, 2012)፡፡

## 2.7.1 ንባብን ማበረታታት

የንባብ ማበረታቻ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት፤ መምህራን ተማሪዎቻቸው መረጃ ለማግኘት ሲሉ በማበብ እንዲበረታቱ ከፍ ያለ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡ ከዚህም ጋር የተማሪዎች የማበብ ፍላጎት ጥራት ላለው ትምህርት እንደ አንድ ግብአት የሚቆጠር ነው፡ ከተለያየ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ የመጡ የተለያየ አንብቦ የሚረዳት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች በተቀራራቢ ሁኔታ በማበብ ክሂል ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲቻል የማበረታቻ ስልቶችን መተግበር አስፈላጊ ነው (Chatzisarantis እና Hagger, 2013)፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው በማበብ እንዲያበረታቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ግፊቶችን ማድረግ የክፍሉ ተማሪዎች ተቀራራቢ የትምህርት ውጤታማነት ይዘው እንዲገኙ ለማድረግ ይረዳል (Creswell እና Plano, 2017)፡፡

ነጻ እና በቁጥጥር የሚካሄድ የንባብ ማበረታቻ ስልቶች አሉ፡ ተማሪዎች በበርካታ ምክንያቶች በማበብ እንደሚበረታቱ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡ ተማሪዎች ስለራሳቸው መማር ራሳቸው ሃላፊነት መውሰድን በሚያሳይት የቀረቡ ንድፈ ሃሳቦች እንደሚያረጋግጡት የነጻ ንባብ ማበረታቻ ተማሪዎቹ ማበብን የመምረጥ የሚሰጡት ለራሳቸው ደስታ ስለሚሰጣቸው ነው፡ ይህም ከፍላጎትና ተዝናኖት ጋር የተያያዘ ነው፡ በቁጥጥር የሚካሄድ ንባብ በሌላ በኩል የማበብ ግፊቱ የሚመጣው ከውጪያዊ ሃይል ሆኖ አንድን ነገር በማስናወን ለማሸለም ወይም አውቆ ማግኘት ግድ በሚልበት ጊዜ ነው (Daniels እና Steres, 2011)፡፡

## 2.7.2 ጽህፈትን ማበረታታት

አጠቃላይ በሆነ መልኩ ጽህፈት እና በተለይ ደግሞ ድርሰት ለሁለተኛ **ቋንቋ** ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ አዳጋችነት የሚታይበት ነው፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎቹ በአንድ በኩል የሁለተኛ **ቋንቋውን** ቃላት አጠቃቀም እምብዛም ባለማወቃቸው ወይም ባለሚረዳታቸው የተነሳ ሲሆን (Bataineh 2015)፤ **በሌላ በኩል ደግሞ የድርሰትን የአጻጻፍ መርሆዎች ጠብቆ፣ ልዩ ልዩ የድርሰት ክፍሎችን**

ተገንዝቦ ጥሩ ድርሰት መጻፍ አብዛኛውን ጊዜ ለብዙ ተማሪዎች አዳጋችና የሚፈሩት ተግባር በመሆኑ ነው (Cedar 2014)፡፡ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ መጻፍ እንዲችሉ በርከት ያሉ ቃላትን ማወቅ፣ ቃላቱን በተፈላጊው ሁኔታ በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ትርጉም ባለው መንገድ መገልገል፣ በአረፍተነገሮች መካከል ተገቢ ውህደቶችን በመፍጠር አንቀጾችን መገንባት እና በአንቀጾች ጥምረት ድርሰት ማቅረብ በጽህፈት መርሆዎች ላይ በሰፊው የሚመረኮዝና ችሎታንም የሚፈትን ተግባር በመሆኑ ነው (Arter እና Spandel 2010)፡፡

ጽህፈት በሁለተኛ ቋንቋ ይቅርና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ደረጃም ቢሆን ከባድ ሂደት ነው፡ በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት ውስብስብነት የተሞላበት ነው (Bataineh 2015፣ Cedar 2014)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ አብዛኛውን ጊዜ በሁሉም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች አዳጋችነት ያለበት ሲሆን፣ በተለይ ደርሰት የመጻፍ ሂደት አረፍተ ነገርና አንቀጽ ከመጻፍ ሰፊ የጽህፈት ግብአቶችንና ሁነኛ ልምድ የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ተማሪዎችን በእጅጉ የሚያስጨንቃቸው መሆኑን የቋንቋ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ (Arter እና Spandel 2010)፡፡

ተማሪዎችን በጥሩ ሁኔታ የተገነባ፣ ጽዱና ስህተት የሚያገኝበት ጽሁፍ እንዲያቀርቡ ማድረግ አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ መምህራን ምኞት ቢሆንም፣ ተማሪዎቻቸው በአብዛኛው ይህን ለማድረግ ፍርሃት ይይዛቸዋል፡፡ Richards እና Renandya (2012፣ 203) እንዳቀረቡት፤ ‹‹በእርግጥም የጽህፈት ክሂል ተማሪዎቹን ማስጨበጥ ከሁሉም ክሂሎች ይልቅ አዳጋችነት ጎልቶ የሚታይበት ክሂል ነው፡፡ አዳጋችነቱም ሃሳብ አመንጭቶና ተገቢ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ በማቅረብ ላይ ብቻ ያረፈ አይደለም፡፡ ቃላትን በማቀነባበር፣ በማዋሃድና በተገቢ መንገድ ስርአተ-ነጥቦችን በመጠቀም ተነባቢ (legible) ጽሁፍ ማቅረብ ስለሚሳናቸው ጭምር ነው፡፡››

ጽህፈት በርከት ያሉ ተፈላጊ ጉዳዮችን ማሰብን ያካትታል፡፡ የአጻጻፍ ስልት መምረጥንም ይጠይቃል፡፡ ይዘት፣ መዋቅር፣ አደረጃጀት እና ‹‹የዝቅተኛ ክሂል አካላት›› (“lower level skills”) የሆኑትን እንደ ስርአተ‹ነጥብ፣ የቃላት ምርጫ፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች በተገቢ መንገድ የመጠቀም አስፈላጊነት በነ Richards እና Renandya (2012) የተጠቆሙ ትኩረቶች ናቸው፡፡ ከዚህም ጋር የጽህፈት ክሂል ተከታታይ በሆነ መልኩ ልምምድ ማድረግና እየጻፉ መማርን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ሃሳቦችን በማዋሃድና የሚያጋጥሟቸውን የመጻፍ ችግሮች እያቃለሉ ወደፊት በመጓዝ ሂደት ተማሪዎቹ ጥንድ መስተጋብሮችን ያከናውናሉ፤ ቀጣይነት ባለው መልኩ የጽህፈት እውቀትን ማካበትና

ቀጣይነት ባለው መልኩ የጽሁፍ ውጤቶችን ማፍራት (Bereiter እና Scardamalia 2007፣ 12)፡፡

በእርግጥ በትምህርት ቤት የሚካሄድ የጽህፈት ክንውን ሁነኛ ጥረት እና ተከታታይ የድረሰት መጻፍ ሙከራ ማድረግን ግድ ይላል፡፡ ከተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አንጻር ሲገናዘብ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ሂደት በቋንቋው ቃላት በተገቢ ሁኔታ የመጠቀም ብቃትና የጽህፈት ስልቶችን፣ ቴክኒኮችንና ክሂሎችን በትክክል የመጠቀም ችሎታ እንዲሁም ስህተት አልባ (error-free) ጽሁፍ የማቅረብ ጥንቃቄን ይጠይቃል (Richards እና Renandya 2012)፡፡

ይሁን እንጂ በርከት ያሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ከብዷቸው ያገኙታል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስጽፉ ተማሪዎቹ ስህተት መፈጸማቸው እንደማይቀር ከመጠበቅ ጋር በተቻለ መጠን ለጽሁፉ ይዘትና አቀራረብ ትኩረት በመስጠትና የሚገጥሟቸውን ስህተቶች ነቅሰው እያወጡ በየጊዜው ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂልን እንዲማሩና የተሻለ ልምድ እንዲገበዩ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡

Ying (2017) እንደሚገልጹት፤ ጥሩ የጽህፈት ውጤት በርካታ ነገሮችን ይጠይቃል፡፡ ሃሳቦችን የማደራጀት እና መረጃዎችን የማቀነባበር ከፍ ያለ ችሎታ፣ ጽሁፉ ያዘለው መልእክት እንዳይዛባ ወይም የተለየ ትርጉም እንዳያዝል ሃሳብን በትክክል የማቅረብ ጥንቃቄ፣ ሰዋሰዋዊ ዘዴዎችን በጥልቀትና በአግባቡ በስራ ላይ በማዋል ጽሁፉ ያተኮረባቸውን ጉዳዮች በአጽንኦትና በትኩረት የማሳየት ዝግጁነት እና ቃላትን በአግባቡ የመጠቀም፣ አረፍተነገሮችን በስርአት የመደርደር ችሎታዎችን ይጠይቃል ብለዋል፡፡

Rivers (2008:243) እንዳቀረቡት፤ ‹‹የጽህፈት ክሂል ሌሎች በርከት ያሉ ንኡሳን ክሂሎችን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋልን ይጠይቃል፡፡ እነዚህም በሚጻፍበት ጉዳይ ላይ አጠቃላይ እውቀት መያዝ እና ሃሳብን በተቀነባበረ መንገድ ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን ሳያፋልሱ ወደ ጽሁፍ የመለወጥ ችሎታ ናቸው፡፡›› Rivers አክለው እንዳቀረቡት ጥቆማ፤ ማንኛውም በትምህርት አለም የሚገኝ ጸሐፊ አራት አስፈላጊ መሰረታዊ ሁኔታዎችን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡ እነዚህም (1) የቋንቋውን የአጻጻፍ ስርአት መማር ወይም መልመድ፣ (2) በቋንቋው ህግጋት መሰረት ፊደላትን መጻፍ፣ (3) ለአንባቢ አረዳድ በሚመጥን መልኩ

የቋንቋውን መዋቅር ጠብቆ ጽሁፍ ማቅረብ መቻል እና (4) የቃላትንና የሃረጋትን ስርአታዊ ቅንብርና የግንኙነት ስልት መርጦ በጽሁፉ ማሳየት የሚፈልገውን ጉዳይ ማቅረብ ናቸው ብለዋል፡፡

## 2.8 ንባብና ጽህፈትን የማበረታቻ ብልሃቶች

### 2.8.1 አዎንታዊ የሆነ የጽህፈት፣ የንባብና የመማሪያ ክፍል ደባብ መፍጠር

እንደ Freeman (2010) **ገለጻ**፣ ተቀባይነት ባለው መልኩ አዋጭ የሆኑ የጽህፈት ልምዶች የሚለዩት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ነው፡ መምህራን በክፍል ውስጥ ጽህፈትን ሲያስተምሩ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እንዳሉም ይታወቃል፡፡ ይሁንና መምህራን በጽህፈት ክፍል ውስጥ አዎንታዊ የሆነ የመጻፊያ ደባብ (environment) መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡ የጽህፈት ክፍሉ ደባብ አዎንታዊ ግፊትን የሚፈጥር፣ ተማሪውን በጽህፈቱ ተግባር የሚረዳ፣ የሚገጥሟቸውን ችግሮች የሚያቃልል፣ በይበልጥ እንዲያነቡና እንዲያስቡ የሚያበረታታ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎቹ ጥሩ የጽህፈት ውጤቶችን ባቀረቡ ጊዜም ስራዎቻቸውን መደነቅ፣ ማበረታታት፣ መሸለምና በማህበረሰቡ ፊት እንዲቀርብ ማድረግ አዎንታዊ ግፊት ይፈጥርላቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ማድረግ ያለባቸው ጉዳዮች አሉ፡

*ሀ) በክፍል ውስጥ ግፊት መፍጠር*

በርግጥ ሁሉም ተማሪዎች የተዋጣላቸው ጸሃፊ ለመሆን እንደማይችሉ የታወቀ ቢሆንም፣ መማሪያ ክፍሉ ተማሪዎቹ በጽህፈት ተግባር እንዲበረታቱ አዎንታዊ ግፊት የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ ያህል የመማሪያ ክፍሉ ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ደረጃ እርስ በርስ እንዲወያዩና በመተባበር እንዲሰሩ፣ ለመጻፍ የሚያገለግሉዋቸውን መሳሪያዎች እንዲዋዋሱ የተመቻቸ መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላም በኩል የጽህፈት ክፍሉ የመጻፍ ሂደትን የሚያግዝና የጽህፈት ተግባርን የሚያበረታታ መሆን ይኖርበታል (Freeman (2010)

*ለ) በተማሪዎቹ መካከል የመተባበርና የመረዳዳት ስሜትን ማስፈን*

Arter **እና** Spandel (2010) **እንደገለጹት**፣ ለአዎንታዊ የጽህፈት ደባብ መኖር አንዱ አስፈላጊ ሁኔታ ተማሪዎቹን ማክበርና እርስ በርሳቸውም እየተሳሰቡ እና እየተደጋገፉ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡ ማክበር ሲባልም የተማሪዎቹን ስሜት፣ ባህላዊ ዳራ፣ ፍላጎታቸውን፣ ማድረግ የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች የሚመለከት ሲሆን መምህሩ እነዚህን ጉዳዮች በተለያዩ መንገዶች በግልጽነት ማሳየት መቻል አለበት፡፡ መምህሩ እንደግልጽነቱ ከጽህፈት ክንዋኔ ጋር በተያያዘ መልኩ እርስ በርስ መማማርን፣ የሚጨነቁበትን ጉዳይ እንዲነጋገሩ ማድረግን፣ ባህላዊ ልዩነቶችን ማክበርን፣ ሃሳቦቻቸውን ማከባከብን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

*ሐ) መምህሩ እንደ ጸሃፊ ሚናርግ ያለበት*

በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ራሳቸው የሚጽፉ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ጽህፈት ለማስማማድ ቅርብ ናቸው፡ መምህራን በዚህ ሚናኩ ራሳቸውን፣ ተማሪዎቻቸውንና የጽህፈት ተግባርን የሚያከብሩና በስርአት የሚያስተባብሩ እንዲሁም የጽህፈት ተግባሩ የሚፈልጋቸውን ግብአቶችና የሚጠይቃቸውን ትኩረቶች በተሻለ እይታ የሚያጤኑና የጽህፈት ተግባራትን በአላማው መሰረት በብልሃት የሚተገብሩ ይሆናሉ (Bachman 2011)፡፡

*መ) የሚጠበቁ ውጤቶች*

በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ከጽህፈት ሂደት የሚጠበቁ ውጤቶች አሉ፡ እነዚህ ውጤቶች በበቂ ክንዋኔዎች የተደገፉ፣ ስሜት በሚሰጡ ዝርዝር ተግባራዊ ሂደቶች የታጀቡ ወይም የተገነቡ መሆን አለባቸው፡ ማንኛውም የጽህፈት ክንዋኔ ውሱን (rigid) አይደለም፡ በርካታ መምህራን በጽህፈት ተግባር ውስጥ ከተማሪዎቻቸው የሚጠብቁት ውጤት (ግብ) አለ፡፡ ለዚህ ይረዳቸው ዘንድ ተማሪዎቹ ግራ ሳይጋቡ የተሰጣቸውን ስራ በመተባበር እንዲያከናውኑ ጠንከር ያለ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ተሳትፎዎቻቸውንም በማያያም ያበረታታሉ (Arter **እና** Spandel 2010)፡፡

### 2.8.2 **ጽህፈትን ማቀናጀት**

መምህራን ተማሪዎቹ በጽህፈት እንዲበረታቱ እንደ ተማሪዎቹ ሁኔታ እና እንደ ትምህርቱ ግብ ተለዋዋጭ አሰራር ላይ መመርኮዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ስልታዊ እና ብዙ ቁምነገሮችን የሚያሰላስሉ መሆንም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የጽህፈት ተግባርን ለማቀናጀት ማቀድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የሚቀድመው ጉዳይ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ልምድ፣ ፍላጎት እና ከአጠቃላይ መማሪያ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎቹ ወደፊት ራሳቸውን ችለው መጻፍ እንዲችሉ የሚያበረታታ የመማሪያ ክፍል መፍጠርና የተማሪዎቹን የጽህፈት ክንዋኔ ማስተባበር ያስፈልጋል (Bachman 2011)፡፡

### 2.8.3 **ጽህፈትን ለተማሪዎቹ በሚስማማ ሁኔታ ማደራጀት**

እንደ Ackner (2011) **ገለጻ**፣ ይህ መሰረታዊ መማሪያ መምህሩ ተማሪዎቹ ለጽህፈት ክንዋኔ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሊደረግ የሚገባውን ውይይት ይመለከታል፡፡ ይሁንና የጽህፈቱ ክንዋኔ ከሚካሄድበት ክፍለ ጊዜ አስቀድሞ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው፡ የጽህፈት ክንዋኔውን እንደ ቤት ስራ መስጠትም ይቻላል፡፡ መምህራኑ አስቀድሞ እንደተገለጸው ተማሪዎቹ ስለሚያከናውኑት የጽህፈት ተግባር በሚገባ ማሰላሰል

ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎቹም በሚከናወኑት የጽህፈት ተግባር ሊደርሱበት ስለሚገባ ግብ ማቀድና ይህንኑ ይደርሱበታል ተብሎ የሚታሰብ ግብ ለማሳካት የሚረዳ ክንዋኔ ሚቋቋጀት ያስፈልጋል፡፡

ሀ) *የጽህፈት ዎርክ ሾፕ*

ጽህፈትን በተቃና ሁኔታ ለማስተማር በርካታ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በጽህፈት ‹ዎርክ ሾፕ› እንዲሳተፉ በማድረግ ያስተምራሉ፡፡ ለዚህም እንዲረዳቸው የተለየ የመጻፊያ ክፍል (studio approach) ይፈጥራሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የሚጽፉቸውንም ሆነ የሚጽፉባቸውን ነገሮች በማክተት ተማሪዎች በጽህፈት ተግባር እንዲነቃቁና እንዲበረታቱ ለማድረግ ይረዳል (Bachman 2011)፡፡

እንደ (Bachman 2011) ገለጻ፤ የጽህፈት ዎርክ ሾፕ ሊያሟላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ፡፡ ከጥቂ ጎደል፡- በእለቱ ስለሚጻፉበት ርእሰ ጉዳይ የተብራራ ገለጻና የሂደት ዝርዝር፣ ስለሚከናወኑት ሂደታዊ የጽህፈት ተግባር እቅድ፣ ድረፍት፣ መከለስ፣ ኤዲት ማድረግና የአቻ ምልከታ፣ ጽሁፉን የማበልጸና አስተያየት መስጫ ጊዜ፣ ተማሪዎቹ በጻፉት ጉዳይ ላይ ግብረ-መልስ የመቀበያ ጊዜ፣ በሚጽፉት ጉዳይ ላይ ምን አይነት ግብአቶችን መጠቀም እንዳለባቸው ግልጽ በሆነ መንገድ መመራት አለባቸው፡

ለ) *የጸሃፊ ማስታወሻ ደብተር*

ሌላው የጽህፈት ተግባርን ለማለማመድ የሚረዳው ጠቃሚ የጽህፈት መሳሪያ የጸሃፊው ማስታወሻ ደብተር ነው፡ ይህ የጽህፈት መሳሪያ በስርአት የተደራጀና በጽህፈት ክንዋኔው ዙሪያ የመምህሩንና የተማሪውን ግንኙነትና ግብረ-መልስ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል (Bachman 2011)፡፡

*ሐ) ተገቢነት ያለው የጽህፈት ስልተ-ትወራ (approach)*

Arter **እና** Spandel (2010) **እንደሚገልጹት**፤ የጽህፈት ተግባርን ለማደራጀት አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ተገቢነት ያለው የጽህፈት ስልተ-ትወራ መምረጥ ነው፡ መምህራን የጽህፈት ልምዳቸውንና የማስተማር ብቃታቸውን መሰረት በማድረግ እንዲሁም የተማሪዎቻቸውን ችሎታና ብቃት እግምት ውስጥ በማስገባት ሙዋዊ በሆነ መንገድ እንዲጻፍበት ከተወሰነው ጉዳይ ጋር በሚጣጣም መልኩ ስልተ-ትወራ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡ መምህሩ ለምሳሌ ብዙ አይነት (multigenre) ስልተ-ትወራን ወይም በስነጽሁፍ አደረጃጀት የሚዋድ ስልት መርጠውና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለተማሪዎቹ ናሙና ሊሆን የሚችል ጽሁፍ አቅርበው የጽህፈት ክፍሉን ቢመሩ ይመረጣል፡፡

የተለያዩ የጽህፈት ስልቶች አሉ፡

- ሞሮሜ የአጻጻፍ ስልት (Inquiry-based writing)
- በታዋቂ ብዙሃን ማናኛ ጥናት የታገዘ አጻጻፍ (Writing based on study of popular media)
- በጭብጥ ላይ የተመሰረተ አጻጻፍ (Writing relevant to a theme)
- በትረካ፣ በገለጻ፣ ወዘተ ዙሪያ ልምድ ለማብየት የሚረዳ አጻጻፍ (Writing to gain experience with selected genres)
- በፕሮጀክት ላይ የተመሰረተ አጻጻፍ (Writing relevant to a project)
- በማሰብ ሂደት ላይ የተገነባ አጻጻፍ (Writing based on thinking processes)
- በተማሪው ርእስ ምርጫላይ የተመሰረተ አጻጻፍ (Student choice of topic)

ሲሉ Arter እና Spandel (2010) ይገልጻሉ፡፡

### 2.8.4 የንባብ ክንዋኔን ለጽህፈት ማጎሻ ማድረግ

በሰፊው እንደሚታወቀው በማንበብ ልምድ ማዳገዝና ደጋግሞ ደጋግሞ ማንበብ የተሻለ የጽህፈት ስራ ለማቅረብ የሚያስችል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡ ተማሪዎች በሚያነበበት ጊዜ ሁሉ የተለያዩ ጸሃፊዎች ጽሁፎቻቸውን ለማቅረብ የተከተሉዋቸውን የተለያዩ ስልቶች የመቅሰም እድል ያገኛሉ (Bachman 2011)፡፡

የጽህፈት ተግባር ከሚደራጀት አንጻር መምህራን ማስተዋል የሚገባቸው አንዱ ጉዳይ በበቂ ንባብ የተደገፉ ተማሪዎች የቱን ያህል የሚያዘጋጁትን የጽህፈት ስራ በጥሩ ሁኔታ ለሚደራጀትና ወደፊትም የጽህፈት ክሂል ብቃት እንዲቀዳጁ እንደሚያደርጋቸው ነው፡ በተለይ የንባብ ግብኣቶቹ ተማሪዎቹ እንዲጽፉባቸው ከሚያሰቡ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት እንዲኖራቸው ማድረጉ እንደ ሞዴል እንዲያገለግሏቸው ለማድረግ አጋዥ ነው፡ ብዙህ የሆነ እይታ ይፈነጥቅላቸዋል (Arter እና Spandel 2010)፡፡

Bachman (2011) እንዳቀረቡት፣ ማንበብና ባነበቡዋቸው ጉዳዮች ዙሪያ በቂ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ ለጽህፈት ክንዋኔ አበረታች ልምድ ነው፡ አንብበው በሚወያዩባቸው የተጻፉ ነገሮች ውስጥ የተለያዩ የጽሁፍ አቀራረቦችን ይቃኛሉ፡ ለአጻጻፋቸው የሚረዱዋቸው ጠቃሚ ስልቶችና አካሄዶች በንባብ ግብኣቶች ውስጥ ሊያገኙ እንደሚችሉም ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን ወደ ጽህፈት ክንዋኔ እንዲገቡ ከማድረግ በፊት በንባብ ማዳገዝና በተነባበው ነገር አቀራረብ ዙሪያ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ በሚጽፉበት ጉዳይ ላይ ፈር እንደሚያዝ የሚቆጠር ነው፡

### 2.8.5 ደጋግመው በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች እንዲጽፉ ማበረታታት

ደጋግሞ መጻፍ የጽህፈት ችሎታን በልምምድ ለማዳበር ዋንኛው መንገድ ነው፡፡ Ackner (2011) እንደሚሉት፤ መምህራን ከሚሃ-ትምህርቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ የተለያዩ የጽህፈት አይነቶችን ባካተተ ሁኔታ ለተማሪዎቻቸው የጽህፈት ክንዋኔዎችን መቅረብና በጽህፈት ተግባር ዘላቂነት ባለው መንገድ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ - በጋዜጣ ላይ የቀረቡ ጽሁፎች ላይ ምላሽ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ ፈጣን የጽሁፍ ክንዋኔ እንዲያካሂዱ ማድረግ፣ በእረፍት ጊዜያቸው ምን እንዳደረጉ፣ በአል እንዴት እንዳሳለፉ፣ የተወሰነ ክስተት በእነሱ እይታ ምን እንደሚመስል፣ ወዘተ በርከት ያሉ ርእሰ ጉዳዮችን በማንሳት ለደረጃቸውና ለግንዛቤያቸው የተመቹ ጽሁፎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችላሉ፡ ትልቁ ቁምነገር የጽህፈቱ አላማ ነው፡ አላማው ደግሞ ከሚሃ-ትምህርቱ ጋር መጣጣሙ ሚጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 2.8.6 እርስበርስ የሚዳዳበትን እድል ማመቻቸት

ይህ የእርስ በርስ መደጋገፍ ክንዋኔ ተማሪዎቹ ወደፊት በሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳብ ለሃሳብ ማለዋወጥን፣ ልምድ ማጋራትን፣ ሚዳዳትን እንዲሁም በጻፉት ጉዳይ ዙሪያ ውይይት ማካሄድን ሁሉ ያካትታል፡፡ መምህሩ ቅደም ተከተላዊነት ባለው መንገድ እርስበርስ የሚደጋገፉበትንና ለየብቻቸው የሚሰሩባቸውን ጊዜያት ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ዋንኛው የመጻፍ ሂደት እያንዳንዱ ተማሪ በግል የሚያከናውነው ተግባር ተደርጎ መቀናጀት ይኖርበታል፡፡ በጋራ የሚያከናውኑዋቸው ተግባራት በሚከተሉት ስልቶች መታጀብ ይኖርባቸዋል (Bachman 2011)፡፡ አክለውም፤ ተማሪዎቹ በጋራ ለመስራት እንዲያስችላቸው አደርጎ ክፍሉን ማመቻቸት፣ የጋራ ተግባሩ የሚከናወንበት አዋጪ ስልት ዙሪያ እንዲወያዩ ማድረግ፣ የሚሰጡዋ የጽህፈት ክንዋኔ እንዴት ቢያከናውኑት እንደሚሻላቸው ማሳየት፣ ጽህፈት ተግባሩ ማከናወኛ የሚዳቸው መመሪያ (checklist) መቅረብ፣ በጻፉት የመጀመሪያ ንደፍ ላይ እርስ በርስ እንዲወያዩ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ እርስ በርስ የሚደጋገፉባቸውን ትንንሽ ቡድኖች መመስረት የመሳሰሉት ክንዋኔዎች ለጽህፈት ክሂል መዳበር ምቹ ሁኔታዎች መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

### 2.9 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናታዊ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች አሉ፡ ከውጪ ጥናቶች መካከል፤ Masgoret እና Gardner (2013) ‹‹Attitudes, Motivation, and Second Language Learning›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ተቃኝቷል፡፡ ይህ ጥናት ተንትኖ ያቀረበው በሁለተኛ ቋንቋና በአመላካከትና ማበረታቻ መካከል ያሉ ተለዋዋጮችን ከማህበራዊ ትምህርታዊ ሞዴል አንጻር በማያያዝ ነው፡ በዚህ ጥናት ማበረታቻ ከሁለተኛ ቋንቋና ከአመላካከት ጋር ያለውን ተዛምዶ በፈተና መንገድ ለሚጋገጥ የተሞከረ ሲሆን በግኝቱም የተማሪዎቹ እድሜ በማህበረሰቡ ውስጥ ታላሚው ቋንቋ ያለው ጠቀሜታ በማበረታቻ ስልቱ ላይ ተጽእኖ

እንዳደረጉ ተመልክቷል፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ ቀደምት ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሚያደርገው ሁለቱም ጥናቶች በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ማጠረታቻ ዙሪያ ያተኮሩ በመሆናቸው ሲሆን የቀደመው ጥናት በዉጪ ቋንቋ ያተኮረና የተጠኚዎቹን አማካከት ያካተተ በመሆኑ፣ በተጠኚዎቹ ባህርያትና በሚጃ ማሰብሰቢያ ስልት (የቀደመው ጥናት በፈተና ሚጃ ማሰብሰቢያ ላይ ያተኮረ በመሆኑ) ይለያያሉ፡፡ ይህ ጥናት በተማሪዎቹ የማንበብ ሟፍ ክሂሎች የተወሰነ፣ የተማሪዎች የአማካከት ጉዳዮችን ለይቶ የሚያጠና እና ፈተናን እንደ ሚጃ ማሰብሰቢያነት የሚጠቀም በመሆኑ ከቀደመው ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

Clément እና Kimberly (2014) ‹‹Motivation, Self-confidence, and Group Cohesion in the Foreign Language Classroom in Oman, English Language Teaching›› በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናት ሌላው በአጥኚዋ የተዳሰሰ ጥናት ነው፡ ይህ ጥናት በማህበራዊ ስነ ልቦናዊ ሞዴል እና በአንድ አይነት ቋንቋ ተናጋሪ ሃንጋሪያውያን ማህበረሰብ ላይ በማትኮር በቡዳፔስት በሚኙ 301 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በመጠይቅ የሚጃ ማሰብሰቢያ በመደገፍ ጥናታቸዉን አቅርበዋል፡፡ በጥናታቸው አማካከት፣ ቁጡት (anxiety) እና የማጠረታቻ ስልቶች እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ማስተማር የክፍል ዉስጥ ደባብ ያሉባቸዉን ችግሮች ዳስሰው አቅርበዋል፡፡ በግኝታቸውም አማካከት፣ በራስ መተማመን እና ብቃት (proficiency) በክፍል ዉስጥ የሚጠቅን የቋንቋ ማስህራን የማጠረታቻ ስልቶች እንደሚወስኑ አጥንተዋል፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ የቀደመ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆነ ው ሁለቱም በማጠረታቻ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው፣ ሁለቱም በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ በማትኮራቸዉና የጽሁፍ መጠይቅን እንደ ሚጃ ምንጭ በማ ልገላቸው በከፊል የሚያመሳስላቸው ሲሆን፤ የሚያዩት ደግሞ የቀደመው ጥናት በዉጪ ሀገር የተማሪዎች ባህርያት ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ይህ ጥናት ከመጠይቅ በተጨማሪ ሌሎች የሚጃ ማሰብሰቢያ ስልቶችን የሚጠቀም በመሆኑና የተማሪዎችን አማካከት፣ ቁጣ እና ብቃት በተናጠል የሚያመለከት በመሆኑ ይለያያሉ፡

ከሃገር ዉስጥ ይህ ጥናት በሚያተኩርበት አካባቢ (በጅማ ዞን) የተሰራ በዘዉዓ (2014) ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ‹‹A Comparative Study of Students' Performance and motivation In EFL Paragraph Writing: Grade 11 In Jimma And Eldan Preparatory Schools›› **በሚል ርእስ የቀረበ** ጥናት ተቃኝቷል፡፡ ዘዉዓ በአነጻጻሪ የአጠናን ስልት በመደገፍ በአንድ የመንግስትና በአንድ የግል ትምህርት ቤቶች ላይ በማትኮር የአንቀጽ ጽህፈትን ከማጠረታቻ ስልቶች ጋር በማያያዝ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎቹ ዘንድ ያለዉን የጽህፈት ማጠረታቻ አነጻጽሮ አቅርቧል፡፡ የዘዉዓ ጥናት ምንም እንኳ ጽህፈትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ከማጠረታቻ አንጻር የቃኘ በመሆኑና በሁለተኛ **ቋንቋ** ማስተማር መማር ሂደት የተቃኘ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፣ ጥናቱ የቀረበው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል ነው፡ ይህ ጥናት በአማርኛ **ቋንቋ** ንባብና ጽህፈትን ማስተማር ማስህራን በሚያደርጓቸው ማጠረታቻዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑና በሚከተለው የአጠናን ዘዴ ከዘዉዓ ጥናት

ይለያል፡፡ በዚሁ መቅረት የዘወዓ ጥናት ተሜዎቹ በሚፅሩት ስራ ላይ ያተኮረና ፈተናን የሚጀ ማቅብሰቢያ አደርጎ የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ማህራኑ በሚከናወኑት የክፍል ውስጥ የማበረታቻ ተግባር ላይ በማትኮሩ ከቀደመው ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

እንዳለ (2015)፣ ‹‹English Language Teachers' Motivational Strategies In Helping Students Develop Writing Skills: The Case Of Shebe & Seka High Schools›› በሚል ርእስ ያቀረበው ቀደምት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ባለው ተዛምዶ ተቃኝቷል፡፡ የእንዳለ ጥናት በሰቃ እና በሸቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂልን እንዲያጎለብቱ በሚደረገው ማበረታቻ ላይ ያተኮረ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን፣ እንዳለ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍልና በጽህፈት ክሂል ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋና በንባብና ጽህፈት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ብሎም በጥናቱ አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

ልዑልሰገድ (2007) ‹‹በወላይትኛና በሲዳምኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ የንባብ ክሂል ለማስተማር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና›› በሚል ርእስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ተቃኝቷል፡፡ የልኡል ሰገድ ቀደምት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል በሚደረጉ ማበረታቻዎች ላይና በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ባህሪያት ላይ በማትኮራቸው ነው፡፡ የልኡል ሰገድ ጥናት የቀረበው በንባብ ክሂል ማስተማሪያ ክፍል በሚደረጉ ማበረታቻዎች ላይ በማትኮር በመሆኑና ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ንባብና ጽህፈት በማትኮሩ እንዲሁም በጥናት አካባቢ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ፡፡

አማረ (2006)፣ ‹‹አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመጻፍ የሚያጋጥሟቸው ችግሮችና የማበረታቻ ስልቶች›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተዛምዶ ተቃኝቷል፡፡ የአማረ ትኩረት ምንም እንኳን በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል ላይ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም በዋንኛነት በተማሪዎቹ ችግሮች ላይ ያተኮረ መሆኑ እንዲሁም በተማሪዎቹ ባህሪና በጥናት አካባቢ ይለያያሉ፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል በአጥኚዋ የተቃኙት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስሏቸውና የሚለያዩዋቸው ባህርያት እንዳሉ መመልከት ተችሏል፡፡ የዘውግ እና

የእንዳለ ጥናቶች በጽህፈት ክሂል ትግበራ ያተኮሩ ቢሆኑም የቀረቡት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል የማበረታቻ አተገባበር ላይ ነው፡፡ የዘውገ ጥናት በተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበልና የጽህፈት ክንዋኔ ላይ ያተኮረ ሲሆን በመረጃ አሰባሰብ የተከተለው ስልት ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ይህን ጥናት ከዘውገ የተለየ የሚያደርገው ዋንኛ ባህሪው ከተማሪዎቹ ተግባራትና ክንዋኔዎች በበለጠ ለመምህራኑ የማስተማሪያ ስልቶች ተገቢነት ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ የእንዳለ ጥናት ለዚህ ጥናት የበለጠ ቅርብ የሚያደርገው በማስተማሪያ ስልትና በጽህፈት ክሂል ማበረታቻ ግንኙነት የተቃኘ መሆኑ ነው፡፡ የእንዳለ ጥናት በሚያተኩርበት ቋንቋና በጥናት አካባቢ ከዘህ ጥናት ይለያል፡፡ የልዑልሰገድ እና የአማረ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱት በተለያየ ሁኔታ ነው፡፡ ልኡል ሰገድ ስለቋንቋ ማስተማሪያ ስልት ማጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎ ቢሆንም በምናተኩርበት የቋንቋ ክሂል እና አካባቢ እንዲሁም የተጠኚዎች ባህሪ ስለምንለያይ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከተለያየ ማጠቃለያ ልንደርስ እንደምንችል ይታሰባል፡፡ የአማረ ጥናት በጽህፈት ክሂል ላይ በማትኮሩና በጥናቱ ውስጥ ‹‹የማስተማሪያ ዘዴዎች ብቃት ትንተና››ን ማካተቱ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ላይ ጥናቱን መመስረቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም፤ በስህተት ትንተና ላይ ማትኮሩና በጥናት አካባቢና በተጠኚዎቹ ባህሪያት ከዚህ ጥናት ስለሚለይ ይህ ጥናት የሚደርስበት ማጠቃለያ ከአማረ ጥናት የተለየ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡

በአጠቃላይ ከቀደሙት ጥናቶች መካከል ከፊሎቹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማሪያ አውድ ላይ ያተኮሩ፣ ሌሎቹም አንድን ክሂል ብቻ በመቃኘት ላይ አጽንኦት ያደረጉና ሁሉም ደግሞ ይህች አጥኚ ባተኮረችበት የጥናት አካባቢና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ያላተኮሩ በመሆናቸው ብሎም አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ከማበረታቻ አለመኖር ወይም ውሱንነት የሚነሱ መሆን አለመሆናቸውን መቃኘት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ስልትና ዘዴ

ይህ ምዕራፍ ጥናቱ የሚያተኩርባቸውን ቁልፍ የጥናት አካሄድ ጉዳዮች (methodological issues) ያቀርባል፡፡ ምዕራፉ የጥናት ስልት፣ የጥናቱ አካላዮች፣ የተጠኚዎች አመራረጥና የናሙና ማውጫ፣ መረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶችና የመረጃ አተናተን ዘዴን አካቷል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት የተከተለው ዘዴ ገላጭ (descriptive) ጥናታዊ ዘዴ ነው፡ በዚህ ዘዴ በማገዝ የማበረታቻ ጥናቱ ትግበራ ሂደትን በመመርመር በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚቀርቧቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን እንደሚመስሉ፣ ከመረጃዎች በማሳት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አወዶቹ በምን በምን ሜለኩ ጠንካራና መሻሻል የሚባቸው የማበረታቻ ትግበራዎች እንደሚያዩባቸው በገለጻ አስደግፎ ለማትንተንና መፍትሄዎቻቸውን ለማቅረብ ምቹ በመሆኑ የተመረጠ ነው፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ መጠናዊና አይነታዊ ትንተናዎችን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ ቅይጣዊ ዘዴ ላይ አትኩሯል፡፡

### 3.2 የጥናቱ አካላዮች

የዚህ ጥናት አካላዮች በጢሮ አፈታ ወረዳ የሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ አኮ፣ ዲምቱ፣ ገበራ እና ራጋ ሲባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዚህ ጥናት አካላዮች ናቸው፡፡ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ላይ በመመርኮዝ በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን አራቱንም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

### 3.3 የተጠኚዎች አመራረጥና የናሙና ማውጫ

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤት | መማሪያ ክፍል ብዛት | የተማሪ ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | አኮ 2ኛ ደረጃ | 7 | 363 |
| 2 | ዲምቱ 2ኛ ደረጃ | 8 | 482 |
| 3 | ገበራ 2ኛ ደረጃ | 3 | 208 |
| 4 | ራጋ ሲባ 2ኛ ደረጃ | 4 | 265 |
| | ድምር | | 1318 |

በእነዚህ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2010ዓ.ም. ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአኮ በሰባት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 363፣ በዲምቱ በስምንት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 482፣ በገበራ በሶስት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 208

ተማሪዎች እና በራጋ ሲባ በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 265 ተማሪዎች ናቸው *(ምንጭ፡- የየትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር የ2011ዓ.ም. የተማሪዎች ቅበላ ስታቲስቲክስ*)፡፡

ይህ ጥናት መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ በወሳኝ ንሞና ዘዴ ላይ ተመርኩዟል፡፡ በወሳኝ ንሞና ወቅት ከጥናቱ አካላይ መመረጥ የሚኖርባቸውን የናሙና አባላት የሚወስኑት ተመራማሪው ራሱ፣ የምርምሩና የጥናቱ አካላይ ባህሪ ይሆናሉ፡፡ ይህም ማለት እነማን የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ናሙና ሆነው መመረጥ እንዳለባቸው የሚወሰነው በእጣ ወይም እድል ሳይሆን በምርምሩ ባህሪ የተነሳ ተመራማሪው መረጃውን ከተወሰኑ ሰዎች እንዲሰበስብ ሲገደድ፣ ተመራማሪው እነዚህን ብመርጣቸው ለምርምሩ አስፈላጊና በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ ሲወስን የሚጠመው የናሙና ዘዴ ነው (ያለው 2004፣ 131)፡፡

በዚሁ መሰረት አጥኚዋ በወሳኝ ንሞና ዘዴ በመጠቀም በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙት የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች ሁሉ ከ1–10 ደረጃ የወጡ ተማሪዎችን ለዚህ ጥናት በቂ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ብላ ስላመነች በየትምህርት ቤቱ ባሉት መማሪያ ክፍሎች ልክ 10 /አስር/ ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች ከየክፍሉ በመምረጥ በመረጃ አቀባይነት አሳትፋለች፡፡ እነዚህ በመረጃ አቀባይነት የተመረጡ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ውጤቶች አማካይ ውጤታቸው መሰረት ከ1–10 ደረጃ የወጡ በመሆናቸው ተማሪዎቹ ከሌሎች አቻዎቻቸው የተሻለ መበረታታት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ አጥኚዋ በመገመት፤ ጥናቱ ስለሚያቀርበው ማበረታቻ ነክ ጥያቄዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ የማበረታቻ አመለካከትና ግንዛቤ ይዘው ሊገኙ እንደሚችሉ ታስቧል፡፡ በወሳኝ ንሞና ዘዴ እነዚህ ከ1–10 ደረጃ የወጡ ተማሪዎች በአንጻራዊ የተሻለ መረጃ ሊያቀብሉ ይችላሉ ከሚል እሳቤ በመነሳት በናሙናነት የተመረጡ ናቸው፡፡ ሰንጠረዥ 1 (ከስር) ይህንኑ የናሙናዎች መጠን ይዞ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 1፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች እና ናሙናዎች ጥመርታ*

| ተ.ቁ. | የት/ቤቱ ስም | የ9ኛ መማሪያ ክፍሎች ብዛት | የተማሪዎች ብዛት | የናሙናዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | አኮ | 7 | 363 | 38 | 32 | 70 |
| 2 | ዲምቱ | 8 | 482 | 49 | 31 | 80 |
| 3 | ገበራ | 3 | 208 | 18 | 12 | 30 |
| 4 | ራጋ ሲባ | 4 | 265 | 21 | 19 | 40 |
| | ድምር | 22 | 1318 | 126 | 94 | 220 |

በጠቅላላው በ4ቱ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በ22 የዘጠነኛ መማሪያ ክፍሎች ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ 1318 የአራቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መካከል በወሳኝ ንሞና ዘዴ በመደገፍ ከ1–10 ደረጃ ከወጡ ከ220 ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የመምህራን ቁጥር በየትምህርት ቤቶቹ አንድ ወይም ሁለት ነው፡ በአጠቃላይ በአራቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ብዛት አምስት በመሆኑ ከእነዚህ መምህራን መረጃ ማሰባሰቡ አዳጋች ስለማይሆን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ሁሉም በመረጃ አቀባይነት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

### 3.4 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ በርካታ ስልቶች አሉ፡፡ ፈተና፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታ፣ መጠይቅ ቃለመጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለግላሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት ሦስት መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ እነሱም፡ የክፍል ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

#### 3.4.1 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የጽሁፍ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ በመጠቀም ለ220 የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በንባብ እና ጽህፈት ክፍሎች ስለሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች የሚመለከቱ ዝግ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ ዝግ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በቀላሉና

በፍጥነት እንዲመልሱ ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ ጥያቄዎቹ ባለአምስት ምድብ ‹ሊከርት ስኬል› *(በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አቋም የለኝም፣ አልስማማም እና ፈጽሞ አልስማማም)* አማራጭ መልሶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎቹ ከዚህ ቀደም በንባብና ጽህፈት ክሂል የማበረታቻ ስልቶች ላይ በተዘጋጁ ጥያቄዎች በClement እና Kimberly (2014) ላይ በመመስረት (adoption) ተዘጋጅተዋል፡፡ ይህም የመጠይቅ ጥያቄዎቹን አስተማማኝ ለማድረግ ረድቷል፡፡ ተማሪዎቹ መጠይቁን ከመሙላታቸው አስቀድሞ ስለአሞላሉ በአጥኚዋ ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡

### 3.4.2 ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቅ ከተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መረጃ ለመሰብሰብ የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር በከፊል በተዋቀሩ ከአምስት ያልበለጡ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ላይ በመመርኮዝ በንባብና ጽህፈት ማስተማር ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ስለሚጠቀሙባቸው የማበረታቻ ስልቶች ውይይት ተካሂዷል፡፡

### 3.4.3 የክፍል ምልከታ

ምልከታ የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደት በሚከናወንባቸው ክፍሎች ውስጥ በአካል በመገኘት መምህራኑ ንባብና ጽህፈትን እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ በንባብና ጽህፈት ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ምን አይነት ማበረታቻዎችን እንደሚያካሂዱና ተማሪዎቹ እንዴት እንደሚማሩ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ነው፡፡ በአምስቱ የጥናቱ ተተኳሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን አጠቃላይ ብዛት አምስት ነው፡፡ እያንዳንዱን የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመከተል ለሁለት ለሁለት ጊዜያት የክፍል ምልከታ ተካሂዷል፡፡ የክፍል ምልከታው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች ያካተተ የምልከታ ማካሄጃ Check List በማዘጋጀት ከክፍል ምልከታ የሚገኙ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለው Syverson (2016) ያቀረቡትን የክፍል ውስጥ መከታተያ ቅጽ ለዚህ ጥናት እንዲስማማ አድርጎ በማቅረብ ነው፡፡

## 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከመረጃ አቀባዮቹ የተሰበሰቡት የተለያዩ መረጃዎች በመጠናዊ እና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች ተተንትነዋል፡፡ ከተማሪዎቹ በመጠይቅ የተሰበሰቡት መጠናዊ መረጃዎች በትክክል መሞላታቸው እየተረጋገጠ በማህበራዊ ሳይንስ ቅመራዊ ስታቲስቲካዊ ስሌት ማዕቀፍ (SPSS) Version 20 የስታቲስቲካዊ ስሌት ቋት ውስጥ ገብተው የ‹‹ሊከርት ስኬል›› ውጤታቸው ተሰልቷል፡፡ የተገኙት ውጤቶች ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት መሰረት እየተደራጁ በፐርሰንት፣ በአማካይና በመደበኛ ልይይት ስታቲስቲካዊ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች መኖር አለመኖራቸውን ለመተንተን አስችሏል፡፡

ከቃለመጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች መጠናዊ ትንተናዎች ከቀረቡ በኋላ ከጥናቱ ጥያቄዎች ጋር ባላቸው ዝምድና መሰረት እየተደራጁ በአይነታዊ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በመጠናዊ እና አይነታዊ መረጃዎች መካከል ያሉ ተዛምዶዎችን በመቃኘትም በበቂ ገለጻና ማብራሪያ ትንተናው እንዲደገፍ በማድረግ ወደ ማጠቃለያ ተደርሷል፡፡ በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያዎች ድጋፍ የተገኙት መረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲያነቡና ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው? እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ማንበብና መጻፍ ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማበረታቻ ስልት አነቃቂ ነውን? የሚሉ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመተንተን ረድተዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ መረጃ ትንተና

በዚህ ምእራፍ በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለመጠይቅና በክፍል ምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠናዊና አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ መጠናዊው መረጃ ከ220 የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለመሰብሰብሰብ ታቅዶ ከ220 (100%) ተማሪዎች የተሟላ መረጃ በጽሁፍ መጠይቅ ለመቀበል ተችሏል፡፡ ተማሪዎቹ መጠይቁን ከመሙላታቸው አስቀድሞ ስለአሞላሉ በአጥኚዋ ገለጻ የተደረገላቸው በመሆኑ ተሳታፊዎቹ መረጃውን በጥንቃቄ ሞልተዋል፡፡

ከቀረቡት 36 የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች መካከል አስሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች አሉ? ከሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ ሌሎች አስር የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው? የሚለውን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የረዱ ናቸው፡፡ ሌሎች ሰባት የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው? ከሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ዘጠኝ የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ደግሞ መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ሲያስጽፉ እና ሲያስነብቡ ተማሪዎቹን ለማበረታታት የሚጠቀሟቸው የማበረታቻ ስልቶች የቱን ያህል አነቃቂ ናቸው? በሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዱን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የትንተናው አምድ በማድረግ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተንና ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

## 4.1 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች

በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህራን የሚደረግ ማበረታቻ የተለያዩ ክሂሎችንና ንኡሳን ክሂሎችን በተሻለ ሁኔታ ለተማሪዎቹ ለማድረስ፣ ትምህርቱን በተማሪዎቹ የነቃ ተሳትፎ ላይ እንዲመሰረት ለማድረግና የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሻለ ተጨባጭ ለማድረግ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም ለሁለተኛ ቋንቋ የሚሟጥን ማበረታቻ ሚቅደና ሚተግበር አሚኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን ተገብሮ ማጤን አስፈላጊ ነው፡፡ በዚሁ

መሰረት ሰንጠረዥ 1 (ከስር) ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ ማበረታቻ ስለመኖሩ የሰጡት ምላሽ በገላጭ ስታቲስቲካዊ ልኬት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 1፡ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚደረግ ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ*

| | አመልካቾች (indicators) (n=220-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልን ማበረታቻ በክፍል ውስጥ በጓደኛዊ ስሜት እንድማር አግዞኛል፡፡ | 3.94 | .678 |
| 2 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የጥንድና የቡድን ተግባራትን ያካተተ ነው፡ | 3.86 | .607 |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍላችን በተማሪዎች መካከል የመተባበርና የመረዳዳት ስሜት ፈጣሪ ነው፡ | 3.77 | .591 |
| 4 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ ክፍሉን በራሳችን መንገድ እንድንጠቀምበት አድርጓል፡፡ | 3. 65 | .645 |
| 5 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በቋንቋ ለመዳ ሂደቱ ተሳትፎዬን ከፍ አድርጎልኛል፡፡ | 3.57 | .650 |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን በአብዛኛው ያካሂዳሉ፡፡ | 3.48 | .587 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ እንድማር ረድቶኛል፡፡ | 3.35 | .598 |
| 8 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ ምቹ የመማሪያ መድረክ ፈጥሮልኛል፡፡ | 3.21 | .501 |
| 9 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የመቻል ስሜት እየተሰማ እንድንማር ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው፡ | 3.12 | .618 |
| 10 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የትምህርት ግቦችን እንድናስቀምጥ በማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡ | 2.78 | .584 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) | **3.47** | **0.607** |

ከፍ ሲል በቀረበው ስታቲስቲካዊ ውጤት ሰንጠረዥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ማበረታቻ ስለማካሄዳቸው የተጠኚዎቹን ተማሪዎች ምላሾች በገላጭ ስታቲስቲክስ

**ተጠቃለው በየአመላካቾቹ አንጻር በአማካይ ቁጥር ተገልጸዋል፡፡ ከተጠኚዎቹ መካከል የሚበዙት** 81 (36.8%) **አቋም የለኝም፣** 49 (22.3%)**፣ እስማማለሁ፣** 42 (19.1%) **አልስማማም፣** 28 (12.7%) **በጣም እስማማለሁና ቀሪዎቹ** 20 (9.1%) **ፈጽሞ አልስማማም የሚሉ አማራጮች መልሶችን የጠቆሙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የምድቡ አመላካቾች** አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) ልኬት = 3.47 ከአማካይ መደበኛ ልይይት 0.607 ጋር ነው፡ ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ ውጤት መሰረት በተጠኚዎቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማበረታቻ አተገባበር ስታቲስቲካዊ ልኬት መካከለኛ (modest) መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የአማካይ መደበኛ ልይይቱ መጠን እያንዳንዱ መልስ ከአጠቃላይ የአማካይ አማካይ በአንጻራዊ ሰፋ ያለ ልይይት (ሚዛንነጥ) ማሳየቱን የሚያመለክት ነው፡

በዝርዝር ሲታይ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች በአንጻራዊ ከፍ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማበረታቻ ክንውኖች አመላካቾች ሆነው የቀረቡት፤ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በክፍል ውስጥ በጓደኛዊ ስሜት እንዲማሩ ያገዛቸው መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.94 ከመደበኛ ልይይት = 0.678 ጋር (መደበኛ ልይይቱ በአንጻራዊ ሰፊ መሆኑን ይጠቁማል)) ሲሆን፣ ከዚህ በመቀጠል አነስ ባለ ስታቲስቲካዊ ልኬት የተጠቆመው አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የጥንድና የቡድን ተግባራትን ያካተተ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.86 ከመደበኛ ልይይት = 0.607 ጋር)፣ የማበረታቻ ስልቶቹ በተማሪዎች መካከል የመተባበርና የመረዳዳት ስሜት ፈጣሪ መሆናቸው (አማካይ ውጤት = 3.77 ከመደበኛ ልይይት = 0.591 ጋር)፣ የሚደረግላቸው ማበረታቻ ተማሪዎቹ ክፍሉን በራሳቸው መንገድ እንዲጠቀሙበት ወይም እንዲቆጣጠሩት ማድረጉ (አማካይ ውጤት = 3.65 ከመደበኛ ልይይት = 0.645 ጋር) በተማሪዎቹ ምላሾች ተደግፈው ቀርበዋል፡፡ ከፍ ሲል ከቀረቡት ዝርዝር ስታቲስቲካዊ ልኬቶች እንደምንመለከተው በማበረታቻ ትግበራው የተጠኚዎቹ ስምምነት ከፍተኛው ጫፍ አማካይ ውጤት 3.94 ሲሆን ዝቅተኛው 2.78 ነው፡ ከዚህ የምንረዳው በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር የተቀናጀ የማበረታቻ ትግበራ መኖሩንና አተገባበሩ ገደቦች ያሉበት መሆኑን ነው፡

ቀጥሎ የምናገኛቸው ስታቲስቲካዊ ልኬቶች፤ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በቋንቋ ለመማር ሂደቱ ተሳትፏቸውን ከፍ ያደረገላቸው መሆኑን የገለጹበት ስታቲስቲካዊ ልኬት (አማካይ ውጤት = 3.57 ከመደበኛ ልይይት = 0.650 ጋር) ተጠቁሟል፡፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ማበረታቻዎች የተማሪዎቹን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማጎልበት ያበረከቱት ጠቀሜታ መጠን የሚያሳይ ነው፡ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመሆናቸው የማበረታቻ ብልሃቶች ትግበራ ለቋንቋ ለመማሩ ሂደት ትልቅ ግብአት መሆን ከፍርሃትና ሀፍረት በመላቀቅ ስህተት እየሰሩም ቢሆን ለመማር ግፊትና መነቃቃት እንደሚፈጥሩ የታወቀ ነው፡ ይሁንና የማበረታቻ ትግበራው በቋንቋ መማር ሂደቱ ተሳትፏቸውን ለማነሳሳት ያበረከተው ጠቀሜታ ከሌሎች ከስር ከቀረቡ የማበረታቻ አመላካቾች የተሻለ ነው ሊባል ይችል እንደሆን ነው

እንጂ አጥጋቢ ነው ለማለት አያስችልም፡ አማካይ ውጤቱም የሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ማበረታቻዎች በቋንቋ መማር ሂደቱ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ረገድ የሚታየውን ክፍተት ወይም ማሰራት ያለበትን ስራ ነው፡

**አንጻራዊ ዝቅተኛ ስታቲስቲካዊ ልኬት የተመዘገበባቸው አመላካቾች፤** የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን በአብዛኛው ስለማካሄዳቸው (አማካይ ውጤት = 3.48 ከመደበኛ ልይይት = 0.587 ጋር)፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ እንዲማሩ የረዳቸው መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.35 ከመደበኛ ልይይት = 0.598 ጋር)፣ የሚደረግላቸው ማበረታቻ ምቹ የመማሪያ መድረክ የፈጠረላቸው መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.21 ከመደበኛ ልይይት = 0.501 ጋር)፣ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የመቻል ስሜት እየተሰማቸው እንዲማሩ ለማድረግ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.12 ከመደበኛ ልይይት = 0.618 ጋር) እና ከሁሉም ዝቅተኛ ስታቲስቲካዊ ልኬት የተመዘገበበት፤ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የትምህርት ግቦችን እንዲያስቀምጡ በማድረግ ላይ ያተኮረ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 2.78 ከመደበኛ ልይይት = 0.618 ጋር) ቀርበዋል፡፡

ከፍ ሲል ከቀረበው ስታቲስቲካዊ ልኬት ለማስተያየት በሚረዳ መልኩ ከቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ማያያዙ ተገቢ ነው፡ ከቃለመጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፤ እርስዎ አማርኛ ***ቋንቋ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን እንዲጨብጡ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች አሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ መ.1 (መምህር አንድ) ሲመልሱ፤ አዎ፣ ማበረታቻ የሚማሩትን ነገር በተነቃቃ ሁኔታ እንዲማሩ ለማድረግ ስለሚረዳ ማበረታታት አካሂዳለሁ፡፡ በትምህርቱ መጀመሪያ የሚማሩት ርእሰ ጉዳይ ስላለው ፋይዳ አብራራለሁ፤ ያልገባቸውን እንዲጠይቁና ለሚጠየቁት ጥያቄ እንሳሳታለን ብለው ሳይፈሩ በአእምሯቸው የሚጉላለውን ሀሳብ በመሰንዘር በተሳትፎ እንዲማሩ አበረታታለሁ ሲሉ መልሰዋል፡፡***

***መ.2 በበኩላቸው፤ ተማሪዎቹ ስህተት ሲሰሩ ሌሎች ተማሪዎች እንዳይስቁባቸው በማድረግ፣ የተሳሳቱትን ነገር በራሳቸው እንዲያርሙ እድል በመስጠት፣ በራሳቸው መተማመን እንዲፈጥሩ፣ ፍርሃትን እንዲያስወግዱ በማደፋፈር ብሎም በየጊዜው የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታቸውን በጥረታቸው እንዲያሳድጉ በመምከርና በመገፋፋት ማበረታቻ አካሂዳለሁ ሲሉ መልሰዋል፡፡***

***መ.3 በበኩላቸው ቃላዊ ማበረታቻዎችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ፤ ሲያነቡ ‹‹ጎበዝ››፣ ‹‹እጅግ በጣም ጥሩ፣ ይህን እንዲህ በል፣ ያን እንደዚህ አድርግ›› እያልኩ ተማሪዎቹን***

ለማበረታታት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ሲጽፉ ‹‹በጣም ጥሩ ጽፈሃል/ሻል/ ሁላችሁም እንደዚህ ጻፉ››፤ የሆሄያት ግድፈት ሲያጋጥም ‹‹ጥሩ ነው ግን ይህችን በዚህ አስተካክል/ይ/›› በማለት ያለቂጣ ስህተታቸውን እንዲያርሙ አደርጋለሁ፡፡ ከስህተት የጸዳ ስራ ሲያጋጥመኝ ደግሞ ተማሪውን/ዋን/ በስም ጠርቼ አማሰግናለሁ፡፡ ይህን ማድረጌ ብዙዎቹን ተማሪዎች ስህተታቸውን እንዲቀንሱ ሲያደርጋቸው ተመልክቻለሁ ብለዋል፡፡

መ.4 በበኩላቸው፤ አዎ፣ ተማሪዎቹ ማንበብ እንዲችሉ ማንበብ ስለሚያስገኘው ሰፊ ጠቀሜታ በመግለጽ፣ አንድ ትንሽ ጽሁፍ አንብበው እንዲመጡ አድርጌ የተረዱትን መልእክት ለጓደኞቻቸው እንዲገልጹ እድል በመስጠትና እንዲጨበጨብላቸው በማድረግ፣ ስህተቶቻቸውን በትክክለኛ ቅርጽ እንዲለውጡ በመንገር፣ ደጋግመው እንዲያነቡ ግፊት በማድረግና ‹‹እስቲ ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ እንዲህ የሚል መልእክት የሚገኘው የት ጋ ነው? ይህን ቀድሞ የሚነግረኝ አንድ ማርክ ሁለት ማርክ አሁኑኑ እሸልመዋለሁ›› እያልኩ ግፊት እፈጥራለሁ፡፡ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመሆናቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ በሚጽፉበት ጊዜ በአብዛኛው የሳልስና ሳድስ፣ የራብእና ሳብእ ፊደላትን ይገድፋሉ፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል አስቀድሜ የፊደል ገበታን በጽሁፍ አስተምራለሁ፡፡ የሆሄያት ግድፈቶች ሲያጋጥሙኝ ወደ ፊደል ገበታው ሄደው ትክክለኛውን ቅርጽ እንዲጽፉ እመክራለሁ፡፡ ብዙ ጊዜም ብዙ የሆሄያት ስህተቶችን የማርመው በዚህ መንገድ በመሆኑ የፊደል ገበታ መስጠት የእርማት ጫናዬን ቀንሶልኛል ብለዋል፡፡

መ.5 በሰጡት መልስ፤ በንባብ ወቅት ስህተቶችን ሳያስቡ እንዲያነቡ በማድረግ፣ በጽህፈት ወቅት የፊደል፣ የመደብ አመልካች እና ቅጥያዎች ግድፈት ሲፈጽሙ እንዲያስተካክሉ በማድረግና ይህ ችግር በንግግር ጊዜም ሆነ በንባብ ጊዜ ይከሰታል እያልኩ ስህተትን ሳያስቡ እንዲያነቡና እንዲጽፉ በማድረግ እንደሚያበረታቱ ገልጸዋል፡፡

ከቃለመጠይቁ መረጃዎች እንደምንመለከተው በትምህርቱ መጀመሪያ የሚማሩት ርእሰ ጉዳይ ስላለው ፋይዳ በማብራራት፣ ተማሪዎቹ ስህተት ሲሰሩ ሌሎች ተማሪዎች እንዳይስቁባቸው በማድረግ፣ የተሳሳቱትን ነገር በራሳቸው እንዲያርሙ እድል በመስጠት፣ በራሳቸው መተማመን እንዲፈጥሩ፣ ፍርሃትን እንዲያስወግዱ በማደፋፈር፣ በክፍል ውስጥ ተግባራት ቃላዊ ማበረታቻዎችን በመጠቀም፣ በንባብ ወቅት ስህተቶችን ሳያስቡ እንዲያነቡ በማድረግ መምህራኑ ማበረታቻ የሚያካሂዱ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ እነዚህ ማበረታቻዎች በክፍል ውስጥ ግፊት ለመፍጠር ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ ይሁንና

በተማሪዎቹ መካከል የመረዳዳት ስሜትን በማስፈን፣ ጽህፈትን ለተማሪዎቹ በሚስማማ ሁኔታ በማደራጀት፣ ተገቢነት ያለው የጽህፈት ስልተ ትወራ በመምረጥና ደጋግመው እንዲጽፉ በማበረታታት በመሳሰሉት ተለዋዋጭ ስልቶች የተደገፉ ክንዋኔዎችን መምህራኑ አለማካሄዳቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.2 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች

ከሌሎች ክሂሎች አንጻራዊ በሆነ መንገድ ሲታይ የመጻፍ ክሂል አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋም ቢሆን ለበርካታ ተማሪዎች ውስብስብነት የሚታይበት ክሂል እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ክፍል ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው ራሳቸውን ለመግለፅ ፈልገው መግለጫ ቃላት ሲያጡ በተግባቦት ሂደት የሚያሣድርባቸው የፍርሃት ስሜት ከፍተኛ መሆኑንና በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከት ሲያሳድርባቸው ተደጋግሞ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የማበረታቻ ብልሃቶች ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የመማር ሂደታቸውን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩና እንዲመሩ፣ የቋንቋ መማር ሂደታቸውን እንዲያቀላጥፉ፣ የክሂሉን ውስብስብነት ለማቅለልና በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ስልት እንዲያሳድጉ የሚረዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እውቀት ማደግ የሚችለውም ተማሪዎች ራሳቸው የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ በመሆን በንቃት ሲሳተፉ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ማበረታቻዎችን ከሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ አውድና ከክሂሉ ውስብስብነት ባህሪ ጋር ባገናዘበ መልኩ መተግበር አለመተግበራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 2 በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን እንደሚመስሉ ተማሪዎቹ የሰጧቸው ምላሾች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

*ሰንጠረዥ 2፡ በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ*

| | አመልካቾች (indicators) (n=220-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት መጻፍ እንዳለብን ተገቢ መመሪያ ከመምህራችን ይሰጠናል፡ ፡ | 3.52 | .566 |
| 2 | መምህራችን የአማርኛ ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአትንና መዋቅርን እንድንጠብቅ ያለማምዱናል፡ ፡ | 3.50 | .507 |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በየጊዜው የመጻፍ ክንውኖቻችንን በማማማ ያበረታቱናል፡ ፡ | 3.47 | .521 |
| 4 | በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ ለልምምድ የሚሆኑ ክንውኖችን ያካተተ ነው፡ | 3. 35 | .545 |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በመጻፍ እንድንበረታታ የሚያደርጉት ማበረታቻ ስህተቶቼን እያረሙኩ የመጻፍ ችሎታዬን እንዳሳድግ ረድቶኛል፡ ፡ | 3.27 | .550 |
| 6 | መምህራችን አዎንታዊ የሆነ የመጻፍ ክሂል መመሪያ ምቹ ደባብ ይፈጥሩልናል፡ ፡ | 3.18 | .567 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መመሪያ ክፍላችን በመጻፍ ክንዋኔ እንድንበረታታ አዎንታዊ ግፊት ፈጣሪ ነው፡ | 2.85 | .598 |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ተከታታይ የድርሰት መጻፍ መጣራ እንድናደርግ ያበረታቱናል፡ ፡ | 2.71 | .581 |
| 9 | በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ በቂ ማበረታቻ ይደረግልናል፡ ፡ | 2.62 | .543 |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ደጋግመን እንድንጽፍ በማድረግ ተከታታይ በሆነ መልኩ ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል፡ ፡ | 2.52 | .558 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) | **3.10** | **0.553** |

***ከተጠኚዎቹ መካከል የሚበዙት*** 78 (35.5%) ***አልስማማም፣*** 57 (25.9%) ***አቋም የለኝም፣*** 41 (18.6%)፣ ***እስማማለሁ፣*** 25 (11.4%) ***በጣም እስማማለሁና ቀሪዎቹ*** 19 (8.6%) ***ፈጽሞ አልስማማም የሚሉ አማራጮች መልሶችን የጠቆሙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የመጻፍ ክሂል ማበረታቻ አመላካቾች*** አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) ልኬት = 3.10 ከአማካይ መደበኛ ልይይት 0.553 ጋር ነው፡ ተጠኚዎቹ ከመጻፍ ክሂል ጋር በተያያዘ መምህራት ስለሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች የሰጧቸው ምላሾች አጠቃላይ የአማካይ አማካይ ስታቲስቲካዊ ልኬት ከሌሎቹ ሰንጠረዦች ምላሾች አንጻር ሲታይ በጣም ዝቅተኛው ሲሆን ይህም የሚያሳየው በመጻፍ ክሂል የሚገበረው ማበረታቻ በጣም ውስንና መሻሻል የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡

በዝርዝር ሲታይ በአንጻራዊ የተሻሉ ከመጻፍ ክሂል ጋር የተያያዙ የማበረታቻ ስልቶች እንዳሉ የሚጠቁሙ አመላካቾች፤ ተማሪዎቹ በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ተገቢ መመሪያ ከመምህራቸው የሚያገኙ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.52 ከመደበኛ ልይይት = 0.566 ጋር) ሲሆን፣ መምህራኑ የአማርኛ ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአትንና መዋቅርን እንዲጠብቁ የሚያለማምዱ መሆኑ ሁለተኛው የተጠኚዎቹ አንጻራዊ የተሻለ ትኩረት (አማካይ ውጤት = 3.50 ከመደበኛ ልይይት = 0.507 ጋር) ያገኘ ነው፡ ቀጥሎም፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በየጊዜው የተማሪዎቹን የጽሁፍ ክንውኖች በማየት ተማሪዎቹን የሚያበረታቱ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.47 ከመደበኛ ልይይት = 0.521 ጋር)፣ በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግላቸው ማበረታቻ ለልምምድ የሚረዱ ክንውኖችን ያካተተ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.35 ከመደበኛ ልይይት = 0.545 ጋር)፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በመጻፍ እንዲበረታቱ ለተማሪዎቹ የሚያደርጉት ማበረታቻ ስህተቶቻቸውን እያረሙ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ የረዳቸው መሆኑ (አማካይ ውጤት = 3.27 ከመደበኛ ልይይት = 0.550 ጋር) በተጠኚዎቹ ተጠቁመዋል፡፡

ሌሎች እንደ አዎንታዊ የሆነ የመጻፍ ክሂል መመሪያ ምቹ ደባብ መፍጠር (አማካይ ውጤት = 3.18 ከመደበኛ ልይይት = 0.567 ጋር)፣ መመሪያ ክፍላቸው በመጻፍ ክንዋኔ እንዲበረታቱ አዎንታዊ ግፊት ፈጣሪ መሆኑ (አማካይ ውጤት = 2.85 ከመደበኛ ልይይት = 0.598 ጋር)፣ ተከታታይ የድርሰት መጻፍ መልመጃ እንዲያደርጉ ማበረታታት (አማካይ ውጤት = 2.71 ከመደበኛ ልይይት = 0.581 ጋር)፣ በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረገው ማበረታቻ በቂ ስለመሆኑ (አማካይ ውጤት = 2.62 ከመደበኛ ልይይት = 0.543 ጋር) እንዲሁም ተማሪዎቹ ደጋግመው እንዲጽፉ በማድረግ ተከታታይ በሆነ መልኩ ምጋቤ ምላሽ መስጠት (አማካይ ውጤት = 2.52 ከመደበኛ ልይይት = 0.558 ጋር) መሆኑን ስታቲስቲካዊ ልኬቶቹ ያሳያሉ፡፡

ቀጥሎ በቃለመጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ አማካኝነት፤ አማርኛ ቋንቋ በሚያስተረምሩባቸው ክፍሎች ተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በቀረበላቸው ጥያቄ፤ መምህር 1 (መ.1) ሲመልሱ፤ ምን እንደሚጻፉ አስቀድሜ ለማብራራት ጥረት አደርጋለሁ፡ ከሚጻፉት ይዘትና አላማ ጋር በተገናዘበ መልኩ ሊከተሉት የሚገባ (ሞዴል) ጽሁፍም አቅርቤ አወያያለሁ፡ ከበድ ያሉ ቃላትን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትርጉማቸውን እገልጻለሁ፡ በሚጽፉበት ጊዜ ስለሚጽፉት ጉዳይ እንዲያሰላስሉ ለማድረግ የሚበቃ ጊዜ እሰጣለሁ፡ በመጻፍ ሂደት እያሉ በመዘዋወር እየተመለከትኩ ስህተቶችን እንዲያቃኑ እመክራለሁ፡ ስለመጻፍ ጥቅምም በየጊዜው እነግራቸዋለሁ፡ ይሁን እንጂ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ከባድ በመሆኑ እንደ አንቀጽና ድርሰት ባሉ ጽሁፎች ውስጥ ተማሪዎቹ በርካታ ስህተቶችን ስለሚፈጽሙ እርማቱና ምጋቤ ምላሹ ጫና ያለበት በመሆኑ ብዙ ጊዜ እንዲጽፉ አላደርግም ብለዋል፡፡

መ.2 በበኩላቸው ለመጻፍ የተፈለገውን ጽሁፍ የሚዋቅል ይዘት አስቀድሜ አቀርብላቸዋለሁ፡፡ ከመጻፋቸው በፊት ከሚጽፉት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ይዘት ያለው ጽሁፍ እንዲያነቡ፣ በሚልእክቱ ላይም የአቻና የቡድን ውይይት እንዲያካሂዱ በማድረግ ጭብጡን እንዲገነዘቡ አደርጋለሁ፡፡ ተገቢ ስርአተ ነጥቦችንና አያያዥ ቃላትን በተገቢ ቦታቸው እንዲጠቀሙ አስተምሬ ሳበቃ ሲጽፉ በመከታተል ለሚያም እሞክራለሁ፡፡ በጻፉት ነገር ላይ የእርስ በርስ እርማት እንዲያካሂዱም እድል እሰጣለሁ፡፡ ይሁንና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ፊደላትን መማር የጀመሩት ከ5 ክፍል ደረጃ በመሆኑና በቂ የመጻፍ ክሂል ተጋልጦና ልምድ ይዘው አልመጡም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ለማንገርና ለመጻፍ ያላቸው ተጋልጦ በክፍል ውስጥ ብቻ የተገደበ መሆኑ ከመጻፍ ክሂል ውስብስብነት ጋር ተዳምሮ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለመጻፍ ተበረታችነት አያሳዩም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ውስጥ አንዳንድ የኦሮምኛ ቋንቋ ቃላትን የሚጠቀሙ ተማሪዎች አሉ፡፡ አንዳቸው ከሌላቸው ለለዩ የሚችሉት በእጅ ጽሁፍ (የፊደል አጻጻፍ) እንጂ በብዙ መልኩ ሀሳብን በጽሁፍ ውስጥ አሳክቶ ወይም አቀናብሮ በማቅረብ ተመሳሳይና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለዚህ የአማጪኒት ክሂል ያላቸው ዳራ እውቀት እጅግ በጣም ውሱን በመሆኑ የመጻፍ ክሂል ማበረታቻዎች እምብዛም ውጤታማ አይደሉም፡፡ ይህም በአማርኛ ቋንቋ ዘግይተው መጻፍ ከመጀመራቸውና አብዛኞቹ ተማሪዎች በቋንቋው ተግባቦት ማካሄድ የሚችገሩ ከመሆናቸው ጋር የተያያዘ ችግር እንደሆነ እገምታለሁ ሲሉ አስተያታቸውን ሰጥተዋል፡፡

መ.3 በበኩላቸው፡- የእከሌን አጅ ጽሁፍ ተመልከቱ! በጣም ያምራል፡፡ እከሌ እንደዚህ አርገህ መጻፍ በመቻልህ አደንቅሃለሁ፡፡ ሁላችሁም የእሱን የብእር አጣጣል ተከትላችሁ ብትጽፉ ጽሁፋችሁ ያማረ ይሆናል እያልኩ እሞክራለሁ፡፡ የጻፉትን ደጋግመው በማንበብና በማየት በችኮላ የፈጸሙት ስህተቶች ካሉ እንዲያርሙ ግፊት አደርጋለሁ፡፡ የቋንቋ ልምዳቸው ውሱን በመሆኑ የተነሳ ብዙ ተማሪዎች አጥርተውና አብራርተው ሃሳባቸውን በጽሁፍ የማቅረብ ችግር አለባቸው፡፡ በዚህ ተጽእኖ የተነሳ መጻፍ ለብዙ ተማሪዎች ከባድ በመሆኑ በበኩሌ ብዙ ጊዜ ደርሰት አላስጽፍም፡፡ ምክንያቱም ከልምድ እንደተገነዘብኩት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ደርሰት ጻፉ ብዬ በተመሳሳይ መንገድ የቀረበ ጽሁፍ አሳይቼ፣ ስህተት አንዱ የመማሪያ መንገድ እንደሆነ ደጋግሜ በመናገር አበረታትቼ ብዙ ተማሪዎች ቁጡ ይሆናሉ፤ ፍላጎት ያጣሉ ብለዋል፡፡

መ.4 በበኩላቸው፡- የቃላት ስህተት ብዙ ጊዜ የሚያጋጥም የበርካታ ተማሪዎች ችግር ነው፡፡ እንደመፍትሄ በማስተምርባቸው ክፍሎች ሁሉ በአመቱ የመጀመሪያው ክፍለጊዜ የማደርገው የፊደል ገበታን ከዲቃላ ፊደላት ጭምር በደብተራቸው ላይ አስፍረው እንዲያሳዩኝ ማድረግ ነው፡፡ ፊደላት ሲሳሳቱ ወደዚያ እማራቸውና ትክክለኛውን ቅርጽ እንዲጠቀሙ አደርጋለሁ፡፡ በየመማሪያ ክፍላቸው በቡድን ተግባር የስርአተ ነጥቦች ቻርት አዘጋጅተው በየክፍሉ ግድግዳ እንዲለጥፉ በማድረግ ሲጽፉ የስርአተ ነጥቦች ቻርቱን እንዲመለከቱ እነግራቸዋለሁ፡፡ በዚህ መልኩ የፊደላትና የስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም ስህተቶችን ለመቀነስ ብችልም ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪነታቸው የቃላት አጠቃቀማቸው ላይ ብርቱ ተጽእኖ አለው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር በቅድሚያ ለቃላት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ ምክንያቱም በተግባቦት ሂደት ተማሪዎች ፍላጎታቸውንና

ሐሳባቸውን በተመለከተ በተገቢው መንገድ ጽፈው ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል የቃላት እውቀታቸው ቁልፍ ሚና ያለው በመሆኑ ነው፡ ይሁን እንጂ በትምህርት ቤታችን የበርካታ ተማሪዎች የቃላት ግንዛቤ በሚፈለገው ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችል አይደለም፡ አማርኛ ቋንቋ በሚማሩባቸው ክፍሎች ውስጥ አብዛኞቹ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በስፋት ለማጎልበት የሚያስችል የቃላት ግንዛቤ የላቸውም፡ ያለ ቃላት እውቀት ከሚዲያ ሚዲያዎች ትእዛዛት ጋር በተገናዘበ መልኩ መጻፍን ማጎልበር አስቸጋሪ ነው፡ ሚዲያ ሚዲያዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ዳራ ይመጥናል ወይ? ማጣናትና መቅለስ ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል ብለዋል፡፡

*መ. 5 ደግሞ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን እንዳይፈጽሙ፣ ቢፈጽሙም ለማረም የሚያስችላቸውን አቅጣጫ በመጠቆም፣ ከቃላት ወደ ቃላት፣ ከሃረግ ወደ ሃረግ እና ከአረፍተነገር ወደ አረፍተነገር ሲሸጋገሩ መከተል የሚገባቸውን ቀለል ያለ መንገድ በማሳየት እገዛ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡*

*በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቹ* ምን እንደሚጽፉ አስቀድመው ለማብራራት ጥረት በማድረግ፣ ለመጻፍ የተፈለገውን ጽሁፍ የሚያቅል ይዘት አስቀድመው በማቅረብ፣ የጻፉትን ደጋግመው በመቅለስና በማየት በችኮላ የፈጸሟቸው ስህተቶች ካሉ እንዲያርሙ ግፊት በመፍጠርና ለጥሩ ስራ እውቅና በመስጠት፣ የቃላት፣ የስርአተ ነጥቦችና *ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን እንዳይፈጽሙ ክትትል በማድረግ የሚያበረታቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ይሁንና ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ለመጻፍ በቂ የቃላት እውቀት የሌላቸው ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ መምህራኑ እያንዳንዱ ተማሪ ዘንድ ደርሰው ለመርዳትና ለማበረታታት የሚያደርጉት ጥረት እንዲሁም ተማሪዎቹ የመጻፍ ክንዋኔን እንዲወዱና እንዲለምዱ የሚፈጥሩት ግፊት መኖሩ አልተገለጸም፡፡ የመምህራኑ የጽህፈት ክፍለ ጊዜ ማበረታቻ ተማሪዎቹ ስለሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይ የተብራራ ገለጻና የሂደት ዝርዝር፣ ስለሚያከናውኑት ሂደታዊ የጽህፈት ተግባር እቅድ፣ ድራፍት፣ መከለስ፣ አርትኦት ማካሄድ፣ የአቻ እርማት፣ ጽሁፉን የማንበቢያና አስተያየት መስጫ፣ እንዲሁም የግብረ መልስ ክንዋኔዎችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ማካተት ቢያስፈልግም* (Bachman 2011) *በነዚህ ስልቶች የተጠናከረ የመጻፍ ክሂል ማበረታቻ አይካሄድም፡፡*

## 4.3 *የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች*

የማንበብ ክሂል በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሁሉንም ክሂሎች ለማዳመጥ ወይም ለመናገር መሰረት ነው፡ ተማሪዎች በሚያነበቡበት ጊዜ ሁሉ የተለያዩ ጸሃፊዎች ጽሁፎቻቸውን ለማቅረብ የተከተሉዋቸውን የተለያዩ ስልቶች የመቅሰም እድል ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ጥሩ ማንበብ ለጥሩ መጻፍ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ከማንበብ ክሂል ጋር ተያይዞ ተማሪዎቹ የሚያከናውኗቸው አጥጋቢ አንብቦ የመረዳት ሂደቶች በጽሁፍ የቀረቡ መልእክቶችን በሚገባ መረዳት ያስችላቸዋል፡፡ አንብቦ መረዳታቸው እየተሻሻለ በሄደ መጠን ማንበብን በራሳቸው ውስጣዊ ግፊት በማካሄድ የሚያነቡትን ጽሁፍ ያለምንም እገዛ መርጠው አንብበው ይረዳሉ፡ መምህራን በማንበብ ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ብልሃቶችን በማቅረብ ልምምድና ማበረታቻ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንዱ የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄም **የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በማንበብ ጊዜ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን እንደሚመስሉ ማወቅ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በሰንጠረዥ 3 (ከስር) የተሳታፊዎቹ ምላሽ ስታቲስቲካዊ ልኬት ቀርቧል፡፡**

***ሰንጠረዥ 3፡ በአማርኛ ቋንቋ ሲያነቡ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ ስለመኖሩ የተማሪዎቹ ምላሽ***

| | አመልካቾች (indicators)<br>(n=220-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት ማንበብ እንዳለብን ተገቢ መመሪያ ከመምህራችን ይሰጠናል፡፡ | 4.04 | .555 |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ብዙ ጊዜ የማንበብ ክንዋኔን ለመጻፍ መነሻ ያደርጋሉ፡፡ | 4.00 | .568 |
| 3 | በመማሪያ ክፍላችን ውስጥ የማንበብ ችሎታችንን እንድናሻሽል ለማድረግ በሚዳ መልኩ መምህራችን ማንበብን ከመጻፍ ጋር አቀናጅተው ያስተምራሉ፡፡ | 3.97 | .541 |
| 4 | በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ በምማረው ጉዳይ ላይ ተመስጦ ፈጣሪነቴ ከፍ ያለ ነው፡ | 3. 89 | .585 |
| 5 | በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ አዳዲስ መረጃዎችን እንድናስስ ያደርገናል፡፡ | 3.87 | .560 |
| 6 | በማንበብ ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ ከቀሰምነው እውቀት፣ ካገኘነው ልምድና መረጃ ጋር ተገናዛቢ ነው፡ | 3.78 | .513 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ ማማህራችን ራሳችን እንደናነብ ቀጣይነት ባለው መልኩ ግፊት ያደርጋሉ፡ | 3.69 | .557 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) | **3.89** | **0.554** |

**ከተጠኚዎቹ መካከል** 83 (37.7%) **አቋም የለኝም፣** 72 (32.7%)፣ **እስማማለሁ፣** 53 (24.1%) **አልስማማም፣** 12 (5.5%) **በጣም እስማማለሁ፣** 0 (0%) **ፈጽሞ አልስማማም የሚሉ አማራጮች መልሶችን የጠቀሙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የምድቡ አመላካቾች** አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) ልኬት = 3.89 ከአማካይ መደበኛ ልይይት 0.554 ጋር ነው፡ ከተሰበሰቡት የመጠናዊ መረጃዎች ምድቦች (categories) ሁሉ አንጻራዊ የተሻለ ምላሽ (ẍ) = 3.89 የታየበት በማንበብ ክሂል ዙሪያ በሚደረጉ የማበረታቻ አመላካቾች (indicators) ሲሆን መደበኛ ልይይቱም በአንጻራዊ ጠበብ ያለ መሆኑ በተሳታፊዎቹ ምላሾች መካከል ከአጠቃላይ የአማካይ አማካይ ውጤት የሚታየው ግለሰባዊ ሚዛንገጥ ጠበብ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡ በሌላ አገላለጽ አብዛኛዎቹ ተጠኚዎች በአብዛኛው ተቀራራቢ ምላሾችን እንደሰጡ ማሳያ ነው፡

በዝርዝር ሲጠኑ ማላሾቹ ከፍ ባለ ሁኔታ ማስማማታቸውን የገለጹባቸው የማንበብና ማበረታቻ ተጠማሽ አመላካቾች በቅደም ተከተል፤ በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ተገቢ መመሪያ ከመምህራቸው የሚሰጣቸው መሆኑ (አማካይ ውጤቱ = 4.04 ከመደበኛ ልይይት = 0.555 ጋር)፣ ብዙ ጊዜ የማንበብ ክንዋኔን ለጽህፈት ማገሻ ማድረጋቸው (አማካይ ውጤቱ = 4.00 ከመደበኛ ልይይት = 0.568 ጋር)፣ በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ተማሪዎቹ የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ በሚዳ መልኩ መምህራኑ ማንበብን ከጽህፈት ጋር አቀናጅተው ማስተማራቸው (አማካይ ውጤቱ = 3.97 ከመደበኛ ልይይት = 0.541 ጋር) በተጠኚዎቹ አንጻራዊ ከፍ ያለ ስምምነት የታየባቸው መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡

ቀጥሎ በአብዛኛዎቹ ተጠኚዎች የተደገፉ የማንበብና ማበረታቻ ጥምረት አመላካቾች ስታቲስቲካዊ ልኬት መካከለኛ የማበረታቻ ትግበራ መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው፡ እነዚህም፤ በማንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በሚነበቡት ጉዳይ ላይ ተመስጦ ፈጣሪነቱ ከፍ ያለ መሆኑ (አማካይ ውጤቱ = 3.89 ከመደበኛ ልይይት = 0.585 ጋር)፣ በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግላቸው ማበረታቻ አዳዲስ መረጃዎችን እንዲያስሱ ለማድረግ የሚዳ መሆኑ (አማካይ ውጤቱ = 3.87 ከመደበኛ ልይይት = 0.560 ጋር)፣ በማንበብ ክፍለ ጊዜ የሚደረግላቸው ማበረታቻ ከቀሰሙት እውቀት፣ ካገኙት ልምድና መረጃ ጋር ተገናዛቢ መሆኑ (አማካይ ውጤቱ = 3.78 ከመደበኛ ልይይት = 0.513 ጋር) እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቹ ራሳቸው እንዲያነቡ ቀጣይነት ባለው መልኩ ግፊት ማድረጋቸው (አማካይ ውጤቱ = 3.69 ከመደበኛ ልይይት = 0.557 ጋር) ተጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል፤ ከማንበብ ክሂል ጋር በተዛመደ ሜሎኩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ስለሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች በቃለመጠይቅ የተሰበሰበት ሚጃዎች ከመጻፍ ክሂል የተሻለ ተሞክሮ እንዳለ ያሳያሉ፡፡ ከማንበብ ጋር የተያያዙ ማበረታቻዎችን በተመለከተ መምህር 1 (መ.1) የቀረበውን ጽሁፍ /ምንባብ/ በአንቀጽ በአንቀጽ በመከፋፈልና በቡድን በቡድን ሆነው አንብበው እንዲረዱና የተረዱትን ጽሁፍ ሜእክት በአንድ አረፍተነገር አሳጥረው እንዲያቀርቡ፣ የማንበብ ክንውኑን በቤት ስራነት በመስጠት ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው አንብበው የተረዱትን ሜእክት በክፍል ውስጥ እንዲወያዩበት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

መ.2 በበኩላቸው በማንበብ ሂደት እያሉ በመከለሉ ማንበጡ ገታ አድርገው ስላነበቡት ፍሬ ነገር በጥልቀት እንዲያስቡና ወደፊት በምንባቡ ውስጥ ስለሚቀርበው ጉዳይ እንዲገምቱ ማድረግ፣ የቀረበውን ጽሁፍ ደግሞ አውጥተው በየተራ እንዲያነቡ በማድረግ አሳታፊ የማንበብ ክፍለ ጊዜ እንደሚፈጥሩና ከማንበብ በኋላ ስለጽሁፉ አጠቃላይ ጭብጥ ሃሳብ እንዲሰጡ የማድረግ አቅጣጫ አብዝተው እንደሚከተሉ የገለጹ ሲሆን፤ ሁሉንም ተሜዎች በማንበብ ለማሳተፍ ግን ማንበብ አዳጋች የሚሆንባቸው ተሜዎች እንደሚጋጥሟቸው፣ የቃላት ትርጉም ሳይረዱ የሚያነቡ ተሜዎች እንዳሉ፣ አልፎ አልፎ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ ፍላጎት የሚያሳዩ፣ አይገባኝም ብለው ተስፋ የሚቆርጡ ቋንቋውን አስተካክለው ማንገር የሚችሉና የማንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተሜዎች እንደሚጥሟቸው ጠቁመዋል፡፡

መ.3 በበኩላቸው ቃላትን ሳይቆጥሩና ሳይደግሙ ማንበብ እንዲሞክሩ እንደሚለማመዱ፣ መክራቸው አበረታች እንደሆነ ና ሆሄያትና ቃላትን አከታትለው በማንበብ ያልተቆራረጠ ማንበብ ለማካሄድ ልምምድ እንዲያደርጉ እንደሚመክሩ፣ በክፍል ውስጥ በጥሩ ሁኔታ አጢርተው የሚያነቡ ተሜዎችን በስም ጠርተው እንደሚሞገሱ ገልጸዋል፡፡ መ.4 ደግሞ ደጋግመው በማንበብ እንዲተጉ፣ ሲያነቡ የተሳሳቱትን ቆም አድርጎ ራሳቸው እንዲያስተካክሉት እድል በመስጠት፣ ያለ ፍራቻ እንዲያነቡ በማፋፈር፣ በጥሩ ሁኔታ ያነበበትን <<አመሰግናለሁ፣ በርታ/ቺ ወደፊት ጥሩ አንባቢ ትሆናለህ/ሽ>> በማለት እንደሚበረታቱ ጠቁመዋል፡፡

መ.4 በሰጡት ምላሽ፤ በቅድሚያ እንደ ንባቡ አላማ ስልት አስቀድሜ አንብቤ ሳበቃ ለተሜዎቹ ቁልፍ ቃላትን በቅድመ ንባብ ጊዜ በማቅረብ፣ ምንባቡ ያዘለውን ርእሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ የሚሞክል ገለጻ በማቅረብ ማነቃቂያ አድርጎ ወደ ንባቡ እንዲያመሩ የማድረግ አቅጣጫ በመከተል፣ በበንባብ ጊዜ የዘለሏቸው ፊደላትና ቃላት ካሉ ደግመው እንዲሏቸውና አስተካክለው እንዲያነበዋቸው በማድረግ እንደሚያስተካክሏቸው ገልጸዋል፡፡

## 4.4 *መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ሲያጽፉ እና ሲያስነብቡ ተማሪዎቹን ለማበረታታት የሚጠቀሟቸው የማበረታቻ ስልቶች የአነቃቂነት ደረጃ*

በቋንቋ መሜያ ክፍል ውስጥ ከክሂል ትምህርቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርብ ማበረታቻ ተሜዎቹን በማነቃቃት ትምህርቱን ለመቀበል ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡ በጥሩ ሁኔታ የታቀደ ማበረታቻ በሚገበርበት

የመማሪያ አዉድ ተማሪዎች የተሻለ ማቃቃት እንዲኖራቸዉ፣ በሚማሩት ነገር ዙሪያ ተሳትፎ፣ ማስተጋብርና ትከረት እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡ ይህ አይነቱ ማቃቃት ባለበት **ቋንቋ መማሪያ** ክፍል ዉስጥ በመምህሩና በተማሪዎቹ እንዲሁም በተማሪዎቹና በተማሪዎቹ መካከል ተፈላጊዉን አዎንታዊ ትምህርታዊ ግንኙነት በመፍጠር ተግባራትን ለማቀላጠፍ እንደሚዳ የታወቀ ነዉ፡ በዚህ መሰረት **የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ የአነቃቂነት ደረጃ ምን እንደሚመስል ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 4 ተተንትኖ ቀርቧል፡፡**

***ሰንጠረዥ 4፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ የአነቃቂነት ደረጃ የተማሪዎቹ ምላሽ***

| | አመልካቾች (indicators) (n=220-1) | አጠቃላይ አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል መምህራችን ከችሎታ፣ ልምድና ፍላጎታችን የተዛመዱ ተግባራትን በማቅረብ ያነቃቁናል፡፡ | 3.84 | .566 |
| 2 | በክፍል ዉስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በመማር ሂደት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች ለማቃለል ረድቶኛል፡፡ | 3.80 | .569 |
| 3 | በክፍል ዉስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ ጠንካራና ደካማ ጎኖቼን ለይቼ በማወቅ ጠንክሬ እንድሰራ ረድቶኛል፡፡ | 3.77 | .621 |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ዉስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ትምህርቴን በኃላፊነት ማፈስ እንዳከናዉን ረድቶኛል፡፡ | 3. 68 | .645 |
| 5 | በክፍል ዉስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በራስ መተማመን ፈጥሮልኛል፡፡ | 3.55 | .590 |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ዉስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የመማር ዝንባሌና ፍላጎቴን ከፍ አደርጎልኛል፡፡ | 3.48 | .546 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ዉስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የትምህርቱን ዉጤት ለማሻሻል አግዞኛል፡፡ | 3.31 | .588 |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በመጻፍ ተግባር እንድንበረታታ የጽህፈት መልመጃ /ዎርክ ሾፕ/ ይሰጡናል፡፡ | 2.76 | .609 |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ዉስጥ የተለያዩ የማበረታቻ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ | 2.63 | .544 |
| | አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) | **3.42** | **0.586** |

**ከተጠኚዎቹ መካከል በአንጻራዊ ከፍ ያለ እጅ የያዙት 64 (29.1%) አቋም የለኝም፣ 55 (25%)፣ እስማማለሁ፣ 41 (18.6%) አልስማማም፣ 33 (15%) በጣም እስማማለሁና ቀሪዎቹ 27 (12.3%) ፈጽሞ አልስማማም የሚሉ አማራጮች መልሶችን የጠቆሙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የዚህ ምላሾች ምድብ አመላካቾች** አጠቃላይ የአማካይ አማካይ (ẍ) ልኬት = 3.42 ከአማካይ መደበኛ ልይይት 0.586 ጋር ተመልክቷል፡፡ የገላጭ ስታቲስቲካዊ ውጤቱ አጠቃላይ ልኬት በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ማበረታቻ ስልቶች የአነቃቂነት ማነስ ገደቦች ያሉበት መሆኑን የሚያሳይና ማበረታቻን ይበልጥ አነቃቂ ለማድረግ ከአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚጠበቀውን የማሻሻያ ጥረት በጉልህ የሚያሳይ ነው፡ በሌላ አገላለጽ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የሚተገበሩ የአማርኛ ቋንቋ ማበረታቻ ስልቶች ቢኖሩም በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎቹን ለማነቃቃት ያላቸው ድርሻ ገደቦች ያሉበት መሆኑ ይታያል፡፡

በዝርዝር ሲታይ በአንጻራዊ የተሻሉ ማነቃቃት ፈጣሪ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶች ስታቲስቲካዊ ውጤቶች የተመዘገበት፤ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል መምህራኑ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ልምድና ፍላጎት የተዛመዱ ተግባራትን ማቅረባቸው (አማካይ ውጤት = 3.84 ከመደበኛ ልይይት = 0.566 ጋር)፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በመማር ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል ያላቸው ጠቀሜታ (አማካይ ውጤት = 3.80 ከመደበኛ ልይይት = 0.569 ጋር)፣ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረጉላቸው ማበረታቻዎች ተማሪዎቹ ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን ለይተው በማወቅ እንዲማሩ ማድረጉ (አማካይ ውጤት = 3.77 ከመደበኛ ልይይት = 0.621 ጋር)፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በኃላፊነት ማፈስ እንዲያከናውኑ ያለው ጠቀሜታ (አማካይ ውጤት = 3.68 ከመደበኛ ልይይት = 0.645 ጋር) በምላሾቹ ተጠቁመዋል፡፡

በመቀጠልም፤ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በራስ መተማመን መፍጠሩ (አማካይ ውጤት = 3.55 ከመደበኛ ልይይት = 0.590 ጋር)፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የመማር ዝንባሌና ፍላጎታቸውን ከፍ ለማድረግ ያለው ጠቀሜታ (አማካይ ውጤት = 3.48 ከመደበኛ ልይይት = 0.546 ጋር)፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የተማሪዎቹን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል ያበረከተው እገዛ (አማካይ ውጤት = 3.31 ከመደበኛ ልይይት = 0.588 ጋር) መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

እነዚህ የማበረታቻ አሃዶች አስቀድሞ ከተተነተኑት ምላሾች ዋጋቸው በአንጻራዊ አገላለጽ ያነሰ ነው፡ ማበረታቻ በአጥጋቢ ሁኔታ የተበጀና የተደራጀ ከሚያሰኙት ጉዳዮች አንዱ ሆኖ የሚታሰበው በተማሪው የመማር ተሞክሮ በበቂ ሁኔታ በራስ መተማመን ለመፍጠር ማገልገሉ ነው፡ በራስ መተማመን በትምህርት አለም ትልቁ

ማነቃቃትና የመማር ዝግጁነት ማለጫ ነው፡ በዚሁ መሰረት በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በራስ መተማመን መፍጠሩ እንዳለ ሆኖ የቀረበበት ስታቲስቲካዊ ልኬት ውሱን ነው፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የመማር ዝንባሌና ፍላጎታቸውን ከፍ ለማድረግ ያለው ጠቀሜታ እና የተማሪዎቹን የትምህርት ውጤት ለማሻሻል ያበረከተው እገዛ ተቀራራቢ መሆናቸውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ የሌሎች ተላውጦዎች ተጽእኖ ከሌለ የመማር ዝንባሌንና ፍላጎትን ለማነሳሳት ማበረታቻ ባለው አበርክቶ መጠን ትይዩ የተማሪዎች የትምህርት ውጤት እድገት ያሳያል፡፡

በመጨረሻ ዝቅተኛ አማካይ ውጤት የተመዘገበባቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ ማበረታቻዎችና የተማሪዎቹ መነቃቃት መጠን ስታቲስቲካዊ ልኬቶች የሚታዩባቸው፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ተማሪዎቹ በጽሁፍ ተግባር እንዲበረታቱ የጽህፈት መስራ /ዎርክ ሾፕ/ ማስጠታቸው (አማካይ ውጤት = 2.76 ከመደበኛ ልይይት = 0.609 ጋር) እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማበረታቻ ዘዴዎችን መጠቀማቸው (አማካይ ውጤት = 2.63 ከመደበኛ ልይይት = 0.544 ጋር) ተጠቁመዋል፡፡

ቀደም ሲል ስለመጻፍ ክሂል ከተተነተነው መረጃ ጋር ትይዩ ሆኖ የቀረበው መምህራኑ ተማሪዎቹ በጽሁፍ ተግባር እንዲበረታቱ የጽህፈት መስራ /ዎርክ ሾፕ/ ማስጠታቸው በጣም ዝቅተኛ በሆነ ስታቲስቲካዊ ልኬት የቀረበ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማበረታቻ ዘዴዎችን የተጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ ልኬት ከሚጠበቀው በጣም የወረደ ነው፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በርከት ካሉ ተለዋዋጭ የማበረታቻ ብልሃቶች ጋር መተዋወቅ ይጎድላቸዋል፤ አለያም ልዩ ልዩ የማበረታቻ ብልሃቶችን ለዋውጠው በመጠቀም ተማሪዎቹን በሚፈለገው መልኩ ለማነቃቃት ሌሎች ችግሮች ገጥመዋቸዋል የሚል ግምት ተወስዷል፡፡

***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቹ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ የአነቃቂነት ደረጃ ለማወቅ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው መረጃ መሰብሰቢያ የክፍል ምልከታ ነው፡፡ የክፍል ምልከታ መቃኛ ሆነው የቀረቡት መስፈርቶች ከክለሳ ድርሳናት በመውጣጣት ለዚህ ጥናት እንዲስማሙ ተደርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ ምልከታው የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደት በተከናወነባቸው ክፍሎች ውስጥ በአካል በመገኘት መምህራኑ ማንበብና መጻፍን እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ በማንበብና መጻፍ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ምን አይነት ማበረታቻዎችን እንደሚያካሂዱና ተማሪዎቹ እንዴት እንደሚማሩ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ተከናውኗል፡፡ እያንዳንዱን የአማርኛ ቋንቋ መምህር በመከተል ለሁለት ለሁለት ጊዜያት የክፍል ምልከታ ተካሂዷል፡፡ የክፍል ምልከታው ያተከረባቸውን***

ነጥቦች ያካተተ የምልከታ ማካሄጃ Check List በማዘጋጀት ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ የምልከታውን ሂደት ያስቃኛል፡፡

*ሰንጠረዥ 5፡ የምልከታ ሂደት ማጠቃለያ*

| ትምህርትቤት | ቀን | መማሪያ ክፍል | የምልከታ ትኩረት | የትምህርት ርእስ |
|---|---|---|---|---|
| ዲምቱ | 4/08/11 | 9C | የማንበብ ክሂል | ዲሞስቴን የምርጥ ንግግር አባት |
| አኮ | 10/08/11 | 9A | የማንበብ ክሂል | ‹‹ለወሬ ሞትኩ ይበሉ›› ምንባብ |
| ራጋ ሲባ | 11/08/11 | 9B | የማንበብ ክሂል | ዲን ሱዊፍት /የእንግሊዝ ደራሲ/ ታሪክ |
| ገበራ | 3/08/11 | 9C | የማንበብ ክሂል | ቆሻሻና አወጋገዱ |
| ዲምቱ | 15/08/11 | 9D | የመጻፍ ክሂል | አንቀጽን በተገቢ ስርአተ ነጥቦች ማሟላት |
| አኮ | 16/08/11 | 9C | የመጻፍ ክሂል | በመሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት |
| ራጋ ሲባ | 17/08/11 | 9A | የመጻፍ ክሂል | አረፍተነገሮች ምስረታ |
| ገበራ | 18/08/11 | ---- | የመጻፍ ክሂል | ታቅዶ በመምህሩ ምክንያት ያልተካሄደ |

የምልከታው መረጃ የተተነተነው በተዘጋጀው የምልከታ ማረጋገጫ ቅጽ በመደገፍ ሲሆን፣ በአራቱም ትምህርት ቤቶች በመጀመሪያ ዙር በተለያዩ ቀናት የክፍል ምልከታ ትኩረት የተደረገው በማንበብ ክሂል ሲሆን በሁለተኛ ዙር ምልከታ ትኩረት የተደረገው በመጻፍ ክሂል ላይ ነው፡፡ ምልከታዎቹን ለማካሄድ በተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ በመጠቀም ሂደቱ አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ተከናውኖ ተጠናቋል፡፡

በዚሁ መሰረት በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8 አመት አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህር የተጎበኙ ሲሆን፣ በማንበብ ክሂል ትግበራ ወቅት ሲያስተምሩ የነበረው ‹‹ዲሞስቴን የምርጥ ንግግር አባት›› በተሰኘ ርእስ ከመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 148–150 የቀረበ የምንባብ ጽሁፍ ላይ ተመስርተው ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ተዘጋጅተው የቀረቡ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡-

1) የምርጥ ተናጋሪ ጥበብ እንዴት ያለ ነው?

2) ስለ ጥንት የግሪክ ስልጣኔ አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3) ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንዴት ያሉ ጥቅሞች አሉት?
4) አንድ ንግግር የአድማጨን ቀልብ ሊስብ ወይም ላይስብ የሚችልባቸው ጉዳዮች ምንድናቸው? የሚሉ ናቸው፡፡

ምንባቡ ለመናገር ክሂል ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹ ረጅሙን የማንበብ ተግባር ከማከናወናቸው በፊት እነዚህን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ለክፍሉ ተማሪዎች ተራ በተራ በማቅረብ ከተማሪዎቹ የግል ምላሽ ቢጠብቁም ከአንድም ተማሪ ለእነዚህ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት እንደ አጥኚዋ እምነት ‹‹ዲሞስቴን የምርጥ ንግግር አባት›› የተሰኘው የምንባብ ታሪክም ሆነ ምንባቡን ቀድመው የመጡት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ችሎታ፣ ፍላጎት የመረዳት አቅም ምቹ አይደሉም፡፡

በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል መማሪያ ክፍሉ የማበረታቻ ስልት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፍ መልኩ ታቅዷል ለማለት አይቻልም፡፡ መምህሩ ይህን ስለ ግሪክ ጥንታዊ ፈላስፎች፣ ባለቅኔዎችና ሊቃውንት የሚያትት ምንባብ ከማቅረባቸው በፊት ተማሪዎቹን ለማነቃቃት የሚያስችል ከርእሱ ጋር የተያያዘ አንድ አጭር የሀገር ውስጥ ታዋቂ ግለሰብ ታሪክ ወይም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ርእስ መርጠው ቢያቀርቡ ለተማሪዎቹ መነቃቃት የተሻለ አውድ መፍጠር ይችሉ እንደነበር የአጥኚዋ ግምት ነው፡፡ በዚህ የተነሳም መምህሩ የሚያካሂዱት ማበረታቻ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ችሎታና ፍላጎት የሚመጥንና የሚያነቃቃ ካለመሆኑም በላይ ማበረታቻው ተማሪዎቹን ኅደኛ የማድረግና ችግሮቻቸውን አውቆ የመርዳት መርህ የተከተለ አለመሆኑም በምልከታው ተረጋግጧል፡፡

የማበረታቻ ስልቱ የሚሰጠውን ትምህርት አላማና ይዘት ግባዊ ከማድረግ አንጻር በቅድመ ንባብና ድህረ ንባብ ጥያቄዎች በመመርኮዝ ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ ይሁንና እንደ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ ሁሉ የድህረ ንባብ ጥያቄዎቹም ከሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የቋንቋ ልምድ የተመዛዘኑ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹በዚህ ዘመን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንደ ጥንታዊው ግሪካዊ ዴሞስቴን ተገልሎ ለብቻ በመሆን ንግግር መለማመድ አስፈላጊ ይሆናል? እንዴት?›› የሚለው ከንባብ በኋላ የቀረበ ጥያቄ በልእለ-አእምሯዊ አንብቦ የመረዳት ብልሃት ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ከበድ ያለ ጥያቄ በመሆኑ ተማሪዎቹ

ሊሳተፉበትም ሆነ ሊመልሱት አልቻሉም፡፡ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ምንባቡን ተመርኩዘው መምህሩ ቀለል ያሉ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ማቅረብ ቢችሉ መልካም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የማበረታቻ ስልቱ በተማሪዎቹ አስተሳሰብና አሰራር ላይ ተፈላጊውን አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችል መልኩ ተደራጅቷል ለማለት አልተቻለም፡፡

ማበረታቻው ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ አቅጣጫ ጠቋሚ በሆነ መልኩ የቀረበበት መንገድ አልተስተዋለም፡፡ መምህሩ በመጽሃፉ የቀረቡትን መረጃዎች ተማሪዎቹ እንዲገነዘቡ የተወሰነ ጥረት ቢያደርጉም የተማሪዎቹን መረዳት መሰረት አላደረጉም፡፡ የማበረታቻ ዘዴው በተለዋዋጭና አነቃቂ ስልቶች አልታጀበም፡፡ ለምሳሌ፡- የምንባቡን ለተማሪዎቹ ተሞክሮ እንግዳ መሆን መሰረት ባደረገ ሁኔታ አጫጭር መረጃዎችን በአሰሳና ግርፍ ንባብ እንዲያወጡ ለማድረግ ቢሞክሩ ዘዴው የተወሰኑ መረጃዎችን ፈልጎ በማውጣት እሽቅድድም ስለሚታገዝ የተሻለ አነቃቂ ይሆን ነበር፡፡

በእርግጥ የማበረታቻ ስልቱ ለተማሪዎቹ የጥንድና የቡድን ተግባራትን በማቅረብ እርስ በርስ እንዲደጋገፉ አውድ ፈጥሯል፡፡ ይሁን እንጂ በራስ መተማመንና አብሮ መስራት በአውዱ በበቂ ሁኔታ አልታየም፡፡ ይህም በተማሪዎቹ የቋንቋ እጥረት ብቻ ሳይሆን በጽሁፉ መልእክት ክብደት የተነሳ የተከሰተ ችግር መሆኑን አጥኚዋ ለመገንዘብ ችላለች፡፡

በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ተማሪዎቹ ከማንበብ ክሂል ጋር በተያያዘ የአጭር ጊዜ ግቦቻቸውን እንዲያስቀምጡ ማነቃቂያ አልተደረገም፡፡ የአጭር ጊዜ የማንበብ ክሂል ግብ ማስቀመጥ ተማሪዎቹ ለማንበብ አላማና ተነሳሽነት እንደሚፈጥርላቸው ቢታሰብም በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዚህ ወሳኝ ክሂል ማስተማሪያ የማበረታቻ አላባ ትኩረት አለመስጠታቸው የግንዛቤ ክፍተት እንዳለ አጥኚዋ እንድትገምት አድርጓታል፡፡ የማከናወንና የመቻል ስሜት እንዲሰማቸው፣ መማሪያ ክፍሉን በራሳቸው መንገድ እንዲቆጣጠሩት፣ ምኞት ተሰምቷቸው እንዲማሩ ለማድረግ መምህሩ ግፊት ሲያደርጉ ነበር፡፡ በመጨረሻም በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ትግበራ ላይ ተመስርተው ለተማሪዎቹ በክፍለ ጊዜው ማጠናቀቂያ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ተማሪዎቹ ሲያነቡ የተደረገላቸው ማበረታቻ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማሻሻልና በማንበብ ሂደት ለማነቃቃት የነበረው ጠቀሜታ በጉልህ አልታየም፡፡ ከተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ ባህሪ፣ ከመምህሩ ምንባቡን ቀለል ባለ መንገድ

የማደራጀት ዝግጅትና ትግበራ ማነስ፣ ከምንባቡ ለተማሪዎቹ ፍላጎትና ልምድ ጋር አለመገናዘብ ብሎም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ልእለ-አእምሮአዊ የማሰብ ችሎታ የሚጠይቁ ሆነው መገኘት የተነሳ የማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜው አነቃቂነት የሌለው መሆኑን ከምልከታው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል፤ በአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7 አመት አማርኛ ቋንቋ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህር የተጎበኙ ሲሆን፤ በማንበብ ክሂል ትግበራ ወቅት ሲያስተምሩ የነበረው ‹‹ለወሬ ሞትኩ ይበሉ›› የተሰኘ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 134–136 የቀረበ ምንባብ ነው፡፡ ከዚህ ምንባብ ትግበራ በፊት ቀድመው የመጡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን መምህሩ በሰሌዳ ላይ ጽፈዋል፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ፡-

- መገናኛ ብዙሃን ተብለው የሚጠቀሱት የትኞቹ ናቸው? ዘርዝሩ፡፡
- አዘውትራችሁ የምትከታተሉት የትኛውን መገናኛ ብዙሃን ነው? ለምን?
- መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ ምን ይከሰት ይመስላችኋል?
- ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
- ርእሱንና የመጀመሪያውን አንቀጽ አንብባችሁ ምንባቡ ስለምን ሊያወሳ እንደሚችል ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ገምቱ፡፡

የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ በዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምልከታ ከተተኮረበት ምንባብ በአንጻራዊ ሲቃኝ በመጽሃፉ ዝግጅት የተሻለ ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው፡፡ ከተማሪዎቹ የመገናኛ ብዙሃን ግንዛቤና ልምድ የፈለቁ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ መምህሩ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ተመስርተው የጥንድና የነጠላ ምላሾችን ለመቀበል ሲያበረታቱ ተስተውለዋል፡፡ ምንም እንኳ የተማሪዎቹን ተሳትፎ ተደራሽነት መያዝ ያልተቻለ ቢሆንም ስለመገናኛ ብዙሃን የተሻለ ግንዛቤና በአማርኛ ቋንቋ ሃሳብን ለመግለጽ የተሻለ መነቃቃት የሚያሳዩ ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ የመሰኋቸውን መልሶች አቅርበዋል፡፡

በዚህ ክፍል አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ የማበረታቻ ስልቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፍ መልኩ ታቅዶ ቀርቧል፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፉ ውስጥ በመመሪያነት ባይቀርብም መምህሩ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ በመሃሉ ማንበባቸውን ገታ አድርገው ስላነበቡት

ነገር እንዲያስቡ ሲያደርጉ መመልከት ተችሏል፡፡ መምህሩ ያካሄዱት ማበረታቻ ለተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታ የጠቀመው በተወሰነ መልኩ ነው፡፡ ምክንያቱም በቅድመ ንባብም ሆነ ከንባብ በኋላ ጥያቄዎች በመመለስ ጉልህ ሚና የነበራቸው የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ማበረታቻው አሳታፊ ወይም ሁሉን አካታች ነበር ለማለት አልተቻለም፡፡ ማበረታቻው ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን ጓደኛ የማድረግና ችግራቸውን አውቆ የመርዳት አቅጣጫን እምብዛም አልተከተለም፡፡

የማበረታቻ ስልቱ የቀረበውን ትምህርት አላማና ይዘት ግባዊ ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታ አለው ለማለት የሚቻለው ፈቃደኞች እጅ እያወጡ ተራ በተራ አንቀጾችን እንዲያነቡ (ማንበብን በየተራ እንዲለማመዱ) በማድረጉ ነው፡፡ የማበረታቻ ስልቱ በተማሪዎቹ አስተሳሰብና አሰራር ላይ ተፈላጊውን ለውጥ በማምጣት በኩል የነበረው ድርሻ ጉልህ ባይሆንም ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ዘንድ አብዛኞቹ ከተግባራቱ መድረክ በሚያፈገፍጉበትና ራሳቸውን ባለመታወቅ በሚሸሽጉበት ክፍል ውስጥ ቢያንስ የጥቂቶችን ባለ ንቁ ተሳትፎ ተማሪዎች ከማንበብ ክሂል ጋር የተያያዘ ግብር እየተመለከቱ እንደ ሞዴል እንዲወስዷቸው ለማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ በዚህ መልኩ ከታሰበ ማበረታቻው ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ በተወሰነ መልኩ አቅጣጫ ጠቋሚ ነው፡፡

የማበረታቻ ስልቱ ለተማሪዎቹ የጥንድና የቡድን ተግባራትን አቅርቧል፡፡ ነገር ግን የተመጣጠነ አቻዊ ተሳትፎ ባለመታየቱ በራስ መተማመንን እንዲያሳድጉ ጠቅሟል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በዚህ የአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምልከታ ተማሪዎቹ የአጭር ጊዜ የማንበብ ክሂል ግቦችን እንዲያስቀምጡ በቂ ማነቃቂያ በመምህሩ አልቀረበም፡፡ መምህሩ በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ማቅረቢያ ወቅት ተማሪዎቹ የመቻል ወይም የማከናወን ስሜት እንዲሰማቸው ደጋግመው ግፊት ሲያደርጉ፣ ምንም እንኳን ተገቢነቱ ላይ ተጠየቅ ያለበት ቢሆንም ጥያቄዎቹን በተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ ጭምር ተርጉመው በመቅረብ ጥያቄዎቹን መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ሲሞክሩ መመልከት ተችሏል፡፡ ከዚህም ጋር ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍሉን ድባብ በራሳቸው መንገድ እንዲቆጣጠሩትና ምቾት ተሰምቷቸው እንዲማሩ መምህሩ ጥረት ማድረግ ቢሞክሩም የተማሪዎቹ ተሳትፎ ተደራሽ አልሆነም፤ መነቃቃት የነበራቸው የተወሰኑ ባለ ገቢር ተማሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡

መምህሩ በቅድመ ንባብ ጥያቄዎችና በማስንበብ ሂደት ክፍለ ጊዜውን በማሟጠጣቸው ከንባብ በኋላ አንብቦ መረዳትን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አላቀረቡም፤ ምጋቤ ምላሽ መስጫ ጊዜም አልነበራቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ በጽሁፍ የሚመልሷቸው ንባብ ነክ ጥያቄዎች የሚገኙበትን ገጽ በመጠቆም የየግል የቤት ስራ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን አጠቃለዋል፡፡

በገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ4 አመት የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህር የተጎበኙ ሲሆን፤ እኚህ መምህር ከሌሎቹ መምህራን የተለዩ የሚያደርጋቸው የሰለጠኑት በጂኦግራፊ ትምህርት ሆኖ ሳለ አማርኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ የተመደቡ መሆናቸው ነው፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረት በዚህ ትምህርት ቤት በመኖሩ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ መምህሩ ጂኦግራፊ ትምህርት 10ኛ ክፍል ከማስተማር ጋር አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን 9ኛ ክፍል ላይ ያስተምራሉ፡፡ በማንበብ ክሂል ትግበራ ወቅት ሲያስተምሩ የነበረው ‹‹ቆሻሻና አወጋገዱ›› የተሰኘ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 121–122 የቀረበ ምንባብ ነው፡፡ ከዚህ ምንባብ ትግበራ በፊት ቀድመው የመጡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አሉ፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ፡-

1. የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትሉ ምን ምን ነገሮች ናቸው? በቡድን ተወያዩና በጋራ ውይይት አንድ አቋም ላይ ድረሱ፡፡ የደረሳችሁበትን ከምንባቡ ጋር አገናዝቡ፡፡
2. የአካባቢ ንጽህና አለመጠበቅ ምን አይነት ችግሮች ያስከትላል?
3. የግልና የአካባቢያችንን ንጽህና ለመጠበቅ ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል? የሚሉ ሲሆኑ መምህሩ በእነዚህ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ ክንዋኔ አላቀረቡም፡፡

ሁለት እቅድ የሚያዘጋጁ (ለጂኦግራፊና አማርኛ ቋንቋ) በመሆናቸው መሰላቸት የተፈጠረባቸው ይመስላል፤ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍሉ የሚሆን እቅድ አዘጋጅተው አልያዙም፡፡ የማበረታቻ ስልት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፍ ሁኔታ አልታቀደም፡፡ መምህሩ የተማሪዎቹን ችሎታና ፍላጎት የሚመጥን አንዳችም የማበረታቻ ትግበራ አላካሄዱም፡፡ የቋንቋ ትምህርቱን የሚያስተምሩት በእውቀትና በፍላጎት ሳይሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረትን ለመሸፈን ተገደው የገቡ መሆናቸው በማስተማሩ ሂደት ተንጸባርቋል፡፡ እኚህ መምህር የሰለጠኑት በጂኦግራፊ ትምህርት ሆኖ ሳለ በስልጠና ሂደት ‹‹ማይነር›› አድርገው እንኳ ባልወሰዱት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲመደቡ ማድረጉ

ተገቢ አልነበረም፡፡ አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በተደራቢነት እንዲያስተምሩ የተመደቡት በጂኦግራፊ ትምህርት የያዙት ክፍለ ጊዜ ብዛት ከሌሎቹ በማነሱ ነው፡፡

ይሁንና አማርኛ ቋንቋን ሁለተኛ ቋንቋ አድርገው ለሚማሩ ተማሪዎች ስለ ቋንቋ ትምህርት አተገባበር ምንም ግንዛቤ የሌለው የሌላ የትምህርት አይነት መምህር መመደቡ የግብር ይውጣ አይነት ስራና ለቋንቋ ትምህርቱም ሆነ ለተማሪዎቹ አለማሰብን የሚያሳይ ነው፡፡ ከእኚህ መምህር ይልቅ ለቋንቋ ትምህርት ቅርበት ካላቸው ሌሎች እንደ ኦሮምኛ ወይም እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች መምህራንን መዋስ የተሻለ እንደነበረ የንባብ ትምህርት ክፍለ ጊዜው አለምንም ማበረታቻ መተግበሩ አረጋጋጭ ነው፡፡

መምህሩ ተማሪዎቹ የሚነበበውን ጽሁፍ በየግላቸው አንብበው ቀጥሎ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ 122--123 የቀረቡ መልመጃዎችን በየግላቸው እንዲሰሩ ከማዘዝ ያለፈ አንዳችም የማበረታቻ ስልት ሲያቀርቡ አልተቃኙም፡፡ ከምንባቡ የወጡ የእውነት ሐሰት እና የምርጫ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ከሰጡ በኋላ ተማሪዎቹ ሰፊ ጊዜ የሚጠይቀውን ስራ እየሰሩ ሳለ ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል፡፡ መምህሩም የተሰጣቸውን ስራ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አጠናቀው እንዲቀርቡ በማድረግ ወጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ የገበራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የንባብ ክፍል ጉብኝት ከተቀሩት ጉብኝቶች ጋር ሲነጻጸር ያለምንም ማበረታቻ የተካሄደ የንባብ ክፍለ ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ማበረታቻ ማካሄድ ቀርቶ በቅድመ ንባብ የቀረቡ ጥያቄዎችን እንኳ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ እንዲያጤኗቸው ለማድረግ እሾት ባለማሳየታቸው መምህሩ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ራሳቸው ተነሳሽነት የሌላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሲጠቃለል፤ በአኮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህሩ የቀረበው የማንበብ ክሂል ትምህርት ከዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትግበራ ሲነጻጸር ለተማሪዎቹ ልምድ፣ ግንዛቤ የሚመጣጠን፣ የተማሪዎችን ልእለ-አእምሯዊ አንብቦ የመረዳት ብልሃት እምብዛም የማይጠይቅና ቀለል ያለ በመሆኑ ተሳትፎ የሚጋብዝ ነው፡፡ የተማሪዎቹ ተሳትፎና መነቃቃት ግን አጥጋቢ ነበር ለማለት አያስደፍርም፡፡ መምህሩ ተሳትፏቸው የሰመረ እንዲሆን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ጭምር ተጠቅመው ማብራሪያ ለመስጠት ሙከራ ቢያደርጉም የክፍለ ጊዜውን የማንበብ ክሂል ክንዋኔዎች ሲቆጣጠሩ የነበሩት የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ በመሆናቸው አሳታፊና አነቃቂ የማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ‹መምህሩ እኔ ዘንድ ደርሶ ጥያቄ ይጠይቀኛል› በሚል ፍርሃት ይመስላል፤

ራሳቸውን ለመሸሸግ ሲሞክሩ የነበሩ ተማሪዎች ሁኔታ በመምህሩ ችላ የተባለና የማንበብ ክፍለ ጊዜው ትምህርት ከሞላ ጎደል የተሻለ የሚንቀሳቀሱትን ጥቂት ተማሪዎች ያማከለ ነበር፡፡

በራጋ ሲባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2 አመት አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህር የተጎበኙ ሲሆን፣ በማንበብ ክሂል ትግበራ ወቅት ሲያስተምሩ የነበረው ‹‹ዲን ሱዊፍት›› በሚል ርእስ በመማሪያ መጽሐፉ በገጽ 154 የቀረበ የአንድ የእንግሊዝ ደራሲ በጣም አጭር ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩ አዝናኝ ገጽታና በጣም አጭር ጭብጥ ያለው ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፋቸውን ወደ ክፍል ይዘው ባለመምጣታቸው የማንበብ ትምህርቱ በውቅቱ በክፍሉ ለተገኙት 56 ተማሪዎች 7 መማሪያ መጻህፍት ላይ መወሰን ግድ ያለ ነበር፡፡ ማበረታቻ ተማሪዎቹን ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ከማዘጋጀት ይጀምራል፡፡ መምህሩ በማንበብ ክፍለ ጊዜው ዋዜማ ስለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ምንነት በመግለጽ ተማሪዎቹ አስፈላጊውን የትምህርት ግብአት ይዘው እንዲገኙ ባለማዘጋጀታቸው የተነሳ 56ቱን ተማሪዎች በ7ቱ መማሪያ መጻህፍት መደልደሉ ራሱ ጊዜ አባካኝ ነበር፡፡

ከዚህ ምንባብ ጋር የተያያዙ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሐፉ አልቀረቡም፣ በመምህሩም ይህን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ዝግጅት አልነበረም፡፡ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ ከማንበብ ክሂል ጋር የተያያዘ የማበረታቻ ስልት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያነቃቃ መልኩ ታቅዶ አልቀረበም፡፡ ተማሪዎቹ በአንድ መማሪያ መጽሐፍ 8 /ስምንት/ ሆነው በማትኮር በአንድ መጽሐፉን የተቆጣጠረ ተማሪ ሲነበብ ሌሎች ያዳምጡ ነበር፡፡ እንዲህ እየተደረገ ሁለት ሦስት ተማሪዎች ወረፋ አግኝተው አጭሩን የ‹‹ዲን ሱዊፍት›› ታሪክ በቻሉት መጠን ሲያነቡ ከቆዩ በኋላ ክፍለ ጊዜው ከመጠቃለሉ አስቀድሞ የነበረው ጊዜ በማንበብ ክንውን ሳይሆን በግል ወሬና ጫጫታ የታጠረ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ብዙ ተማሪዎች ሆነው አንድ መጽሐፍ በመጋራት የሚያደርጉት ማንበብ ክፍለ ጊዜው በስርአት እንዳይመራ ተጽእኖ አድርጓል፡፡ በመጨረሻ የተረፈችውን ስድስት ደቂቃ መምህሩ ምንባቡን ራሳቸው በማንበብ ለክፍሉ ተማሪዎች መልእክቱን በማብራራት አጠናቀቁ፡፡ በዚህ አይነቱ ተማሪዎችን በተደጋጋሚ የሌሎች ተማሪዎችና የመምህሩ አዳማጭ ባደረገ መማሪያ ክፍል ተማሪዎቹ የአዳማጭነት እንጂ የአንባቢነት ተሳትፎ ይኖራቸዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡

ለተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታ የሚመጥን ከማንበብ ክሂል ጋር የተያያዘ ማበረታቻ አልቀረበም፡፡ ተማሪዎቹን ጓደኛ ያደረገና ችግራቸውን አውቆ የመርዳት መርህን የተከተለ ማበረታቻም አልቀረበም፡፡ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ አላማና ይዘት ግባዊነት ጋር ትይዩነት ያለው ማበረታቻ ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም መምህሩና ጥቂት ተማሪዎች ብቻ በሚያነቡበት ክፍል ውስጥ ሌሎች አዳማጭ ከሆኑ ማንበብ ተተግብሯል ለማለት አያስችልም፡፡ ይህ አይነቱ ተሞክሮ በተማሪዎቹ አስተሳሰብና አሰራር ላይ ተፈላጊውን አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ያለው ቁብ ያነሰ ነው፡፡

በራጋ ሲባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማንበብ ክሂል የሚመጥን ማበረታቻ ባለመደረጉ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ አቅጣጫ ጠቋሚ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተለዋዋጭና አነቃቂ ስልቶች የታጀበ የማንበብ ክሂል ማነቃቂያም አልታየም፡፡ ለተማሪዎቹ የቡድን ተግባር በመስጠት በራስ መተማመንን እንዲያሰድጉ መደረግ የነበረበት ጥረትም በስህተት አተገባበር ላይ የተመሰረተና አንድ አንባቢ ሌሎች ከሰባት ያላነሱ ተማሪዎችን በተገብሮ አውድ አዳማጭ ያደረገ ነው፡፡

እንደ ሌሎቹ ምልከታው ያዳረሳቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ በራጋ ሲባም ተማሪዎቹ የአጭር ጊዜ የማንበብ ክሂል ግብ አስቀምጠው እንዲንቀሳቀሱ ተገቢው ማነቃቂያ አልተደረገም፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍሉን ድባብ በራሳቸው መንገድ እንዲቆጣጠሩት ቢያደርጉም የማንበብ ክፍለ ጊዜውን ተማሪዎቹ ለማንበብ ክንዋኔ በአግባቡ እንዲቆጣጠሩት የአመራር ሚናቸውን በአግባቡ አልተወጡም፡፡ ከሌሎቹ ምልከታው ያካለላቸው ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ልምድ አንጻር ሲታይ የራጋ ሲባው የአማርኛ ቋንቋ መምህር የማስተማር ተሞክሮ ዝቅተኛ ነው፡፡ ክሂል የማስተማር ግንዛቤ ማነስና የክፍል አመራር ልምዳቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት ያስደፍራል፡፡ ለአብዛኞቹ ተማሪዎች በእድሜ የቀረቡ ወጣት መምህር በመሆናቸው ይመስላል ተማሪዎቹን ተገቢ የመማሪያ ክፍል ባህሪና ባህል እንዲይዙ ተጽእኖ ለማድረግ ሲቸገሩ ታይተዋል፡፡

በገበራ የተኀበኘው የንባብ ክፍለ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ መምህር ሳይሆን የጂኦግራፊ ትምህርት ስልጠና ባላቸው መምህር የተያዘ መሆኑ በፈጠረው ችግር እንኳን የንባብ ክፍለ ጊዜን በማበረታቻ ብልሃቶች አስደግፎ ለማስተማር ይቅርና የንባብ ክሂል ትምህርቱ የሚጠይቃቸው ክንውኖች በተገቢ የማስተማሪያ ብልሃቶች አልተደገፈም፡፡ ይህ ችግር

በመጻፍ ክሂል ትምህርት ምናልባት ለውጥ ይኖረው ይሆን ብላ በማሰብ አጥኚዋ የጂኦግራፊ መምህሩን ጽህፈት በሚያስተምሩበት ክፍል ለመነብኘት ላቀረበችላቸው ጥያቄ ፈቃደኛነት ባለማሳየታቸው ጉብኝቱ ቀርቷል፡፡

በሌላ በኩል፤ በመጻፍ ክፍለ ጊዜያት የተደረጉት ምልከታዎች ውጤቶች ከማንበብ ክሂል ምልከታዎች ውጤቶች የተሻለ ወይም ተመጣጣኝ ተሞክሮ የሚታይባቸው ሆነው አልተገኙም፡፡ የመጻፍ ሂደት ለሁሉም ተማሪዎች ውስብስብና ከአረፍተ ነገር በዘለለ እንደ አንቀጽና ድርሰት መጻፍ ያሉ የተማሪዎቹን የአፍላቂነት ችሎታ ለሚጠይቁ ክንውኖች ተማሪዎቹ በአብዛኛው ድፍረትና ተነሳሽነት የሌላቸው ናቸው፡፡ የተማሪዎቹ ዋናው ችግር ለመጻፍ ክሂልና መጻፊያ አውዱ ግብአት የሆኑ ተገቢ ቃላትን በተገቢ ሁኔታ አፍልቆ ለመጻፍ መቸገር ነው፡፡ የተተገበሩት የመጻፍ ክሂል ትምህርቶች በቀረቡ ቃላት አረፍተነገሮች መመስረት፣ አያያዥ ቃላትን በአግባቡ በመጠቀም አረፍተነገሮች ማዋቀርና በቀረበ አንቀጽ ውስጥ ተገቢ ስርአተነጥቦችን በየቦታቸው ማስገባት ቢሆንም በተማሪዎቹ ተሳትፎ ዲምቱ ሁለተኛ ደረጃ በአንጻራዊ የተሻለ ከሚባል በስተቀር (ምክንያቱም በግድግዳ ላይ የተለጠፈ የስርአተ ነጥቦች ቻርትን በመጠቀም ጭምር በአንቀጽ ውስጥ ባሉ ክፍት ቦታዎች ስርአተ ነጥቦችን ማስገባት ስለነበር) በሌሎቹ የምልከታ አውዶች የጽሁፍ ትግበራዎቹ ቃላትን በተገቢ ሁኔታ ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት ለብዙ ተማሪዎች አዳጋች ክንውን እንደነበር ተቃኝቷል፡፡

ለአማርኛ ቋንቋ በተሰጠው ማህበራዊ ተግባቦታዊ ትኩረት ማነስ፣ ከሌሎች የትምህርት አይነቶችና የቋንቋ ትምህርቶች ጋር ሲነጻጸር ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በበርካታ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል የባሰ ተጽእኖ እንዲያርፍ ማድረጉን አጥኚዋ የክፍል ምልከታዎችን ተከትላ ለአንዳንድ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጥያቄ በማቅረብ መረጃ አግኝታለች፡፡ ስማቸውን አስተካክለው መጻፍ የማይችሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዳሉም ደብተሮቻቸውን በመመልከት አረጋግጣለች፡፡ በምልከታው አውድ ተደግፋ ለሙከራ ያህል ሙሉ ስማቸውን በአማርኛና በኦሮምኛ ቋንቋ ጽፈው እንዲሰጧት ካደረገቻቸው 5 የ‹‹X›› ትምህርት ቤት (ስሙን አለመግለጽ የጥናቱ መረጃ መርህ መሆኑን ልብ ይሏል) ሴት ተማሪዎች መካከል በአማርኛ የቀረቡት ስሞች ከኦሮምኛ ጋር ትይዩ ሆነው የተገኙት የ3ቱ ብቻ ናቸው፡፡ ከሁለተኛ ቋንቋ ተጽእኖው በላይ በተማሪዎቹ የመጻፍ ልምድ ላይ ተጽእኖ ያደረገው በአማርኛ ቋንቋ ፊደል መጻፍ

የጀመሩበት ጊዜና ለመጻፍ ክሂል በቂና ተገቢ ተጋልጦ ማጣት እንደሆነ አጥኚዋ መላምታዊ ግምቷን አስቀምጣ ማለፍ ትወዳለች፡፡

ይህም Rivers (2008) እንዳሉት፤ ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ የሚገለገሉበት ሰፊ አጋጣሚ የላቸውም፡፡ በዚህም የተነሣ በቋንቋው የመጠቀማቸው ሁኔታ በአብዛኛው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተወሰነ ነው፡፡ ሆኖም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቻ የሚያገኙት ትምህርት ቋንቋውን አቀላጥፈው ለመጠቀም ስለማያበቃቸው ለአጠቃቀም ችግር ሲጋለጡ ይስተዋላል፡፡ ተማሪዎቹ ችግራቸውን አቃልለው የቃላት ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በራሳቸው ጥረት ቃላትን መማራቸው ወሳኝ ነው፡፡ ይህ የሚሆነውም ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ለመርዳት እንዲችሉ በሚያደርጉ ብልሃቶች የተደገፈ ትምህርት ሲያገኙ ነው የሚለውን ገለጻቸውን እንድናስታውስና ችግሩን ለማቃለል መኬድ ያለበትን አቅጣጫ እንድንመርጥ ግድ የሚል ነው፡፡

## 4.5 የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

**በመጀመሪያ ደረጃ በተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት ተሰብስበው ከፍ ሲል የተተነተኑት መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች እርስ በርስ ተደጋጋፊ እና አንዱ ሌላውን አጠናካሪ በሆነ መንገድ ችግሩን ለማብራራት የረዱ መሆናቸውን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡**

በዚህ መሰረት በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማበረታቻ ስልቶች ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በጓደኛዊ ስሜት እንዲማሩ ማድረጉ፣ የጥንድና የቡድን ተግባራትን ያካተተ መሆኑ፣ የማበረታቻ ስልቶቹ በተማሪዎች መካከል የመተባበርና የመረዳዳት ስሜት መፍጠር ያስቻሉ መሆናቸው፣ ክፍሉን በራሳቸው መንገድ እንዲጠቀሙበት ወይም እንዲቆጣጠሩት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጠቀሜታ ያለው መሆኑ የተሻለ ትኩረት የተሰጣቸው መሆናቸውን መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ማጠቃለል የሚቻለው በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የሚደረጉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማበረታቻ ስልቶች ከተናጠል ይልቅ በቡድን አቋም ላይ ያተኮሩ፣ ተማሪዎቹ በህብረት እንዲሰሩ የሚያደርጉ የአቻ ክንውኖችንና በሚደጋገፍ የመማማር ብልሃቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡ እነዚህ በቡድን ቁመና ላይ ያተኮሩ የማበረታቻ ስልቶች ተማሪዎቹ እርስ በርስ መረዳዳትንና አቻዊ ተስተምህሮን የሚያጠናክሩ ናቸው፡ ይሁንና የአጽንኦቱና ተደራሽነቱ መጠን (ẍ = 3.47) ብቻ መሆኑ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የተጠናከረ የማበረታቻ ትግበራ መኖሩን አያሳይም፡

በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን ተከታታይነት ባለው አኳኋን አያካሂዱም፡ የመምህራኑ ማበረታቻ አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ

እንዲማሩ ያደረገላቸው አስተዋጽኦ ያን ያህል ጉልህና ተደራሽ አይደለም፡ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የፈጠረላቸው የመማሪያ መድረክ በተማሪዎቹ ዘንድ የፈጠረው አዎንታዊ አመለካከትና የተነሳሽነት ስሜት ጉልህ አይደለም፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአብዛኛው ለተማሪዎቹ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የትምህርት ግቦችን እንዲያስቀምጡ በማድረግ ላይ ያተኮረ አይደለም፡ ምንም እንኳ የማበረታቻ ትልቁ ጠቀሜታ ከሚሃ ትምህርቱ አላማዎችና ይዘቶች ጋር በተገናዘበ መልኩ ተማሪዎቹ ሊደርሱበት የሚገባቸውን የትምህርት ግቦች በየጊዜው እያስቀመጡ ወደእነዚህ የታቀዱ ግቦች ለመድረስ የሚያስችሉ ልምምዶችን መተግበር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ቢሆንም የማበረታቻ ስልቱ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች የሚያሳዩት በጣም ዝቅተኛ ትኩረትን ነው፡

ከሁሉም በላይ፤ የቋንቋ ተማሪዎች የራሳቸውን ግቦች በማስቀመጥና በሚጠበቁት ውጤታማነት አቅጣጫ የራሳቸውን የአጠናን ስልቶች በመቀየስ ውጤታማ ለመሆን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው በማዘዝ፣ የቋንቋ መማር ፍላጎታቸውን በመወሰንና ለምን ቋንቋውን እንደሚማሩ በማወቅ ትምህርታዊ ግባቸውን ሊያሳኩ ይችላሉ (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ ከቋንቋ ትምህርቱ የሚጠበቁትን ቁምነገር ለይቶ ማወቅና ግቡን ማየት ወደ ማበረታታት ይመራቸዋል፡፡ ይህም በበኩሉ ከፍ ወዳለ የቋንቋ ብቃት ያደርሳቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው እንደ ከተናጋሪዎቹ ጋር በበቂ ሁኔታ ተግባቦት ማካሄድ፣ በቋንቋው የተጻፉ መጽሀፍትን በትክክል ማንበብና አገናዝቦ መጻፍ የመሳሰሉ የተወሰነ የአጭር ጊዜ ግብ አስቀምጠው በመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲሳተፉ ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል (Ushioda, 2012)፡፡ ይሁንና በተለያየ መንገድ የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ጥናቱ የደረሰበት ውጤት የሚያመለክተው ተማሪዎቹን ለማበረታታት አይነተኛ ጠቀሜታ ያለው የአጭር ጊዜ የትምህርት ግቦችን እንዲያስቀምጡ አድርጎ ማስተማር በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ትኩረት አልተሰጠውም፡ ይህ ባለመሆኑም ተማሪዎቹ ከቋንቋ ትምህርቱ የሚጠበቁትን ወይም የሚደርሱበትን ግብ ለይተው በማወቅ ሊነቃቁ አይችሉም፡

***ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው፤ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ክፍሎቻቸው ተማሪዎቹን ለማበረታታት ልዩ ልዩ ቴክኒካዊ ድጋፎችንና ግፊቶችን ማድረጋቸውን ነው፡፡ ማበረታቻ በቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦም በአብዛኛው ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም በማበረታቻ አስፈላጊነት የአመለካከት ችግር ያለባቸው መምህራን የሉም፡፡ ለምሳሌ ማበረታቻ አላካሄድም፤ ወይም ደግሞ ማበረታቻ ለክፍለ ጊዜው ያዘጋጀሁትን ትምህርት የመተግበሪያ ጊዜዬን ይሻማብኛል የመሳሰሉ አስተያየቶች አልቀረቡም፡፡ እንደ መምህራኑ ግንዛቤና ልምድ ይነስም ይብዛ የሚያውቋቸውን የማበረታቻ ስልቶች ለመጠቀም መሞከራቸው መልካም ነው፡፡ የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን ከአማርኛ ቋንቋ ማስተማርያ አውድና ልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር አስማምተው ማቀድና መተግበር የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ፤ ሊኖር የሚችለው ክፍተት***

**ተለዋዋጭ የማበረታቻ ብልሃቶች ግንዛቤ እንደሚሆን አጥኚዋ ከቃለመጠይቁ ተሳታፊዎች ምላሾች ተረድታለች፡፡**

ስለመጻፍ ክሂልና የማበረታቻ ስልት በቀረበት ስታቲስቲካዊ ልኬቶች የተተነተኑትን መረጃዎች መሰረት አድርጎ ለመናገር የሚቻለው፤ ምንም እንኳ ከመጻፍ ክሂል ጋር ተያይዞ ለተማሪዎቹ የሚቀርበው ማበረታቻ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም፤ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ከመጻፍ ጋር የተያያዙ የማበረታቻ ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ጨርሶ አይተገብሩም ለማለት አያስችልም፡፡ መጠኑና ተደራሽነቱ ላይ ጥያቄ ያለበት ቢሆንም በቅደም ተከተል፤ ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ተገቢ መመሪያ መስጠት፣ የአማርኛ ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአትንና መዋቅርን እንዲጠብቁ የሚያለማምዱ መሆኑ፣ በየጊዜው የጽህፈት ክንውኖቻቸውን በማረም ተማሪዎቹን የሚያበረታቱ መሆኑ፣ በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ ለተማሪዎቹ የሚደረግላቸው ማበረታቻ ለልምምድ የሚሆኑ ክንውኖችን መስጠቱ፣ በመጻፍ እንዲበረታቱ የሚያደርጉት ማበረታቻ ተማሪዎቹ ስህተቶቻቸውን እያረሙ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ የረዳቸው መሆኑ የተጠኚዎቹን አንጻራዊ የተሻለ ምልከታ ያገኙ አመላካቾች ናቸው፡ ከሁሉም በበለጠ ከመጻፍ ክሂልና የአማርኛ ቋንቋ ማበረታቻ አሰጣጥ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች ሆነው ሊታዩ የሚባቸው ሁኔታዎች፤ መመሪያ ክፍላቸው በአብዛኛው በመጻፍ ክንዋኔ እንዲበረታቱ አዎንታዊ ግፊት ፈጣሪ አለመሆኑ፣ ተከታታይነት ባለው መልኩ የድርሰት መጻፍ ሥራ እንዲያደርጉ የሚደረገው ማበረታታት በጣም አነስተኛ መሆኑ፣ በመጻፍ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረገው ማበረታቻ በቂ አለመሆኑ፣ ተማሪዎቹ ደጋግመው እንዲጽፉ በማድረግ ተከታታይ በሆነ መልኩ ምጋቤ ምላሽ አለመስጠቱ ናቸው፡

ተማሪዎች መጻፍን ደጋግሞ በመጻፍ መለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ የቋንቋ ዳራ፣ ልምድ ጋር በተገናዘበ መልኩ በየጊዜው በመጻፍ ክንዋኔ እንዲበረታቱ አዎንታዊ ግፊት መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የድግግሞሽ ስልት ስህተት እየፈጸሙ እየታረሙ መጻፍን በመለማመድ የመቻል ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ተከታታይነት ባለው መልኩ የድርሰት መጻፍ ሥራ እንዲያደርጉ የሚደረገው ማበረታታት በጣም አነስተኛ በሆነበት የሁለተኛ ቋንቋ መመሪያ ክፍል በቂ ልምምድ ስለማይኖር ተማሪዎቹ ራሳቸውን የቻሉ ጸሃፊዎች ለማድረግ የተቀመጡት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ግቦች ማሳካት አስቸጋሪ ነው፡ አልፎ አልፎ በገሃድ እንደሚስተዋለው በአማርኛ ቋንቋ በበቂ ሁኔታ መጻፍ የማይችሉ 10ኛ ክፍል የጨረሱ ተማሪዎች መኖር መመሪያ ክፍላቸው በአብዛኛው በመጻፍ ክንዋኔ እንዲበረታቱ አዎንታዊ ግፊት ፈጣሪ ካለመሆኑ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ የድርሰት መጻፍ ሥራ እንዲያደርጉ የሚደረገው ማበረታታት እንደሚጠበቀው ጠንካራ ያለመሆኑ ውጤቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡

እንደ Ackner (2011) ገለጻ፤ መምህራን ተማሪዎቹ በመጻፍ እንዲበረታቱ እንደ ተማሪዎቹ ሁኔታ እና እንደ ትምህርቱ ግብ ተለዋዋጭ አሰራር ላይ መመርኮዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ስልታዊ እና ብዙ ቁምነገሮችን የሚያሰላስሉ መሆንም ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጻፍ ተግባርን ለማቀናጀት ማቀድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የሚቀደው ጉዳይ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ልምድ፣ ፍላጎት እና ከአጠቃላይ መማሪያ ክፍሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎቹ ወደፊት ራሳቸውን ችለው መጻፍ እንዲችሉ የሚያበረታታ የመማሪያ ክፍል መፍጠርና የተማሪዎቹን የጽሁፍ ክንዋኔ ማስተባበር ያስፈልጋል፡፡

ከቀረቡት ስታቲስቲካዊ መረጃዎች አንጻር ማጠቃለል እንደተቻለው በመጻፍ ክሂል ዙሪያ በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚደረገው ማበረታቻ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝና ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የተሻለ መነቃቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ ጠቀሜታው ያነሰ ነው፡ የመጻፍ ክሂል በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የመጻፍ ክሂል ሀሳብን ለማስወጣት፣ ልምድን ለማዳበርና አዳዲስ ሀሳቦችን ለመግለጽ ወይም ሀሳብን በማይደበዝዝና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌላ ወገን ለማቆየት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ሆኖ ለማግኘት በተለይም ደግሞ በተማሪው ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ቁልፍ ድርሻ አለው፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች በተለያዩ የመጻፊያ አውዶችና ርእሰ ጉዳዮች አያይዘው በተደጋጋሚ እንዲጽፉ እድል ካልተሰጣቸው፣ በተለይ ደግሞ ደጋግመው እንዲጽፉ በማድረግ ተከታታይ በሆነ መልኩ ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣቸው ያልተደረጉ ተማሪዎች በገሃዱ አለም ለሚጠብቃቸው የመጻፍ ክንውን ሊዘጋጁ አይችሉም፡ ተማሪው አስረኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ መልእክት ለማስተላለፍ የሚቸገሩና የሌሎችን እርዳታ የሚጠይቁ ወጣቶች አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ ከመጻፍ ጋር በተያያዘ ማበረታታት፣ በቂ ልምምድ፣ ድግግሞሽና ተገቢ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ማነስ ውጤቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ መምህራን ስለሚያደርጉት ማበረታቻ በቃለመጠይቅ የተገኙት አይነታዊ መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች አጠቃላይ ይዘት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ከማንበብ ክሂል ሲነጻጸር ለመጻፍ ክሂል መሳ ለመሳ የሆነ ወይም የተሻለ ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎቹን በመጻፍ ክሂል አያበረታቱም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የመጻፍ ሂደት ከሌሎች ክሂሎች አንጻራዊ ክብደት ያለው፣ የአመንጪነት ችሎታን የሚጠይቅና ውስብስብነት የሚታይበት መሆኑ ሲሆን በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ክሂሉን ለማበረታታት ተማሪዎቹ ተገቢው ዝግጁነት ያንሳቸዋል፡፡ Richards እና Renandya (2012) እንዳቀረቡት፤ በእርግጥም የጽህፈት ክሂል ተማሪዎቹን ማስጨበጥ ከሁሉም ክሂሎች ይልቅ አዳጋችነት ጎልቶ የሚታይበት ክሂል ነው፡፡ አዳጋችነቱም ሃሳብ አመንጭቶና ተገቢ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ በማቅረብ ላይ ብቻ ያረፈ አይደለም፡፡ ቃላትን በማቀነባበር፣ በማዋሃድና በተገቢ መንገድ ስርአተ-ነጥቦችን በመጠቀም ተነባቢ (legible) ጽሁፍ ማቅረብ ስለሚሳናቸው ጭምር ነው፡፡

ከመርሃ ትምህርቱ አላማዎችና ይዘቶች የመነጨትን የመጻፍ ክሂል ተግባራትን ከተገቢ የማበረታቻ ብልሃቶች ጋር አቀናጅቶ ለመከወን ተማሪዎቹ በቂ የቃላት ግብአቶችን ለመጻፍ ክሂል ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ውስጥ ለመጠቀም የሚበቃ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት የላቸውም፡፡ የዚህ ተጽእኖ ምንጭ ሁለት ጉዳዮች ናቸው፡፡ አንደኛው ተጋልጦ ማጣት ነው፡፡ የቋንቋ አመለካከትና የቋንቋ እቅድን ጨምሮ በተለያዩ ዳራዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ መጻፍ ከዚህ ቀደም የነበራቸው ተጋልጦ በእጅጉ የተገደበ ነው፡፡ በዚህና በሌሎችም የተማሪዎቹ ስነልቦናዊ ዝግጅቶች ማነስ ለአማርኛ ቋንቋ ቃላትና ጽሁፍ ተገቢ ትኩረት ሰጥተው በበቂ ሁኔታ ባለመለማመድ አሁን የደረሱበት ክፍል ደርሰዋል፡፡

የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ለሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት መዳበር መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ተማሪዎች መማር ያለባቸው ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት ለምን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸውም ጭምር በክፍል ውስጥ መለማመድ አለባቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች እውቀትና ልምድ እየዳበረ ሲሄድ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ቃላትን ለመማር ስለሚያግዛቸው ነው (Bereiter እና Scardamalia 2007)፡፡

በቂ ተጋልጦ ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ ልምድ መሰረት እንደሆነ ቢታመንም፤ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለመጻፍ ግብአት የሚሆኗቸውን ቃላት አውቆ አለመገኘት አሁን በሚገኙበት ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መጻፍን ዘላቂነትና ተደራሽነት ባለው መልኩ ለመተግበርም ሆነ ለማበረታታት እንቅፋት ሆኖ መገኘቱን አይነታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህን ችግር በመፍትሄ አስደግፎ ወደ ተሻለ ሁኔታ ለማምጣት ውስብስብ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የፊደላት ቅርጽን፣ ቃላትንና አረፍተነገሮችን በማስተማር ተገድበዋል፡፡ እንደ አንቀጽና ድርሰት የመሳሰሉትን ከፍ ያለ አእምሯዊ ክንውን የሚጠይቁ ተግባራት እምብዛም የሚሞከሩ አልሆኑም፡፡ ይህም የተማሪዎቹን በቀደሙት የትምህርት እርከኖች በአማርኛ ቋንቋ መጻፍ በቂ ተጋልጦ እያገኙ መጻፍን በበቂ ሁኔታ ካለመለማመድ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡

ሌላው መርሃ ትምህርቱ ለአማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሰጠው ትኩረት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የክልል ቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያነት የሚያበቃው 8ኛ ክፍል ላይ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ለሁለተኛ ደረጃ በብሄራዊ ደረጃ የሚዘጋጀው መርሃ ትምህርት አንድ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መማር የሚጀምሩት 5ኛ ክፍል ሲደርሱ ፊደል መማር በመጀመር ነው፡፡ አንዳንድ የጥናቱ መረጃ አቀባይ መምህራን እንደሚጠቁሙት መማሪያ መጽሃፉ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ መማር ልምድ ያገናዘበ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከአፍ ፈቶች ወይም አማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ መማር ከጀመሩት ጋር በአንድ መማሪያ መጽሃፍ ይማራሉና፡፡ ይህ ችግር ውስብስብ በሆነው በመጻፍ ክሂል ጎልቶ የሚታይና በማበረታቻ ብልሃቶችም ለማቃለል የሚያዳግትና ከመማሪያ መጽሃፉ የዝግጅት ክፍተት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሁለንተናዊ መልኩ ለማንበብ ማበረታቻ የተሻለ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን በዋንኛነት ደግሞ የማንበብ ክንዋኔን ለመጻፍ መነሻ ማድረጋቸውና ማንበብን ከመጻፍ ጋር አቀናጅተው ማስተማራቸው አጽንኦት የተሰጣቸው ከማንበብ ክሂል ጋር የተያያዙ ጠንካራ ማበረታቻዎች ናቸው፡ ጠንካራ የሚያሰኛቸውም የማንበብ ክሂልንም ሆነ የመጻፍ ክሂልን በጥምረት ለማበረታታት ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው ነው፡ በማንበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ተገቢ መመሪያ ከመምህራቸው የሚሰጣቸው መሆኑም በተጠኚዎቹ በዋንኛነት የተጠቆመ ማበረታቻ ነው፡ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚጠቆመው ለቀረበው ጽሁፍ ተገቢ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት ለመምረጥና የማንበብ ተግባሩን ለመቆጣጠር በመሆኑ ቀጣይ በሆነ መልኩ በዚህ አይነት ልምምድ ውስጥ ያለፉ ተማሪዎች ምን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ፤ ማንበብ በተለያየ ሁኔታ መጻፍን እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል ልምድ ለማግኘት የሚረዳ፣ ተማሪዎች አሳማኝ በሆነ ስልት ጽሁፍን ለመቀናበር እንዲችሉ አቅጣጫ እና አላማ የሚያመላክት መንገድ ነው፡ በመሆኑም፤ ተማሪዎቹን በተወሰነ መልኩ የሚያታግል ስራ መስጠት ተገቢ ነው፡ ተማሪዎች ከቀረበው ነገር ሊማሩ የሚችሉት ሊሰሩት የሚችሉት ነገር ግን በተወሰነ መልኩ ጥረታቸውን በሚጠይቅ ተግባር ሲሳተፉ ነው (Bunn, 2011)፡፡ ለተማሪዎቹ በቂ የማንበብና መጻፍ የልምምድ ጊዜ መስጠት ተገቢ ነው፡ ተማሪዎቹ ወደቤት ተመልሰው እንዲያነቡና እንዲጽፉ ከማድረግ ይልቅ የሚሻለው የመማር ማስተማሩ ሂደት በሚካሄደበት በክፍል ውስጥ በቂ ጊዜ በመስጠት ማለማመድ ተገቢ ነው (Greene, 2012)፡፡

መምህራኑ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ልምድና ፍላጎት የተዛመዱ ተግባራትን ማቅረብ ያለባቸው መሆኑን ማንዘባቸው የሚበረታታ ቢሆንም የድጋፉ መጠን የጎለበተ ሆኖ አይገኝም፡ የማበረታቻ ዋንኛ አጽንኦት ታላሚ ማበረታቻ ተቀባዮችን ፍላጎት፣ ልምድና ችሎታ መሰረት አድርጎ መመቻቸቱ ሲሆን ይህም ለማቃቃት ትልቁ መሰረታዊ

ሁኔታ ነው፡ ይሁን እንጂ የማበረታቻ ስልቶቹ ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ልምድና ፍላጎት ያላቸው ተዛምዶ ከስታቲስቲካዊ ማሳያዎቹ አንጻር ተደራሽነት አለው ለማለት አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል፤ ማበረታቻ ተማሪው በመማር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሚከናወን ከሆነ ተማሪውን ካለመቻል፣ ተናዳጅነትና ሀፍረት በማላቀቅ በድርጊትና ደጋግሞ በመሞከር መማርና መለማመድ እንዲችል፣ በአጠቃላይ የመማሪያ ስልቶችን እንዲማር ሊያበረታታው ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረግላቸው ማበረታቻ በመማር ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለማቃለል ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚጠቁሙ ቢሆንም፤ የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ ናቸው ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚደረጉላቸው ማበረታቻዎች ተማሪዎቹ ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን ለይተው በማወቅ እንዲማሩ ማድረጉም እንዲሁ ገደቦች ያሉበት ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ኃላፊነት መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎች ስለራሳቸው መማር ኃላፊነት ከጎደላቸው ተሳትፎአቸው፣ መነቃቃታቸው፣ ለማወቅ የሚያደርጉት አጠቃላይ ጥረት የተገደበ፣ የሚጨብጡትም ቁምነገር ያነሰ መሆኑ የማይቀር ነው፡ ከዚህ አንጻር የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በኃላፊነት መውሰድ እንዲያከናውኑ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ባይካድም የጉልህነት ደረጃው ውሱን ነው፡

**የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመጻፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ክፍል ውስጥ የሚያካሂዷቸው የማበረታቻ ስልቶች ዘለቄታማነት ክሂሉን ለማስረጽ በጣም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ በርካታ አጥኚዎች ይስማማሉ፡፡ በቃለመጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ከማንበብ ጋር የሚስማሙ ማበረታቻዎችን ለመተግበር በተወሰነ መልኩ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የሚተገብሯቸው የማንበብ ማበረታቻዎች የተማሪዎቹን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል የተወሰነ ድጋፍ ቢኖራቸውም ቀደም ሲል ከመጻፍ ጋር በተያያዘ በቀረበው ትንተና ለማመልከት እንደተሞከረው ከተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ዳራ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ጨምሮ፤** ሁሉንም ተማሪዎች በማንበብ ለማሳተፍ በየመማሪያ ክፍሉ ማንበብ አዳጋች የሚሆንባቸው ተማሪዎች እንደሚያጋጥሟቸው፣ የቃላትን ትርጉም ሳይረዱ የሚያነቡ ተማሪዎች መኖራቸው፣ አልፎ አልፎ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ ፍላጎት የሚያሳዩ፣ አይገባኝም ብለው ተስፋ የሚቆርጡ ቋንቋውን አስተካክለው መናገር የማይችሉና የማንበብ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ሁኔታ ብርቱ ትኩረት የሚጠይቅ ነው፡ በተለይ አሉታዊ የማንበብም ሆነ የመጻፍ ፍላጎት ባለበት ክፍል ቋንቋን በተበራችነት አውድ አስተምሮ ተማሪዎቹን ከትምህርት ቤት ውጪ ለሚጠብቋቸው ተግባቦታዊ ክንውኖች ብቁ ማድረግ አዳጋች ይሆናል፡፡ አልፎ አልፎ በገሃድ የሚታዩ 10ኛና 12ኛ ክፍል አጠናቀው በአማርኛ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ ያለመቻል ችግር የሚከሰትበት አንዱ ምክንያት

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ ፍላጎት ከማያዝ ጋር የሚገናኝ ሊሆን እንደሚችልም የአጥኚዋ ግምት ነው፡

በDörnyei & Ushioda (2011) የቀረበ ለሁለተኛ ቋንቋ የሚሆን ማበረታቻ ማቀድና ማጋበር ስልተ ትውራ በሁለተኛ ቋንቋ ትግበራና ማበረታቻ ላይ አጽንኦት የሚያደርግ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው አሉታዊ አመለካከትና ስሜት ሳይይዝ በሁለተኛ ቋንቋው ምን መቼ መናገር ወይም ማጋበር እንዳለበት መማሪያ አውደንና የማስተማሪያ ስልቶችን ከተጨባጭ ሁኔታዎች በማቀናጀት የሚቀርብ የማበረታቻ ስልት ነው፡

የማበረታቻ ስልት ተማሪዎች በሚማሩት ርእሰ ጉዳይ ተፈላጊውን ትኩረት እንዲይዙ ለማድረግ በሚገባ ሜለኩ ማቀድና ማጋበር ካልቻለ ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት አይችልም፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙ የማማህራኑ የማጎበብ ክፍለ ጊዜ ማበረታቻዎች የተማሪዎቹን ተመስጦ የማያዝ አቅም ከፍተኛ ነው ለማለት ባያስችልም በማጎበብ ክንውኑ ዙሪያ ትኩረት እንዲኖራቸው የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በማጎበብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የሚደረግላቸው ማበረታቻ አዳዲስ መረጃዎችን እንዲያስሱ ለማድረግ እንደሚያግዙ፣ የማበረታቻዎቹ ተማሪዎቹ ከቀሰሙ እውቀት፣ ካገኙት ልምድና መረጃ ጋር ተገናዛቢነት እና ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ ቀጣይነት ባለው ሜለኩ የሚደረገው ግፊት የተጠቆሙት ስታቲስቲካዊ ልኬት የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑን መካከለኛ ትኩረት የሚያመለክቱ ናቸው፡

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የማጎበቡ የመጻፍ ክንውኖችን ማቀናጀት በሁሉም የትምህርት ማስኮች የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ያሻሽላሉ፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በሚማሩት ነገር ዙሪያ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ስለሚያስፈልግና ማጎበቡ መጻፍን ማቀናጀት ስለሚያስችል ነው (Ambrose, Bridges እና DiPietro, 2010)፡፡ በዚህ መሰረት፤ ምንም እንኳን በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚደረጉት ከማጎበብ ጋር የተያያዙ የማበረታቻ ስልቶች ከመጻፍ ክሂል ማበረታቻ ትግበራ አንጻር ሲታዩ ማጎበጡን በማበረታታት የተሻለ ጥረት እንዳለ መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ መግለጽ ቢቻልም ከአጠቃላዩ የአማካይ አማካይ ስታቲስቲካዊ ልኬት አንጻር ሲታይ የማጎበብ ክሂል ማበረታቻው በቂና አስተማማኝ ነው ለማለት አያስችልም፡

ስኬታማ ተማሪዎች ምርጫዎቻቸውን፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን በማወቅ ጠንካራ ጎኖቻቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚጠቀሙት ሲሆን ደካማ ጎኖቻቸውን ለማሻሻል ጥረት ያደርጋሉ፡ ውጤታማ የቋንቋ ትምህርትም ከተማሪዎቹ ጥልቅ ስሜት ጋር መዛመድ ይኖርበታል (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ መምህራንም ትምህርቱን ከተማሪዎቹ ጥልቅ ስሜት ጋር ለማዛመድ የሚያስችሉ ስልቶችና ብልሃቶችን በመቀየስ ተማሪዎቹ ከቋንቋ ትምህርቱ በተሻለ ሜለኩ እውቀትና ግንዛቤ እንዲቀስሙ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ማበረታቻ ደግሞ አንዱና ዋናው መንገድ ነው (Reeve, 2013)፡፡

ማበረታቻው ለብዙ ተማሪዎች በራስ መተማመን አለቀዳጃቸውም፡ በእርግጥ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በራስ መተማመን በቀላሉ የሚገኝ አይደለም፡ ተማሪዎቹ በአንድ በኩል ከሁለተኛ ቋንቋ ለመዳው ጎን የአፍ መፍቻ ቋንቋን ተጽእኖ እየተቋቋሙ መማር ግድ ይላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስህተት ላለመስራት የሚያደርጉት ከማገር፣ ማሰብ፣ መጻፍ አውዶች ሲያፈገፍጉ ማየት የተለመደ ነው፡ በመሆኑም ማኛውም የማበረታቻ ስልት እነዚህን በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ችግሮች እግምት ውስጥ በማስገባትና ተማሪዎቹ በራሳቸው ማገድ የመማሪያ አውዱን እንዲቆጣጠሩት በሚያደርግ እንዲሁም ቀለል ባሉ ተግባራትና ልምምዶች ላይ በማትኮር በራስ ወደ መተማመን ደረጃ በደረጃ እንዲጓዙ ማበረታታት ግድ ይላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲጠቃ በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች ማበረታቻ በተማሪዎቹ ዘንድ በራስ መተማመን ለመፍጠር ያለው ጠቀሜታ የሚገበቀውን ያህል አሞቂ ባይሆንም የሚበረታታ ነው፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረትን ለማሟላት ሲባል ብቻ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ መሰረታዊ ስልጠና ያልወሰዱ የሌላ ትምህርት አይነት መምህራንን ባላቸው መደበኛ ክፍለ ጊዜ ማስ መስፈርትነት አማርኛን ደርበው እንዲያስተምሩ ማድረግ በትምህርቱ አቀባበልም ሆነ በማበረታቻ አተገባበር ፋይዳው ያነሰ ነው፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረት ባለበት ሊወሰድ የሚባው መፍትሄ የጂኦግራፊ ትምህርት መምህርን አማርኛ ቋንቋ አስተምር ከማለት ይልቅ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች አማርኛን ‹‹ማይነር›› ያደረጉ መምህራን ስለሚያታጡበነዚያ ላይ መሞርኮዝ የተሻለ እንደነበር ጥናቱ ቃኝቷል፡፡

## ምእራፍ አምስት

## የጥናቱ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ

ይህ ጥናት ያተኮረው ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና ላይ ነው፡ ጥናቱ ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅና የክፍል ምልከታ ላይ በመሞርኮዝ መረጃዎችን ሰብስቦና ተንትኖ በምእራፍ አራት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አራት ሲሆኑ እነሱም፤ (1) ***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች አሉ?*** (2) ***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው?*** (3) ***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በማንበብ ጊዜ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው?*** (4) ***መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ሲያጽፉ እና ሲያስነብቡ ተማሪዎቹን ለማበረታታት የሚጠቀሟቸው የማበረታቻ ስልቶች የቱን ያህል አነቃቂ ናቸው? የሚሉ ሲሆኑ፤*** መረጃዎቹ እርስ በርስ ተደጋጋፊ በሆነ ሁኔታ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስና ችግሩን በበቂ ሁኔታ ለመዳሰስ ያስቻሉ ናቸው፡ በምእራፍ አራት ተተንትነው በቀረቡት መረጃዎችና ግኝቶች ላይ በመሞርኮዝ ጥናቱ ከሚቀተለው ማጠቃለያ ላይ ደርሷል፡፡

## 5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች ***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ቢኖሩም ተደራሽነትና ተከታታይነት የሌላቸው መሆናቸውን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡*** በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርቱ ሂደት ላይ ብቻ አጽንኦት ከማድረግ ይልቅ በተማሪው ማህበራዊና ግላዊ ሁኔታዎች ላይ ተገቢውን አጽንኦት በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪው ፍላጎት ጋር የተጎዳኘ በቂና ጠቃሚ እንዲሁም ተለዋዋጭ ተደራሽ ማበረታቻ ማድረግ ያስፈልጋል (Dörnyei & Ushioda, 2011)፡፡ በተጠኑት ትምህርት ቤቶች የሚገበሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማበረታቻ ስልቶች ከተናጠል ይልቅ በቡድን አቋም ላይ ያተኮሩ፣ ተማሪዎቹ በህብረት እንዲሰሩ የሚያደርጉ የአቻ ክንውኖችንና በሚደገፍ የመማማር ብልሃቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡ እነዚህ በቡድን ቁጥጥ ላይ ያተኮሩ የማበረታቻ ስልቶች ተማሪዎቹ እርስ በርስ ሚደዳትንና አቻዊ ተስተምህሮን የሚጠናከሩ ናቸው፡ ይሁንና የአጽንኦቱና ተደራሽነቱ መጠን ውስን መሆኑ በትምህርት ቤቶቹ የተጠናከረ የማበረታቻ ትግበራ መኖሩን አያሳይም፡

ለሁለተኛ ቋንቋ የሚሟሟን ማበረታቻ መቅደና መተግበር በDörnyei & Ushioda (2011) የቀረበ የማበረታቻ ስልተ ትወራ ሲሆን፤ በሁለተኛ ቋንቋ ትግበራና ማበረታቻ ላይ አጽንኦት የሚያደርግና ተማሪው አሉታዊ አመለካከትና ስሜት ሳይይዝ በሁለተኛ ቋንቋው ምን መፍ መናገር ወይም ማድረግ እንዳለበት መማሪያ አውድንና የማስተማሪያ ስልቶችን ከተጨባጭ ሁኔታዎች በመቅናጀት የሚቀርብ የማበረታቻ ስልት ነው፡ መምህራኑ ***ማበረታቻ በቋንቋ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በአብዛኛው ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም በማበረታቻ አስፈላጊነት የአመለካከት ችግር ያለባቸው መምህራን የሉም፡፡*** ይሁንና በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን ተከታታይነት ባለው አኳኋን አያካሂዱም፡ የመምህራኑ ማበረታቻ አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ እንዲማሩ ያደረገላቸው አስተዋጽኦ ያን ያህል ጉልህና ተደራሽ አይደለም፡ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የፈጠረላቸው የመማሪያ ማድረክ በተማሪዎቹ ዘንድ የፈጠረው አዎንታዊ አመለካከትና የተነሳሽነት ስሜት ውስን ነው፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአብዛኛው ለተማሪዎቹ የሚደረግላቸው ማበረታቻ የትምህርት ግቦችን እንዲያስቀምጡ በማድረግ ላይ ያተኮረ አለመሆኑን ጥናቱ ደርሶበታል፡፡ በዚህ ረገድ ***ሊኖር የሚችለው ክፍተት መምህራኑ ከ***ቋንቋ መማሪያ ክፍሉና ከሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ተጨባጭ ሁኔታ የተገናዘቡ የማበረታቻ ስልቶችን የመቅደና ***ተለዋዋጭ የማበረታቻ ብልሃቶች ግንዛቤ እንደሚሆን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡***

ምንም እንኳን በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚደረጉት ከማበብ ጋር የተያያዙ የማበረታቻ ስልቶች ከማጻፍ ክሂል ማበረታቻ ትግበራ አንጻር ሲቃኙ ማእበብን በማበረታታት የተሻለ ጥረት

እንዳለ ሞዴጃዎቹን መሰረት በማድረግ መግለጽ ቢቻልም ከተለያዩ ሞዴጃዎች ውጤቶች አንጻር ሲታይ የማንበብ ክሂል ማበረታቻው በቂና አስተማማኝ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ በተለይ የአማርኛ ቋንቋ መምህር እጥረት ባለበት ትምህርት ቤት የጂኦግራፊ ትምህርት መምህርን አማርኛ ቋንቋ እንዲያስተምር ማስገደድ ለትምህርት አይነቱም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ የክሂል አቀባበልና ማጎልበት አለማስቻሉ ነው፡፡

ከመጻፍ ክሂል ጋር ተያይዞ ለተማሪዎቹ የሚቀርበው ማበረታቻ በአጠቃላይ ሞዴሉ ሲታይ ዝቅተኛ ይዞታ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ መጠኑና ተደራሽነቱ ላይ ጥያቄ ያለበት ቢሆንም፤ ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂል ክፍለ ጊዜ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ተገቢ መመሪያ መስጠት፣ የአማርኛ ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአትንና መዋቅርን እንዲጠብቁ ማለማመድ፣ በየጊዜው የጽህፈት ክንውኖቻችንን በማማማም ተማሪዎቹን ማበረታት፣ ለመጻፍ ክሂል ልምምድ የሚረዱ ክንውኖችን ማስተት፣ በመጻፍ እንዲበረታቱ የሚደርጉት ማበረታቻ ተማሪዎቹ ስህተቶቻቸውን እያረሙ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ የረዳቸው መሆኑን ሞዴጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ ነገር ግን በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ዘንድ በሚታዩ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት ማነስና ለመጻፍ ክንውን ተጋልጦ ማጣት ችግሮች፣ መምህራኑ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል የመጻፍ ክሂልን ለማበረታታት ባሉባቸው የቴክኒካዊ ብልሃቶች ግንዛቤ ክፍተት፤ እንዲሁም በመጻፍ ክሂል አንጻራዊ ውስብስብነት የተነሳ የማበረታቻ ትግበራቸው በጣም ውሱን ሆኖ ይገኛል፡፡ Arter, Spandel **እና** Culham (2010) **እንደገለጹት**፤ የመጻፍ ተግባርን ለማደራጀት አስፈላጊ የሆነው ጉዳይ ተገቢነት ያለው የመጻፍ ስልተ–ትወራ ማሚጥ ነው፡፡ መምህራን የመጻፍ ልምዳቸውንና የማስተማር ብቃታቸውን መሰረት በማድረግ እንዲሁም የተማሪዎቻቸውን ችሎታና ብቃት እግምት ውስጥ በማስገባት ምቹዊ በሆነ መንገድ እንዲጻፍበት ከተወሰነው ጉዳይ ጋር በሚጣጣም ሞዴሉ ስልተ–ትወራ ማሚጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በተጠኚዎቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሁለንተናዊ ሞዴሉ ለማንበብ ማበረታቻ የተሻለ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን በዋንኛነት ደግሞ የማንበብ ክንዋኔን ለመጻፍ ማነሻ ማድረጋቸውና ማንበብን ከመጻፍ ጋር አቀናጅተው ማስተማራቸው አጽንኦት የተሰጣቸው ከማንበብ ክሂል ጋር የተያያዙ ጠንካራ ማበረታቻዎች ናቸው፡፡ መምህራኑ *የሚተገብሯቸው የማንበብ ማበረታቻዎች የተማሪዎቹን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል የተወሰነ ድጋፍ ቢኖራቸውም፤ ከተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ዳራ ጋር የተያያዙ ችግሮችን* **ጨምሮ**፤ ሁሉንም ተማሪዎች በማንበብ ለማሳተፍ በየመማሪያ ክፍሉ ማንበብ አዳጋች የሚሆንባቸውና የቃላትን ትርጉም የሚረዱ ተማሪዎች መኖራቸው፣ አልፎ አልፎ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ ፍላጎት የሚያሳዩ፣ አይገባኝም ብለው ተስፋ የሚቆርጡ፣ ቋንቋውን አስተካክለው መናገር የማይችሉና የማንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ሁኔታ ብርቱ ትኩረት የሚሻይቅ መሆኑን ጥናቱ ቃኝቷል፡፡ ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርቱ ሂደት ላይ ብቻ አጽንኦት ከማድረግ ይልቅ በተማሪው ማህበራዊና ግላዊ ሁኔታዎች ላይ ተገቢውን አጽንኦት በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ

ከተማሪው ፍላጎት ጋር የተጎዳኘ በቂና ጠቃሚ ማበረታቻ ማድረግ ያስፈልጋል (Dörnyei & Ushioda, 2011) ያሉትን ልብ ማለት የሚገባቅ ነው፡

በተነቃቃ የተማሪዎች ተሳትፎ ከፍ ያለ የትምህርት ውጤታማነት እውን እንደሚሆንና ይህም በበኩሉ የተማሪዎችን ማበረታታት እንደሚያሳድግ ጥናቶች ያሳያሉ (Bunn, 2011)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ማበረታቻዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማጠናከር በተለይ በንባብ ክሂል ማዳበር ላይ የተወሰነ ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆንም፤ በተማሪዎቹ ላይ የሚያሳደሩት ያህል አዎንታዊ ለውጥ አለማምጣታቸውን ጥናቱ ደርሶበታል፡፡ ማበረታቻው ለብዙ ተማሪዎች በራስ መተማመን አላቀዳጃቸውም፡ በእርግጥ በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በራስ መተማመን በቀላሉ የሚገኝ አይደለም፡ ተማሪዎቹ በአንድ በኩል ከሁለተኛ ቋንቋ ለመዳውጎን የአፍ መፍቻ ቋንቋን ተጽእኖ እየተቋቋሙ መማር ግድ ይላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስህተት ላለመስራት ከመናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ አውዶች ሲያፈገፍጉ መዋት የተለመደ ነው፡ ይህን ችግር በመቅረፍ ተማሪዎቹ በተነቃቃ ሁኔታ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የጥንድና የቡድን ተግባራት ላይ ያተኮሩ ማበረታቻዎች መተግበር፣ በሚዲሎች ላይ እንዲደገፉ ማድረግና ስህተት እየፈጸሙ ከስህተቶቻቸው እየተማሩ እንዲቀጥሉ ማበረታታት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ተማሪዎች በመስራት፣ በማድረግ፣ በመጻፍ፣ በመፍጠር፣ ችግር በመፍታት ይማራሉ፡፡ ኢ-ተሳትፎአዊነት ወይም ተገብሮዊነት (passivity) የተማሪዎቹን ማበረታታት እና ትኩረት ይቀንሳል፡፡ የተማሪዎች ብርታት፣ ተሳትፎ እና ፈቃደኛነት የክፍል ውስጥ ትምህርቱ ትግበራ ጥራት ለውጤታማ መማር የሚያበረክተውን ድርሻ ይወስናል፡፡ በትንንሽ ምድቦች የሚካሄድ ተግባር እና የጥንድ ሥራ አጎልባች ሲሆን በራስ መተማመን ከፍ የሚያደርግና የማበረታቻ ምንጭ የመሆን ድርሻ አለው (Gardner እና Lambert, 2009፤ Ushioda, 2012)፡፡ መምህራኑ ለእነዚህ የማበረታቻ ስልቶች ተከታታይ በሆነ መልኩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

**5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ**

ከፍ ሲል ጥናቱ በደረሰባቸው ግኝቶችና የማጠቃለያ ሐሳቦች እንዲሁም በክለሳ ድርሳናት በቀረቡ ጠቃሚ ተሞክሮዎች በሚደገፍ የሚከተሉት የመፍትሄ ሐሳቦች ተጠቁመው ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

*1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማበረታቻ ስልቶችና ትግበራ ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠት፡-* ማበረታቻ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቀላጠፍና የመማሩን ክንዋኔ ውጤታማ ለማድረግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳለው ቢታመንም፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የማበረታቻ ትግበራ ውስንነት የሚታይበት ነው፡ ይህም በአንድ በኩል መምህራኑ ስለማበረታቻ ብልሃቶችና የትኞቹን የማበረታቻ ስልቶች ከምን አይነት ክንዋኔ ጋር አያይዞ ማቅረብ እንደሚገባ ባላቸው የግንዛቤ ክፍተት እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል ጅማ

ዩኒቨርሲቲና የጀማ ዘን ትምህርት ቢሮ በመቀናጀት ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለማጠረታቻ አተገባበር የአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲሰጥ ቢያደርጉ መልካም ይሆናል፡፡

*2. የማዳፍ ክሂል ተነሳሽነትን ማጎልበት* – ዝቅ ያለ የማጠረታቻ ውጤት በታየበት የማዳፍ ክሂል ዙሪያ ጠንካራ አጽንኦት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የማዳፍ ትምህርት ተነሳሽነትን ለማጎልበት የተማሪዎች እምነት እና በራስ መተማመን የጎላ ድርሻ አላቸው፡ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ለማዳፍ ትምህርት ያላቸው እምነት እና በራስ መተማመን የጠነከረ መሆን፣ ተነሳሽነታቸው አወንታዊ እንዲሆን ምክንያት ይሆናል፡፡ በተቃራኒው በማዳፍ ትምህርት ሂደት የተማሪዎቹ እምነት እና በራስ መተማመን እየቀነሰ መምጣት ተነሳሽነታቸው እንዳይሻሻል ምክንያት ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ ዘንድ የሚታየውን የማዳፍ ክሂል ተነሳሽነት ችግር ለማቃለል የሚረዳው አንዱ መንገድ ጽህፈትን ከዝቅተኛ አሃድ አንስቶ በማስተማር የተማሪዎቹን የክሂል ክፍተት ማጥበብ ነው፡ ከመማሪያ መጽሐፉ ትግበራ ጎን ለጎን ትክክለኛ የፊደል ቅርጾችን፣ የቃላትና የአረፍተ ነገር መዋቅሮችን መከለስ፣ ደጋግመው እንዲሰሩ ማለማመድና ስህተት እየሰሩ ከስህተቶቻው እንዲማሩ ማድረግ ብሎም ለዚሁ የሚረዱ ማቴሪያሎች መተግበር ከአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሚጠበቅ ድርሻ ነው፡

*3. ተዘውታሪ ቃላትን በተለያየ ስልትና አውድ ማስተማር፡* – ተጠኚዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መሆናቸው በማንበብ እና በማዳፍ ክሂል ችሎታቸውና ክሂሎቹን በማቀቃት ለመማር ባላቸው ዝግጁነት ላይ የራሱን ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የተለያዩ ቃላትን መማሪያ ብልሃቶችንና አውዶችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስተማር ይገባቸዋል፡፡ የተማሪዎቹ የቃላት ግንዛቤ ከተሻሻለ ለማንበብና ለማዳፍ የተሻለ ማቀቃት የሚያሳዩ ተማሪዎችን በብዛት ማግኘት ስለሚቻል፤ መምህራኑ ተዘውታሪነትና ባህል ገላጭነት ያላቸውን ቃላት በስፋት ማስተማር ቢችሉ መልካም ይሆናል፡፡ መምዋ እገዛዊ ቴክኒኮችም፤ ማሳየት፣ መምራት፣ ተግባርን በቀላል ደረጃዎች መከፋፈል፣ መማሪያ ማቅረብ፣ ማብራራት፣ ትኩረት እንዲኖር ማድረግና ማጠረታታትን ቢያካትት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹን የቃላት መማር ሂደት የሰመረ ሊያደርገው እንደሚችል ይታመናል፡፡

*4. እርስበርስ የሚረዳዱበትን እድል ማመቻቸት፡* – ይህ የእርስ በርስ መደጋገፍ ክንዋኔ ተማሪዎቹ ወደፊት በሚገፉበት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳብ ለሃሳብ መለዋወጥን፣ ልምድ መጋራትን፣ መረዳዳትን እንዲሁም በጻፉት ጉዳይ ዙሪያ ውይይት ማካሄድን ሁሉ ያካትታል፡፡ መምህሩ ቅደም ተከተላዊነት ባለው መንገድ እርስበርስ የሚደጋገፉበትንና ለየብቻቸው የሚሰሩባቸውን ጊዜያት ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ዋንኛው የማዳፍ ሂደት እያንዳንዱ ተማሪ በግል የሚያከናውነው ተግባር ተደርጎ መቀናጀት ይኖርበታል፡፡ የክፍል ውስጥ ተግባራት በጋራ በሚያከናውኑዋቸው ተግባራት መታጀብ ይኖርባቸዋል (Bachman 2011)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ በጋራ ለማንበብና ለማዳፍ የሚያስችሏቸው እድሎችንና አውዶችን ማመቻቸት ቢችሉ መልካም ነው፡ የጋራ ተግባሩ የሚከናወንበት አዋጭ ስልት ዙሪያ እንዲወያዩ ማድረግ፣ የሚሰጡዋቸው የማንበብና የማዳፍ ክንዋኔዎች

እንዴት ቢያከናውኑ እንደሚሻላቸው ሚወያየት፣ ተግባራቱን ለማከናወን የሚረዳቸው መሣሪያ (checklist) ማቅረብ፣ ባነበቡትና በጻፉት ላይ እርስ በርስ እንዲወያዩ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ እርስ በርስ የሚያጋገፉባቸውን ትንንሽ ቡድኖች መመሥረት የመሳሰሉት ክንዋኔዎች ለማበብር መጻፍ ክሂል መዳበር ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥሩላቸዋል፡፡

5. *የአጭርና ጊዜያት የቋንቋ ትምህርት ግቦችን እያስቀመጡ እንዲሜሩ ማበረታታት፡* – የቋንቋ ተማሪዎች የራሳቸውን ግቦች በማስቀመጥና በሚያገኙት ውጤታማነት አቅጣጫ የራሳቸውን የአጠናን ስልቶች በመከተል ውጤታማ ለመሆን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው በማገዝ፣ የቋንቋ መማር ፍላጎታቸውን በማሳደግና ለምን ቋንቋውን እንደሚማሩ በመገንዘብ ትምህርታዊ ግባቸውን ሊያሳኩ ይችላሉ (Gardner እና Lambert, 2009)፡፡ ከቋንቋ ትምህርቱ የሚያገኙትን ቁምነገር ለይቶ ማወቅና ግብን ማየት ወደ ማበረታታት ይመራቸዋል፡፡ ይህም በበኩሉ ከፍ ወዳለ የቋንቋ ብቃት ያደርሳቸዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸው እንደ ከተናጋሪዎቹ ጋር በበቂ ሁኔታ ተግባቦት ማካሄድ፣ በቋንቋው የተጻፉ መጻህፍትን በትክክል ማበብር አገናዝቦ መጻፍ የመሳሰሉ የተወሰነ የአጭር ጊዜ ግብ አስቀምጠው በመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲሳተፉ ማበረታታት (Ushioda, 2012) ቢችሉ በተሻለ ሁኔታ በማንቃት የተደገፈ አማርኛ ቋንቋ መሣሪያ ክፍል መፍጠር ያስችላቸዋል፡፡

### 5.3 የወደፊት ጥናት ሊከናወኑባቸው የሚቡ ርእሰጉዳዮች

በዚህ ጥናት ትኩረት ያልተሰጣቸውና በስፋት ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የወደፊት የጥናት ጥቆማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ይህ ጥናት ይዞ በተነሳቸው የጥናት አላማዎች መሰረት፤ ***የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን ሲማሩ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች ምን እንደሚመስሉ በመመርመር፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ በመፈተሽ፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስነብቡና ሲያስጽፉ የሚጠቀሙት የማበረታቻ ስልት የአነቃቂነት ደረጃ መፈተሽ ላይ አትኩሯል፡፡*** የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከማበረታቻ ስልቶችና ብልሃቶች ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት ሰፊና ጥልቅ ትኩረት የሚያይቅ ነው፡ በተለይ በከፊል ፍትነታዊ የአጠናን ስልት በመመርኮዝ የመቆጣጠሪያና የቁጥጥር ቡድኖች ናሙናዎችን በማዋረጥ በቅድመ ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ለቡድኖቹ የተለያዩ የማበረታቻ ቋቶችን አቅርቦ በማስተማር ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራ ጉልህ ጠቀሜታ

ያላቸውዓ የስልት ቋቶች ፈትሾ ማቅረብ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዳለው/እንዳላቸው ጥልቅና ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል፡፡

እንዲሁም የትኞቹ ቅይጥ የማበረታቻ ብልሃቶች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንደሚስማሙ ለሰዋሰው፣ ቃላትና ስነጽሁፍ ንኡሳን ክሂሎች ምን አይነት የማበረታቻ ስልት ቋቶች ጉልህ ጠቀሜታ እንዳላቸው በከፊል ፍትነታዊ የአጠናን ስልት በማድኮዝ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች ማበረታቻዎች ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ያላቸውዓ ተዛምዶ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ትኩረት የሚሻይቅ ነው፡

---

# ዋቢ


ልዑልሰገድ ባንተይርጋ (2007)፡፡ ‹‹በወላይትኛና በሲዳምኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ የንባብ ክሂል ለማስተማር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ትንተና››፡፡ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

አማረ ድጋፌ (2006)፣ ‹‹አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመጻፍ የሚያጋጥሟቸው ችግሮችና የማበረታቻ ስልቶች››፡፡ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004ዓ.ም.)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር (ሣስተኛ እትም፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

Ackner, W. (2011). Error and Corrective Feedback: Updated Theory and Classroom Practice, *English Teaching Forum,* XXXIII, No.2, p.38.

Al-Mahrooqi, R., & Asante, C. (2010). Analyzing the Use of Motivational Strategies by EFL Teachers in Oman. *Malaysian Journal of ELT Research*, 8 (1), 36-76.

Ambrose, S. A., Bridges, M. W., DiPietro, M. (2010). How Learning Works: Seven Research-Based Principles for Smart Teaching. San Francisco, CA: Wiley.

Arter, J.A., Spandel, V., Culham, R. (2010). Portfolio for Assessment and Format for Précis. The University of Texas at Austin.Retrievedfrom http://www.utexas.edu/courses/arens/can(n)on/PrecisTypes.pdf

Bachman, L.F. (2011). *Fundamental considerations in language testing.* Oxford: Oxford University Press.

Bataineh, R.F. (2015). Motivation and motivating in the foreign language

classroom', *Modern Language Journal* 78:74-80.

Bereiter, C. & Scardamalia, M. (2007). Textens mening och makt: metodbok i samhällsvetenskaplig text- och diskursanalys. 2. [omarb.] uppl. Lund: Studentlitteratur.

Bernaus, M., & Gardner, R. C. (2016). Teacher motivation strategies, students perceptions, student motivation, and English achievement. *The Modern Language Journal*, 08, 387-401.

Bunn, M. (2011). How to read like a writer. In C. Lowe & P. Zemliansky (Eds.), Writing spaces: readings on writing, Volume 2 (pp. 71-86). Anderson, SC: Parlor Press.

Carson, J. (2011). Second language writing and second language acquisition. *In T. Silva and P.Matsuda (Eds.), On second language writing* (pp. 191-200). Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Cedar, P. S. (2014). Transferability and translatability of idioms by Thai-speaking

Chatzisarantis, N. L. D., & Hagger, M. S. (2013). Effects of an intervention based on self-determination theory on self-reported leisure-time physical activity participation. *Psychology & Health, 24*, 29-48. doi: 10.1080/08870440701809533

Clement, R. (2012). Ethnicity, contact and communicative competence in a second language. In H. Giles, W. P. Robinson & P. M Smith (Eds.), Language: Social psychological perspectives (pp. 147-154). Oxford: Pergamon.

Clément, R. and Kimberly, A. (2014). Motivation, Self-confidence, and Group Cohesion in the Foreign Language Classroom in Oman, English Language Teaching. Research in the Middle East and North Africa, 10.1007/978-3- 319-98533-6_22, (479-505), (2018).

Creswell, J. W., & Plano, C. V. L. (2017). *Designing and conducting mixed methods research*. Thousand Oaks, Calif.: SAGE Publications.

Daniels, E., & Steres, M. (2011). Examining the effects of a school-wide reading culture on the engagement of middle school students. *Research in Middle Level Education - Online*, *35*, 1-13.

Debra W. H. (2015). Improving Academic English at Outdoor Nature Centers. Essential Teacher.

Dörnyei, Z. (2015). The psychology of the language learner: Individual differences in second language acquisition. Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum.

Dörnyei, Z. (2018). Motivation in second and foreign language learning. Language Teaching, 31 (3), 117-135.

Dörnyei, Z., & Ushioda, E. (2013). Teaching and researching: Motivation. (2nd ed.). Routledge.

Ellis, Rod (2010). *Current issues in the teaching of English grammar: an SLA perspective.* Tesol Quarterly 40(1): 83-107.

Endale Kumsa (2015). English Language Teachers' Motivational Strategies In Helping Students Develop Writing Skills: The Case Of Shebe & Seka High Schools.. Jimma University College Of Social Sciences And Humanities Department Of English Language And Literature

Ericsson, K. A., Krampe, R. T., & Tescher-Romer, C. (2013). The role of deliberate practice in the acquisition of expert performance. Psychological Review, 100, 363-406.

Freeman, L.D. (2010). *Techniques and principles in language teaching*. Oxford: Oxford University Press.

Gardner, R. C. (2016). "The socio-educational model of second language acquisition". *Canadian Issues*: 24–27.

Gardner (2013) ‹‹Attitudes, Motivation, and Second Language Learning››. *Canadian Issues. 33—39.*

Gardner, R. C.; Lambert, W. E. (2009). "Motivational variables in second- language acquisition". Canadian Journal of Psychology. **13**: 266–272.

Geberew Tulu Mekonnen (2014), EFL classroom Assessment: *Teachers' Practice and Teaching Techniques Adjustment in Ethiopia,* 9(20),1071-1089, October 2014, DOI: 10.5897/ERR2014.1857, retrieved on 28/ 01/2015

Greene, S. (2012). Mining texts in reading to write. Occasional Paper, 29, n.pag.

Hedge, T. (2008). Resource book for Teachers. Oxford: Oxford University Press. Hillsdale, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Jodai, H. and Zafarghandi, A. (2013). Motivation, Integrativeness, Organizational Influence, Anxiety, and EnglishAchievement. Glottotheory. **4** (2). doi:10.1524/glot.2013 .0012. ISSN 21 96-6907.

Masgoret, A.M. and Gardner, R. C. (2013). Attitudes, Motivation, and Second Language Learning: A Meta-Analysis of Studies Conducted by Gardner and Associates. Adaptive Hypermedia in Education, Advanced Methodologies and Technologies in Modern Education Delivery, 10.4018/978-1-5225-7365-4.ch015, (178-191).

Reeve, J. (2013). Understanding motivation and emotion (6 ed.). Hoboken, NJ: Wiley.

Richards, J. & Renandya, W. (eds). (2012) Methodology in LanguageTeaching: An Anthology of Current Practice. Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W. M. (2008) *Teaching Foreign Language Skills.* Chicago: The University of Chicago Press.

Shaaban, K. & Ghaith, G. (2013). Student motivation to learn English as a foreign language. *Foreign Language Annals,* 33(6), 632-644.

Syverson, M. A. (2016). A reference guide for the learning record. The Learning Record. Retrieved from http://www.learningrecord.org/olr.html

Ushioda, E. (2012) Motivation: L2 learning as a special case? In S. Mercer, S. Ryan, & M. Williams (Eds.), Psychology for language learning (pp. 58-73). Basingstoke, HA: Palgrave Macmillan.

Williams, M., & Burden, R. L. (2015). Psychology for teachers. Cambridge University Press.

Williams, W. & Burden, Z. (2015). Understanding L2 motivation: On with the challenge! Modern *Language Journal,* 78,515-523.

Ying, S. Y. (2017). *Types of errors in English compositions by Chinese students: a search for interlanguage.* Unpublished master's thesis, Fu Jen Catholic University, Taipei, Taiwan).

Zewge Haile (2014). A Comparative Study of Students' Performance In Efl Paragraph Writing: Grade 11 In Jimma And Eldan Preparatory Schools In Focus. A Thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for Master of Arts in TEFL. Jimma University College of Social Sciences and Humanities Department of English Language and Literature MA in TEFL Teaching English as a Foreign Language (TEFL).

## አባሪዎች

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር**

### አባሪ 1፡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ለማወቅ የቀረበ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች!

ይህ መጠይቅ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ምን እንደሚመስል ለማጥናት የቀረበ ነው፡፡ ተማሪዎች የምትሰጧቸው መረጃዎች ለጥናታዊ ተግባር ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል መሆኑን አስቀድሜ እየገለጽኩ በቀረቡላችሁ ጥያቄዎች መሰረት ለእናንተ የክፍል ውስጥ የመማር ተሞክሮ ትክክል የሆኑትን ‹‹በጣም እስማማለሁ››፣ ‹‹እስማማለሁ››፣ ‹‹አቋም የለኝም››፣ ‹‹አልስማማም›› ወይም ‹‹ፈጽሞ አልስማማም›› ከሚሉት

አማራጭ መልሶች አንዱን ብቻ በመምረጥ መልሶቻችሁን ስጡ፡፡ ስለትብብራችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡- የተጠኚዎች ግለሰባዊ መረጃ**

1) ጾታ፡- ሀ) ወንድ ____________ ለ) ሴት____________

2) አፍ መፍቻ ቋንቋ፡ – ሀ) አማርኛ _______ ለ) ኦሮምኛ _______ ሐ) ሌላ _______

**ክፍል ሁለት፡- የጥናቱ መረጃ**

ከሥር በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ሐሳቦች በሚገባ አንብባችሁ ስታበቁ፤ ለእናንተ እውነት የሆኑትን በመለየት የስምምነታችሁን ደረጃ በሚወክሉ ሣጥኖች ውስጥ

(√) ምልክት አስቀምጡ፡

ማሳሰቢያ፡- በጣምእስማማለሁ 5
እስማማለሁ 4

አቋም የለኝም 3

አልስማማም 2

ፈጽሞ አልስማማም 1 ነጥብ የመልስ አማራጮችን ይወክላሉ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የመልስ አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አቋም የለኝም | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የማበረታቻ ስልቶችን ያካሂዳሉ፡፡ | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ትምህርቱን በተነቃቃ ሁኔታ እንድማር ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የመማር ዝንባሌና ፍላጎቴን ከፍ አድርጎልኛል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማብረታቻ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ | | | | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ ትምህርቴን በኃላፊነት ማፈስ እንዳከናውን ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ማበረታቻ የትምህርቱን ውጤት ለማሻሻል አግዞኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በመማር ሂደት የሚያጋጥሙኝን ችግሮች ለማቃለል ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በራስ መተማመን ፈጥሮልኛል፡፡ | | | | | |
| 9 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ ጠንካራና ደካማ ጎኖቼን ለይቼ በማወቅ ጠንክሬ እንድሰራ ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 10 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ ምቹ የመማሪያ መድረክ ፈጥሮልኛል፡፡ | | | | | |
| 11 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በቋንቋ ለመዳ ሂደቱ ተሳትፎዬን ከፍ አድርጎልኛል፡፡ | | | | | |
| 12 | አማርኛ ቋንቋ ስማር የሚደረግልኝ ማበረታቻ በክፍል ውስጥ በጓደኛዊ ስሜት እንድማር አግዞኛል፡፡ | | | | | |
| 13 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ ክፍሉን በራሳችን መንገድ እንድንጠቀምበት አድርጓል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የመቻል ስሜት እየተሰማኝ እንድንማር ለማድረግ አስተዋጽኦ አለው፡ | | | | | |
| 15 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የትምህርት ግቦችን እንድናስቀምጥ በማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡ | | | | | |
| 16 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ የጥንድና የቡድን ተግባራትን ያካተተ ነው፡ | | | | | |
| 17 | አማርኛ ቋንቋ ስንማር የሚደረግልን ማበረታቻ በለውጥ አምጪክንዋኔዎች የተደገፈ ነው፡ | | | | | |
| 18 | በንባብና ጽህፈት ክሂሎች ክፍለ ጊዜ በቂ ማበረታቻ ይደረግልናል፡፡ | | | | | |
| 19 | በንባብና ጽህፈት ክሂሎች ክፍለ ጊዜ እንዴት ማንበብና መጻፍ እንዳለብን ተገቢ መመሪያ ከመምህራችን ይሰጠናል፡፡ | | | | | |
| 20 | በንባብና ጽህፈት ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ ከቀሰምነው እውቀት፣ ካገኘነው ልምድና ሚጃ ጋር ተገናዛቢ ነው፡ | | | | | |
| 21 | በንባብና ጽህፈት ክሂሎች ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ በምንማረው ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ፈጣሪነቱ ከፍ ያለ ነው፡ | | | | | |
| 22 | በንባብና ጽህፈት ክሂሎች ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ አዳዲስ ሚጃዎችን እንድናስስ ያደርገናል፡፡ | | | | | |
| 23 | በንባብና ጽህፈት ክሂሎች ክፍለ ጊዜ የሚደረግልን ማበረታቻ ለልምምድ የሚረዱ ክንውኖችን ያካተተ ነው፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | በመሚያ ክፍላችን ውስጥ የማበብና የመጻፍ ችሎታችንን እንድናሻሽል ለሚረግ በሚዳ ሜኪ መምህራችን ንበብን ከጽህፈት ጋር አቀናጅተው ያስተምሯሉ፡ | | | | | |
| 25 | የአሚኛ ቋንቋ መምህራችን በየጊዜው የንበብና ጽህፈት ክንውኖቻችንን በማምም ያበረታቱናል፡፡ | | | | | |
| 26 | የአሚኛ ቋንቋ መምህራችን ራሳችን እንድናነብ ቀጣይነት ባለው ሜኪ ግፊት ያደርጋሉ፡ | | | | | |
| 27 | የአሚኛ ቋንቋ መምህራችን በድርሰት ጽህፈት እንድንበረታታ የሚደርጉት ማበረታቻ ስህተቶቼን እያረሙ የጽህፈት ችሎታዬን እንዳሳድግ ረድቶኛል፡፡ | | | | | |
| 28 | የአሚኛ ቋንቋ መምህራችን ተከታታይ የድርሰት ጽህፈት መራ እንድናደርግ ያበረታቱናል፡፡ | | | | | |
| 29 | መምህራችን የአሚኛ ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአትንና መዋቅርን እንድንጠብቅ ያለማምዱናል፡፡ | | | | | |
| 30 | መምህራችን አዎንታዊ የሆነ የጽህፈትና የንበብ መሚያ ምቹ ደባብ ይፈጥሩልናል፡፡ | | | | | |
| 31 | የአሚኛ ቋንቋ መሚያ ክፍላችን በጽህፈት ተግባር እንድንበረታታ አዎንታዊ ግፊት ፈጣሪ ነው፡ | | | | | |
| 32 | የአሚኛ ቋንቋ መሚያ ክፍላችን በተሚዎች መካከል የመተባበርና የሚዳዳት ስሜት ፈጣሪ ነው፡ | | | | | |
| 33 | በአሚኛ ቋንቋ መሚያ ክፍል መምህራችን ከችሎታ፣ ልምድና ፍላጎታችን የተዛመዱ ተግባራትን በማቅረብ ያነቃቁናል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 34 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን በጽህፈት ተግባር እንድንበረታታ የጽህፈት መቅረ /ዎርክ ሾፕ/ ይሰጡናል፡፡ | | | | | |
| 35 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ብዙ ጊዜ የንባብ ክንዋኔን ለጽህፈት መነሻ ያደርጋሉ፡፡ | | | | | |
| 36 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ደጋግመን እንድንጽፍ በማድረግ ተከታታይ በሆነ መልኩ ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል፡፡ | | | | | |

*(ከClement & Kimberly (2014) ለጥናቱ እንዲስማማ (adapt) ተደርጎ የተወሰደ)*

## አባሪ 2፡ ቃለመጠይቅ

ውድ መምህር!

በቅድሚያ ለዚህ ቃለመጠይቅ ትብብርዎን ስላሳዩኝ ከልብ አመሰግንዎታለሁ፡፡ የዚህ ቃለመጠይቅ አላማ በጢሮ አፈታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ሲማሩ መምህራን የሚያደርጓቸው ማበረታቻዎች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ ለሚደረገው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡ የሚሰበሰበው መረጃ ሚስጥር በሚስጥር የሚያገለግለው ለትምህርታዊ ጥናት አላማ ብቻ ይሆናል፡፡ የሚሰጡኝ መረጃ ትክክለኛ መሆን የጥናቱን ስራ ለማካካት ወሳኝ እንደሆነ በትህትና እገልጽልዎታለሁ፡፡ ጊዜዎን በመሰዋት በቃለመጠይቁ ተሳታፊነት ስላሳዩኝ ቀና ትብብር አስቀድሜ ምስጋናዬን አቀርብልዎታለሁ፡

1. እርስዎ **አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎችን እንዲጨብጡ የሚያደርጉላቸው ማበረታቻዎች አሉ**?
2. **የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ተማሪዎችዎ ሲጽፉ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው**?

---

3. የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ለተማሪዎችዎ በንባብ ጊዜ የሚያደርጉላቸው የማበረታቻ ስልቶች ምን ምን ናቸው?
4. በክፍል ውስጥ የቋንቋ እና የስነጽሁፍ እውቀቶችን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማበረታቻ ስልት ተማሪዎችዎን ምን ያህል ያነቃቃቸዋል?
5. የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ለተማሪዎች በሚያካሂዱቸው የማበረታቻ ስልቶች ስኬታማ አተገባበር ዙሪያ የሚያጋጥሙዎት ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልኝ?

አመሰግናለሁ!

---

## አባሪ 3፡ የምልከታ መሪያ ነጥቦች (Observation Check List)

1. መማሪያ ክፍል፡- ____________
2. ምልከታው የተካሄደበት ቀን፡ -____________________________
3. የምልከታ ዙር፡- 1ኛ____ 2ኛ____ 3ኛ____
4. ምልከታው ያተኮረበት ክሂል፡- ንባብ ____ ጽህፈት ____

**የምልከታ መሪያ ነጥቦች**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ነጥቦች | ከምልከታው የተገኘ ውጤት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሉ የማበረታቻ ስልት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያግፍ ሁኔታ ታቅዷል ? | | | |
| 2 | መምህሩ የሚያካሂዱት ማበረታቻ ለተማሪዎቹ ችሎታና ፍላጎት በሚመጥን መልኩ የቀረበ ነው? | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ማበረታቻው ተማሪዎቹን ጓደኛ የሚያደርግና ችግራቸውን አውቆ የሚረዳት መምህን ተከትሏል? | | | |
| 4 | የማበረታቻ ስልቱ የሚሰጠው ትምህርት አላማ ይዘት ግባዊ ከሚያደርግ አንጻር በሚገባ ተደራጅቷል? | | | |
| 5 | የማበረታቻ ስልቱ በተማሪዎቹ አስተሳሰብና አሰራር ላይ ተፈላጊውን አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት በቂ ነው? | | | |
| 6 | የማበረታቻ ስልቱ ተማሪ ተኮር በሆነ መንገድ ተደራጅቶ ቀርቧል? | | | |
| 7 | ማበረታቻው ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎቹ አቅጣጫ ጠቋሚ በሆነ መልክ ቀርቧል? | | | |
| 8 | የማበረታቻ ዘዴው በተለዋዋጭ እና አነቃቂ ስልቶች የታጀበ ነው? | | | |
| 9 | የማበረታቻ ስልቱ ለተማሪዎቹ የጥንድና የቡድን ተግባራትን በማቅረብ በራስ መተማመን እንዲያሳድጉ ማስቻሉን ታሳቢ አድርጎ የቀረበ ነው? | | | |
| 10 | በመማሪያ ክፍሉ ተማሪዎች የአጭር ጊዜ ግቦቻቸውን እንዲያስቀምጡ በቂ ማነቃቂያ ተደርጓል? | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ የማከናወን /የመቻል/ ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋሉ? | | | |
| 12 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ የመማሪያ ክፍሉን ድባብ በራሳቸው መንገድ እንዲቆጣጠሩት ያደርጋሉ? | | | |
| 13 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ተማሪዎቹ ምኞት ተሰምቷቸው እንዲማሩ ለማድረግ የሚያደርጉት ጥረት አለ? | | | |
| 14 | መምህሩ በተገቢ ጊዜና ሁኔታ ተደግፈው ምጋቤ ምላሽ ያቀርባሉ? | | | |
| 15 | ተማሪዎች ሲያነቡ /ሲጽፉ የሚደረግላቸው ማበረታቻ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የተማሪዎቹን የንባብ /የጽህፈት ክሂል ለማሻሻል በሚያስችል መልኩ የተደራጀ መሆኑ ይታያል? | | | |